# የትምህርት ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የትምህርት ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

# (የሥልጠና ሞጁል)

**ህዳር 2017 ዓ.ም**

**አዲስ አባባ**

**ኢትዮጵያ**

# የትምህርት ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)


አዘጋጆች፡-

አቢ ለማ (PhD) (ጅማ ዩኒቨርሲቲ)

ዓለማየሁ ተክለማርያም (PhD) (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኋላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ



© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ.ም

# የይዘት ማዉጫ

ይዘት-------------------------------------------------------------------------------------------------ገጽ
መግቢያ ..... 5
የትምህርት መስኩ ስልጣንና ተግባራት ..... 6
የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ ..... 7
የሚጠበቁ የባህሪ ገጽታዎች ..... 7
የሞጁሉ ይዘት ..... 8
የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ ..... 8
የተሳታፊዎች አደረጃጀትና የማሰልጠኛ ስልት ..... 9
ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ..... 9
የስልጠናው ተተኳሪዎች ..... 9
የስልጠናው ግምገማ ..... 10
ምዕራፍ አንድ፡ የሙስና ወንጀሎችና አይነቶች (2 ሰዓታት) ..... 11
1.1.የሙስና ምንነትና አይነቶቹ ..... 11
1.2.የትምህርት ጽንሰ ሀሳብና ግቦቹ ..... 16
1.3.ትምህርት ለፀረ-ሙስና መሳሪያነት ..... 18
1.4.የሙስና ወንጀሎች ምንነት፣ ባህሪያትና አይነቶቹ ..... 19
የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ ..... 32
የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች ..... 32
ምዕራፍ ሁለት፡ በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎችና የሚስተዋሉ ክስተቶች (7 ሰዓታት)..33
2.1.በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትና ምክንያቶች ..... 34
2.2.የትምህርት ጥራት መዉድቅ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉ ቁርኝት ..... 40
2.3.የመምህራን ስልጠናና የስራ ስምሪት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ ቁርኝት ..... 43
2.4.ሥርዓተ-ትምህርት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉ ግንኙነት ..... 46
2.5.የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ከሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ጋር ያለዉ ቁርኝት ..... 49
2.6.ሃላፊነትና ተጠያቂነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ ግንኙነት ..... 51
2.7.ሥነ-ምግባርና ዕሴቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ ግንኙነት ..... 54
2.8.በትምህርት መስኩ የሙስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ..... 57
2.9.በትምህርት መስኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ያሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ..... 64
2.10. በአካዳሚክ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ..... 69

የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ........ 74
የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........ 75
ምዕራፍ ሶስት፡- በትምህርት ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች እና የመከላከያ ስልቶች (3 ሰዓታት) ........ 76
3.1.በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች አስመልክቶ በመስኩ የተደረጉ የጥናት ዉጤቶች ........ 77
3.2.የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መጋለጥ በትዉልድ ግንባታ ላይ የሚያሰከትለዉ ጉዳት ........ 80
3.3.የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መጋለጥ በትምህርት ጥራት ላይ የሚያሰከትለዉ ጉዳት ........ 81
3.4.የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መጋለጥ በአገር ላይ የሚያሰከትለዉ ጉዳቶች ........ 83
3.5.በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶች ........ 84
የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ........ 93
የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ይጣቄዎች ........ 94
የሞጁሉ የራስ-ብቃት መገምገሚያ ጥያቄዎች ........ 95
ዋቢዎች/ማጣቀሻዎች ........ 97

## መግቢያ

ከመንግስትና የግል ማህበራዊ ሚዲያዎች ዘወትር እንደምንሰማው የትምህርት ሥርዓታችን ሥር ለሰደደ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ መሆኑን የሚያመላክቱ ጉዳዮች በስፋት ይቀርባሉ፡፡ ትምህርት ሥነ-ምግባርንና እሴቶችን በመገንባት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል ሲገባው እንዴት ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ ሊሆን ቻለ? የትምህርት ሥርዓቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ ከሆነ ፋይዳውስ ምንድነው? ትምህርት ለአዕምሮ ልማት መዋል ሲገባው እንዴት የአዕምሮ ጥፋት ይሆናል? ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ጥፋት መሆናቸዉና ትምህርት ደግሞ እነዚህን ጥፋቶች በመዋጋት ሂደት የሚኖረዉ አዎንታዊ ሚና እጅግ የጎላ ነዉና፡፡ ይህ የሚያመላክተን የሚሰጠዉ ትምህርትም ሆነ ስርዓተ-ትምህርቱም በራሱ ችግር ያለበት መሆኑን ወይም በጠንካራ ሥነ-ምግባርና የሞራል ልዕልና ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን ነው፡፡ ዛሬ በርካታ ሰዎች ስኬትን እውን ማድረግ የሚፈልጉት ጥራት ባለው ማንነትና በጠንካራ የሥራ ውጤት ሳይሆን በአድልዖ፣ በሙስና እና በማጭበርበር መንገድ በመጓዝ ነው፡፡ የትምህርት ሰነድን በመግዛትና ሥራ በመቀጠር በኢትዮጵያ የታየው ማጭበርብር አንዱ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ ሙስና በተስፋፋ ቁጥር ሰው በጥረቱ ማግኘት የሚፈልገውንና አገኛለሁ ብሎ የሚጠብቀው የቁርኝት ገመድ ይበጥሳል፡፡ አብዛኛው ሰው ያለምንም ጥረት አንድን ነገር አገኛለሁ ብሎ የሚጠብቅ ከሆነ አደገኛ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ሁኔታ የአገርን ምጣኔ-ሀብታዊና ማህበራዊ እድገት ያቀጭጫል፡፡ የአንድን ማህበረሰብ የወደፊት ራእይ፤ እድገትና ሕይወት ያዳክማል፡፡ ሙስና ባለበት የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ትምህርት ቤቶች ለዜጎች ተደራሽ ሊሆኑ አይችሉም፤ የትምህርት ጥራት አይታሰብም፤ ምክንያቱም ትውልዱ እየተመለከተ የሚያድገው በጥረትና በጠንካራ ሥራ ሀብትን ማግኘት እንደሞኝነት ሲቆጠር፣ ማጭበርበርና መስረቅ ግን እንደ አዋቂነትና ብልህነት እየተወሰደ ያለ ነገር መሆኑን ነው፡፡ ይህ አካሄድ ግን የአንድን አገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን የሚንድ አደገኛ ችግር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ጥራት ያለው ትምህርት ስነ-ምግባርንና ሞራልን የሚገነባ ነው፡፡ ሰዎች የተሻለ ሕይወት ለመምራት የሚያስችላቸውና በሕይወት ዘመን የሚጠቀሙበትን ተገቢነት ያለው በቂ ገቢ በእውቀታቸውና በክሕሎቶቻቸው እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ነው፡፡ የትምህርት ሥርዓት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመጸየፍና በመከላከል ረገድ ለሌሎች አርኣያ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በአገራችን የምናየው ከዚህ በተቃራኒ ነው፡፡ አሁንም ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የመከላከል ሂደቱ በጠንካራ አሰራር ላይ የተመሰረተ አይመስልም፡፡ ስለዚህ ይህ ሞጁል በትምህርት ዘርፉ የሚስተዋሉትን ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ታቅዶ የተዘጋጀ የማሰልጠኛ ሞጁል ነው፡፡ ሞጁሉ በአምስት ዋና ዋና ምዕራፎች ተከፍሎ የተደራጀ ነው፡፡

## የትምህርት መስኩ ስልጣንና ተግባራት

በትምህርት መስኩ ያሉትን ሁሉንም ዘርፎች የሚወክል ስልጣንና ተግባራት በሙሉ መዘርዘር አስቸጋሪ ቢሆንም ለመነሻ ያክል ለትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ) የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችና እና ፕሮግራሞች ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ የትምህርት እና የትምህርት ተቋማትን ስታንዳርድ ያወጣል፣ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

ሐ) የአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲና ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ዝግጅት፣ ሪከርድ መያዝና የምስክር ወረቀት የመስጠት ሂደቶችን በበላይነት ያስተባብራል፤

መ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በጥናትና ምርምር የጎለበቱ እንዲሆኑ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ የጥናትና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ያመቻቻል፤

ሠ) ከኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ረ) የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አፈጻጸም ይከታተላል፤

ሰ) የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሐዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሸ) የአጠቃላይ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃ መውጣቱን ያረጋግጣል፤ በተቋማቱ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርት መሠጠቱን ይከታተላል፤

ቀ) ጥራቱን የጠበቀ የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፤

በ) ትምህርትን በተመለከተ ሀገራዊ የአሕዝቦት ተግባራትን ያከናውናል፣

ተ) በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ሥራ ላይ ያውላል። በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ውጪ ያሉ ሥልጣንና ተግባራት እና ለትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ትምህርት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

### *የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ*

የዚህ ሞጁል ዋና ዓላማ የስልጠናው ተሳታፊዎች በስልጠና ሂደት ውስጥ በትምህርት ዘርፉ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲሁም የመከላከያ ስልቶችን አስመልክቶ እውቀት፣ ክህሎትና ሙስናን የሚጸየፍ አመለካከት እንዲጎናጸፉ ለማድረግ ነዉ። ይህን አቅም በመጎናጸፍ ስልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላም ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳቶች በመረዳት ሙስናን እንዲጸየፉ፣ በሥራ ቦታና በማንኛውም ማህበራዊ ቦታዎች ሁሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን እንዲከላከሉና ተገልጋዩን ማህበረሰብ በቅንነት፣ በታማኝነትና በብቃት እንዲያለግሉ ማስቻል ነው።

### *የሚጠበቁ የባህሪ ገጽታዎች*

ከዚህ ሞጁል ፍጻሜ በኋላ ሰልጣኞች፡-

- በትምህርት ዘርፉ የሙስናን ምንነት ተንትነው ያስረዳሉ።
- ሙስና ወንጀል መሆኑን ተንትነው ይገልጻሉ።
- በሚሰሩበት የትምህርት ተቋመ/ክፍል የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትን ይተነትናሉ።
- በትምርቱ ዘርፉ ለሙስና ተጋላጫ የሚያደርጉ ምክንያቶችን በመዘርዘር ያስረዳሉ።
- በትምህረት መስኩ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመለየት በዝርዝር ያስረዳሉ።
- ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በትምህርት መስኩ መንሰራፋት የሚያስከትሉትን ጉዳቶች በመገምገም እንደጉዳታቸዉ መጠን በመዘርዘር ያብራራሉ።

- በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉትን ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን በመገንዘብ ስራ ላይ የሚዉሉበት መንገድ ይገልጻሉ፡፡
- የመከላከያ ስልቶችን በሚገባ በመረዳትና በመጠቀም ሙስናዎችንና ብልሹ አሰራሮችን ይከላከላሉ፡፡
- በስልጠናዉ ያጎለበቱትን እውቀት፣ ክህሎት እና የአመለካከት ለዉጥ በመጠቀም በትምህርት መስኩ ያለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር በመከላከል ስራ ግንባር-ቀደም ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

### *የሞጁሉ ይዘት*

የዚህ ሞጁል አበይት ይዘቶች መግቢያዉን ሳያካትት **በሶስት** ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈሉ ናቸዉ፡፡ በምዕራፍ አንድ፡- የሙስና ወንጀሎች እና አይነቶቹ፤ በምዕራፍ ሁለት፡- በትምህርት ዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትና ክስተቶቹ እንዲሁም በምዕራፍ ሶስት፡- በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች እና የመከላከያ ስልቶች/ዜዴዎች ቀርቧል፡፡ ከነዚህ ዋና ዋና ርዕሶች ስር ደግሞ ቀጥታ ግንኙነት ያላቸዉ ጉዳዮች በተለያዩ ክፍሎች ሰፋ ባለ መልኩ ቀርበዋል፡፡ ዝርዝሩን በየምዕራፉ ስር በሚኖሩት የመግቢያ ሃሳቦችና በማዉጫዉ ላይ ማየት ይቻላል፡፡ ሞጁሉን በአግባቡ ተከታትሎ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገዉ ጊዜ **ሁለት ቀናት** የሚጠይቅ መሆኑና 12 **ሰዓታትም እንደሚፈጅ** ይገመታል፡፡

### *የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ*

የስልጠናዉ አመቻች የሆነ ሰው ይዘቶችን በሙሉ በገለጻ ያቀርባል፡፡ ለውይይት የሚሆኑ ጥያቅዎችን በማዘጋጀት ሰልጣኞችን ያወያያል፡፡ ተሳታፊዎችም በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉ የሙስና፣ ብልሹ አሰራሮችና ክስተቶችን ተሞክሯቸውን እንዲያጋሩና በማድረግ የስልጠና ሂደቱ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡ በዚህ የስልጠና ሂደት ተሳታፊዎች በሚያቀርቡት ሀሳብ፣ ተሞክሮዎችን ይጋራሉ፣ አሰልጣኙ ይዘቱን በስፋት ካቀረበ በኂላ መመሪያዎችን በመስጠት፣ በማበረታታትና ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲያቀርቡ በማድግ ስልጠናውን ይመራል፡፡ ሞጁሉም ለተሳታፊዎች እንዲሰራጥ ያርጋል፡፡ በመጨረሻም አሰልጣኙ ማብራሪያ እና ማጠቃለያ በመስጠት ስልጠናዉን ያጠናክራል፡፡

### *የተሳታፊዎች አደረጃጀትና የማሰልጠኛ ስልት*

የስልጠናዉ አሰጣጣጥ ሙሉ በሙሉ ሰልጣኞችን ማዕከል ያደረገ ሆኖ የሚከተሉትን ሂደቶች ይከተላል፡-

ሀ. አሰልጣኙ የተዘጋጀውን የማሰልጠኛ ሞዱል መሰረት በማድረግ ገለጻ ያደርጋል

ለ. ለውይይት የሚሆኑ ጥያቄዎችንና ሀሳቦችን ያራጃል፡፡

ሐ. ከተሳታፊዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ተቀብሎ ያብራራል፡፡

መ. ተሳታፊዎች ተሞክሯቸውን እንዲያቀርቡ እድሎችን ያመቻቻል፡፡

ሠ. አሰልጣኙ ማጠቃለያ ይሰጥና ስልጠናዉ ይጠናቀቃል፡፡

በተጨማሪም እንደ ማሰልጠኛ ስልቶች *የቡድን ስራዎች፣ መጠያየቆች፣ ኬዞች፣* እና ሌሎች ዘዴዎች እንደአስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ ልዉሉ ይችላሉ፡፡

### *ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች*

ስልጠናዉን በተሳካ ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችሉና ተፈላጊ ከሆኑ ቁሳቁሶች መካካል የሚከተሉት ይካታታሉ፡-

- ✓ ኤል ሲዲ ፕሮጀክተር ከአስፈላጊ የሃይል ምንጭና ተያያዥ ግብዓቶች (ድስፕሌይ ማድረጊያ ቦታ ወይም ዕቃ እና ሌሎች)
- ✓ ፊሊፕ ቻርቶች
- ✓ ማርከሮች በተለያዩ ቀለማትና መጠኖች የተሳታፊዉን ቁጥር ባገናዘበ መልኩ
- ✓ ስትከር ወረቀቶች ለተለያዩ ስራዎች የሚዉሉ በተለያዩ ቀለማት
- ✓ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር
- ✓ ለስልጠናዉ አመቺ የሆነና በቂ መቀመጫዎች ያሉት ማሰልጠኛ አዳራሽ/ክፍል እና ሌሎችም እንደአስፈላጊነቱ የሚጨመሩ ይሆናሉ፡፡

### *የስልጠናው ተተኳሪዎች*

ስልጠናዉ በትምህርት መስኩ በየደረጃዉ (ከፌዴራል እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ትምህርት ቤት እንዲሁም የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ድረስ) ያሉትን የስራ ሃላፊዎችንና ሰራተኞችን የሚመለከት ሆኖ የመንግስት፣ የህዝብና የግል ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ተቋማት ሃላፊዎችንና ሰራተኞችንም ያካትታል፡፡

## የስልጠናው ግምገማ

በዚህ ስልጠና ሂደትና በሞጁሉ ማጠናቀቂያ እያንዳንዱ ተሳታፊ በንቃት እንዲከታተል አመቻቺው አስፈላጊዉን የማመቻቸት ስራ ይሰራል፡፡ በዚሁ መሰረት ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ተግባራት የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፡-

- ሰልጣኞች ስልጠናው ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ 100 ፐርሰንት በስልጠና ክፍሉ ተገኝቶ በንቃት የመከታተልና የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው፤
- የተማሩትን ትምህርት አንድምታ በጽሁፍና በቃል በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያቀርባሉ፤
- ሙስና ወንደጀል መሆኑንና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ተንትነው እንዲያስረዱ የሚሰጣቸዉን ተግባራት ይፈጽማሉ፤
- የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ ያደረጉ ምክንያቶችን በተጨባጭ በመመርመር በጽሁፍና በቃል ያስረዳሉ፤
- በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉትን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዴት አስቀድሞ እንደሚከላከሉ/ እንደሚያስወግዱ በግልና በጋራ ስልት ቀይሰው እንዲያሳዩ ይደረጋል፤
- በየመሥሪያ ቤቶቻቸው ወይም በሌሎች ቦታዎች ያስተዋሉትን እውነተኛ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን አስመልክቶ ያላቸዉን ሃሳብ በኬዝ መልክ በማቅረብ በክፍል ውስጥ እንዲተርኩ ይደረጋል፤
- በሞጁሉ መጨረሻ የቀረቡትን የራስ ብቃት መገምገሚያ ቼክ-ሊስቶችን በመስራትና የግንዛቤ ደረጃቸዉን በመለየት ክፍተቶች በታዩት ቦታዎች ላይ ተጨማሪ የማንበብና የመጠየቅ ስራዎችን በንቃት በመፈጸም ብቃታቸዉን እንዲያጎለብቱ ይደረጋል፡፡
- ከዚህ ስልጠና ያገኙትን ዕዉቀት፣ ክህሎትና አመለካት እንዴት በሥራ ላይ ማዋል እንደሚችሉ ስልት ቀይስው እንዲያስረዱ ይደረጋል፤
- የዚህን ስልጠና ዓላማ መሳካት፣ ይዘትና የስልጠና ሂደትን በመገምገም ሃሳብ ይሰጣሉ፤ በመጨረሻም ቀጣይ ስለሚያስፈልጋቸው የስልጠና ይዘት ዝርዝር ያቀርባሉ፡፡

በተጨማሪም የፌዴራል ስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በሚያቀርባቸዉ ተጨማሪ የብቃት መገምገሚያ ስልቶች (የጽሁፍ ፈተናዎች፣ መጠይቆች፣ የስራ ላይ ተጨባጭ ግምገማዎች እና ሌሎች ተያያዥ ስልቶች) በመጠቀም የብቃት ግምገማ በማድረግ ሰልጣኞች ሰርቲፊኬት የሚያገኙበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

## ምዕራፍ አንድ፡ የሙስና ወንጀሎችና አይነቶች (2 ሰዓታት)

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው። ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል። የሙስና ወንጀል ለግላዊ ጥቅም ሲባል፣ ኢ-ሞራላዊና ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ በሐሰተኛ ሰነድ/የአሰራር ሂደት ወይም በማጭበርበር እንዲሁም በግለሰብ ወይም በተቋም ሥልጣን በመመካት የሚፈጸም ወንጀል ነው። ይህ ዓይነቱ ወንጀል በትምርት ሥርዓቱም አለ ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም በዚህ የመጀመሪያዉ ምዕራፍ የሙስና ምንነትና አይነቶቹ፣ የትምህርት ጽንሰ ሀሳብና ግቦቹ፣ ትምህርት ለፀረ-ሙስና መሳርያነት ያለው ጠቀሜታና በትምህርት ሥርዓቱ የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያትና መገለጫዎች ተዳስሰዉበታል።

### የምዕራፉ ዓላማዎች/የሚጠበቁ የባህሪ ገጽታዎች

ሰልጣኞች የምዕራፉን ይዘቶች በአግባቡ ተከታትለዉ ሲያጠናቅቁ፡-

- የሙስና ጽንሰ-ሃሳብን አስመልክቶ የተረዱትን ሃሳብ ይገልጻሉ።
- የትምህርት ጽንሰ-ሃሳብ እና ግቦች በመዘርዘር ማብራሪያ ይሰጣሉ።
- ትምህርት ለጸረ-ሙስና መሳሪያነት ያለዉን ሚና ይተነትናሉ።
- የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ።
- በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉቱን የሙስና ወንጀል አይነቶችን ይለያሉ።
- የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን በመረዳት ለሌሎች ግንዛቤ የመፍጠር ስራን በብቃት ይሰራሉ።

### *1.1. የሙስና ምንነትና አይነቶቹ*

በዚህ የምዕራፉ የመጀመሪያዉ ክፍል በሙስና ምንነትና አይነቶቹ ዙሪያ የተለያዩ ጉዳዮችን በማዉሳትና ዉይይቶችን በማካሄድ ሰልጣኞች ይዘቱን እንዲረዱት ጥረት ይደረጋል።

**መልመጃ 1.1 (10 ደቂቃዎች)**

ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች ለ3 ደቂቃዎች በየግላችሁ ከሞከራችሁት በኂላ በአመቻቹ በሚሰጠዉ እደል መሰረት የተወሰናችሁ ለተቀሩት ተሳታፊዎች ሃሳባችሁን አጋሩ።

ሀ. ሙስና ምንድነው?

ለ. ሙስና ሌላ የሚጠራበት ስያሜ በማህበረሰቡ ውስጥ ይኖር ይሆን? ዘርዝሩ

ሐ. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ፡፡

መ. ሙስና ወንጀል ነው? ለምን?

ሠ. ወንጀል መሆኑ መገለጫው ምንደነው?

**ማስታወሻ**

ሙስና የሚለዉ ቃል የሚያስተላልፈዉን ትርጉም በተገቢዉ ደረጃ ተገንዘቦ አንድ ሊያስማማ የሚችል ሁሉን አቀፍ የሕግ ትርጉም ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International) የተባለ ተቋም “ሙስና” የሚለዉን ቃል ሲፈታዉ እንዲህ ይላል፡፡ corruption is Defined as “Misuse Of Entrusted Power For Private Gain.” በዚህ ትርጉም መሰረት “ሙስና ማለት በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል” ነዉ የሚል ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ በመገልገል ጉዳይን አላግባብ ማጓተት ወይም አላግባብ ፈቃድ በመስጠትና በማጽደቅ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል በሙስና ወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይገልጻል፡፡ ከሙስና ወንጀል አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 881/2007) የተወሰደዉ ሃሳብ ደግሞ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡ ሙስና ማለት፡-

> ማንኛውም የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ሀላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደረግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደረግ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የሕዝብ አደራ ያላግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ ወይም ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ ለመንግስት ወይም ለሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ፣ ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ ወይም በአግባቡ ለተፈፀመ ወይም ለወደፊቱ የሚፈጸም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሥራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ከማንኛውም የመንግስት

ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ ይሆናል።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የሚከተሉት አምስት ነጥቦች ይስተዋላሉ፤ እነዚህ በትምህርት ዘርፍ በምን ሁኔታ ሊገለጹ ይችላሉ?

1) ሀላፊ ሆኖ የማይገባውን ገንዘብ ከኮንትራክተሩ ለማግኘት ሲል የመማርያ ክፍሎች ግንባታ በርካሽ የግንባታ ግብዓት እንዲሰራ የፈቀደና ኮንትራክተሩም ከዉል ውጪ በርካሽ ግብዓት ክፍሎችን በመሥራት ያለአግባብ ያተረፈ፤
2) አንድ ባለሙያ በብቃቱ የመቀጠር መብት እያለው እንዳይቀጠር በማድረግ፣ ጥቅም የሰጠውን ሰው በመጥቀም ባለመብትን የጎዳ፤
3) ጥቅም ለመቀበል ሲል ደረጃውን ያልጠበቀ ቁሳቁስ (ለምሳሌ ብዙ ጥቅም የማይሰጥ ኮምፒውተር) ግዢ የፈጸመ፣ ወይም በጨረታ መግዛት ሲገባው ያለጨረታ በውድ ዋጋ የትምህርት ግብዓቶች እንዲገዛ ያደረገ፤
4) ጥቅም ለማግኘት ሲል የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የሰጠ እና
5) ጥቅም ለማግኘት ሲል በእጁ የገባውን ፈተና ለተፈታኞች ለመስጠት ቃል የገባ ወይም የሰጠ ማለት ይቻላል።

ሙስናን የበለጠ ለመረዳት ደግሞ አይነቶቹን ማየት ጠቃሚ ነዉ። ሙስና ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ። ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grandcorruption) ስርዓታዊ (systemic corruption) እና ፖለቲካዊ (political corruption) ሙስና ተብሎ ይከፈላል።

### 1. ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው። ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው። በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው። መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ

ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

## 2. ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሻሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 "ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተተ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል፡፡

## 3. ስርዓታዊ ሙስና (systemic corruption)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ስርዓታዊ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡ ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic corruption) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

4. **ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)**

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

**ኬዝ 1.1. በፈተና ላይ የተሰራ የሙስና ወንጀል**

*በአንድ ክልል የሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለትምርት ቤቱ ተማሪዎች በቂ የመማርያ ቁሳቁሶችን ሳያሟላ፣ መምህራን በተከታታይ የሙያ ዕድገት ስልጠና ሣይሰጥ፣ ለተማሪዎች ክለሳዎች እንዲኖሩ ሳያደርግ እና ተማሪዎችን በየጊዜው ሳያነቃቃ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ጊዜው ደረሰ፤ በጊዜ መቃረብ የተደነጋጠው ርእሰ መምህር ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር ሰፊ ምክክር ካደረገ በኋላ፣ ተማሪዎች የገንዘብ መዋጮ እንዲያደርጉና ከወረዳ፣ ከዞንና ከክልልትምህርት ቢሮ የሚመጡ ፈታኞችን በመቅረብ በገንዘብ ሀይል ፈተናው እንዲወጣና መምህራን ሰርተው መልሱ ለተማሪዎች በሙሉ እንዲታደል ተደረገ፤ በመጨረሻም 250 የሚሆኑ ተማሪዎች በሙሉ ከዚያ ትምህርት ቤት ከፍ ባለ ውጤት ማለፋቸውን የፈተናዎች ኤጀንሲ አረጋገጠ፤ ሆኖም በነበረው የትምህርት ቤት ዝቅተኛ አቋም፣ በግብዓት ማነስና በተማሪዎች በቂ ዝግጁት አለመኖሩ ተጠንቶ ከተረጋገጠ በኋላ ፈተናው ተሰረዘ፤ ከወራት በኋላ ተቀራራቢ ፈተና ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች በጥብቅ ቁጥጥር ተሰጠ፤ ሆኖም ከ250 ተማሪዎች ከ50 ፐርሰንት በላይ አምጥተው በዝቅተኛ ውጤት ለማለፍ የቻሉት በቁጥር አሥር ተማሪዎች ብቻ ሆነው ተገኙ፡፡ ኩረጃ በአገር ላይ የተሰራ ወንጀል ነው፡፡ ከዚሁ ጋር የሚቀራረብ ምሳሌ፡- በ2013 ዓ.ም. 12ኛ ክፍል ከተፈተኑ ተማሪዎች መካከል 50 ፐርሰንትና ከዚያ በላይ ያመጡት ተማሪዎች ብዛት በፐርሰንት ሲለካ 50.5 ነበር፤ በተከታታይ ሶስት*

*ዓመታት ግን ፈተናው በዩኒቨርሲቲዎች ግቢ ጥብቅ ቁጥጥር ተደርጎበት ሲፈተኑ፣ በ2014 3.3፤ በ2015 3.2፤ እንዲሁም በ2016 5.4 ፐርሰንት የሚሆኑት 50 ፐርሰንትና ከዚያ በላይ ማስመዝገባቸው ሲታወስ፣ ይህ ውጤት በ2013 ዓ.ም. እና ከዚያ በፊት ኩረጃ በኢትዮጵ በስፋት መኖሩን በግልጽ ያመላከተ ሆኖ ተገኝቷል።* እናንተስ በዚህ ጉዳይ ምን አስተያየት አላችሁ? ወደፊትስ ኩረጃን ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት ምን ማድረግ አለብን?

## *1.2. የትምህርት ጽንሰ ሀሳብና ግቦቹ*

በሁለተኛዉ የምዕራፉ ክፍል የትምህርት ጽንሰ-ሃሳብና ግቦች ዙሪያ ትኩረት ተደርጓል። ሃሳቦቹን የበለጠ ለመረዳት የቀረቡትን መልመጃዎች በመስራትና ተያይዘዉ የተሰጡትን ማስታወሻዎች በአግባቡ በማንበብ ግንዛቤአችሁን ማዳበር ትችላላችሁ።

***መልመጃ* 1.2 (15 *ደቂቃዎች*)**

ከዚህ በታች ያለውን መልመጃ ለመሥራት በመልመጃ 1.1. የተጠቀሰውን መመርያ ተከተሉ።

ሀ. ትምህርት ምንድነው?

ለ. ትምህርት ለምን?

ሐ. ትምህርት ሙስናን ለመከላከል ያለው ሚና ምንድነው?

**ማስታወሻ**

ትምህርት የአንድ አገር እድገት የመሰረት ድንጋይ ነው። ከሙስና የፀዳ ትምህርት ዓለምንም ለመቀየር አስተማማኝ መሳርያ ነው። ትምህርት አዕምሮን የማልማት ሂደት ሲሆን፣ በዚህም እውቀትንና ክህሎትን ያስጨብጣ፤ ትምህርት አመለካትን፣ ስነ-ምግባርን፣ እሴቶችንና የሞራል ልዕልናን በሰው አእምሮ ውስጥ የሚያበለጽግ መሳርያ ነው። ትምህርት የህጻናትን/ወጣቶችን አዕምሮ በማልማት ዕውቀት፣ ችሎታዎች፣ አመለካከቶችና አዎንታዊ ባህርያት እንዲዳብሩ የሚያደርግ መሳርያ ነው። ይህም ማለት ትምህርት እውቀትና ባህል በመደበኛም ሆነ በኢ-መደበኛ የትምህርት አቀራብ ውስጥ እንዲተላለፍና እንዲሻሻል የሚያደርግ ሥርዓት ነው። ትምህርት ዋናው ትኩረቱ የዜጎች አዕምሯዊ፣ አካላዊ ብቃት፣ ስነ-ልቡናዊ እና ማህበራዊ እድገት እንዲኖር ማድረግ ነው። ዛሬ በዓለማችን የምንመለከታቸዉ የሳይንስና የቴክኖሎጂ እድገቶች በሙሉ በትምህርት መሳሪያነት የተከሰቱ ናቸው። መሰረታዊና ማህበራዊ ለውጦችም የሚመጡት በትምህርት ነው። በሁሉም ዘርፍ ዘላቂ እድገት የሚመጣዉም ጥራት ባለው ትምህርት ብቻ ነው። ትምህርት በራሱ አንድ ቦታ የሚቆም ሳይሆን በሕይወት

ዘመን ሁሉ አከባቢያዊ ችግሮችን ለመፍታት የምንገበየው ነው። ትምህርት የአከባቢን፣ የማህበረሰብን፣ የባህልንና የምጣኔ ሀብትን እድገት ይወስናል።

የትምህርት ዘርፉ የማይነካው ጉዳይ የለም፤ ሙያዊነትን፣ እቅድን፣ ቴክኖሎጂን፣ ሕግን፣ ሕክምናን፣ የገንዘብ አስተዳደርን፣ ፖሊሲን፣ ሥርዓተ-ትምህርትን፣ የትምህርት አሰጣጥንና ምዘናንም ይመለከታል። የእነዚህ እድገት ጥራት ያለውና አዎንታዊ አቅጣጫን የሚከተል ከሆነ በሁሉም ዘርፍ ዘላቂ እድገትን ማምጣት እንችላለን። ነገር ግን የትምህርት ዘርፉ በሙስና ከተዘፈቀ የትምህርት ጥራቱ እንዲሁም ጊዜያዊም ሆነ ዘላቂ እድገቶች ሊኖሩ አይችሉም። ምክንያቱም ሙስና የትምህርትን ተደራሽነትና ጥራት ያደናቅፋል። ዘላቂ እድገት ካለ አገር ተረካቢው ትውልድ ያለምንም ስጋት ፍላጎቱን ያሟላል፤ ለእሱ የደረሰውን እድገትም ያስቀጥላል። ይህ እንዲሆን ደግሞ የትምህርት ዘርፉ ከማንኛውም ሙስና የጸዳ መሆን አለበት። ይህ በእርግጠኝነት ከተፈጸመ መጪውን ትውልድና አገር ከአደጋ እንጠብቃለን። ጉዳዩን የበለጠ ለመገንዘብ ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በማንበብ ተከትሎ የተነሱትን ጥያቄዎች መልሱ።

### ኬዝ 1.2. የትምህርት ጥራት በደቡብ ኮርያ

*ደቡብ ኮርያ እምብዛም የተፈጥሮ ሀብት የላትም። በዚህ ላይ እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ የነበረው ጦርነት ኮርያን ከድህነት ወለል በታች አውርዷት ነበር። ሆኖም ኮርያ ከሙስና የፀዳ ጥራት ያለው ትምህርት ለሕዝቧ መመገብ በመቻልዋ እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ በእድገትዋ ተዓምር ሰራች፤ ተዓምሩ ደግሞ በትምህርት ጥራት የመጣ ነበር። በእ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ ደቡብ ኮርያ ከኢስያ በኢኮኖሚ ከበለጸጉ አራት አገሮች ውስጥ አንዷ ለመሆን በቃች። ዛሬስ? ዛሬማ ከፍተኛ የነፍስወከፍ ገቢ ካላቸው የዓለም አገራት አንዷ ሆናለች። የአገሪቱ አማካኝ ወርሃዊ ገቢ 2800 ዶላር ነው። የአንድ የኢትዮጵያ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌር ወርሃዊ ገቢ ደግሞ 176 ዶላር ነው። ልዩነቱ የሰማይና የምድር ርቀት ያህል ነው። የእኛ ወርሃዊ ገቢ ከትምህርታችን መዉደቅ ጋር አብሮ የወደቀ ነው። የኮርያኖቹ ደግሞ ከፍተኛ ጥራት ባለው ትምህርታቸው ምክንያት ተመንጥቋል ማለት ይቻላል።* ስለዚህ ትምህርት የሕይወትን መስመር ለማሳመር ወሳኝ መሆኑን ማየት ይቻላል። ደቡብ ኮርያ ከደረሰችብት ለመድረስ ከእኛስ ምን ይጠበቃል? የትምህርት ጥራት መዉደቅ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት ጋር የሚያገናኘዉ ነገር አለ ወይ?

## 1.3. ትምህርት ለፀረ-ሙስና መሳሪያነት

በዚህ ክፍል ጥራት ያለዉ ትምህርት ለጸረ-ሙስና መሳሪያነት እንዴት እንደሚያገለግል ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በመስራትና ማስታወሻዎችን በአግባቡ መማንበብ ግንዛቤአችሁን እንዲታዳብሩ ትመከራላችሁ፡፡

**መልመጃ 1.3. (15 ደቂቃዎች)**

ከዚህ በታች ያለውን መልመጃ ለመሥራት መጀመሪያ በየግላችሁ ቀጥሎ ደግሞ በአራት በአራት በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ምሁሩ የአገር ጠላት እንደሆነ ተደርጎ ሲነገር እንሰማለን፤ እንዴት?

ለ. የተማረ ሰው ሥነምግባር እየራቀው ነው መባል ከጀመረ ቆይቷል? ለምን ተባለ?

ሐ. በየቢሮው ያሉት አገልግሎት ሰጪዎች የተማሩ ናቸው፤ ሕዝብ በእነሱ ይማረራል፤ ለምን?

መ. ግዢና ግንባታ ዋናው የሙስና ጎሬ ነው ይባላል፣ ለምን ተባለ?

ሠ. መምህራን በሙስና ይሳተፋሉ? በምን ሁኔታዎች?

**ማስታወሻ**

ጥራት ያለው ትምህርት በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት አዕምሮን ያለማል፡፡ የለማ አእምሮ ደግሞ በሞራልና በሥነ-ምግባር የተገነባ ነው፡፡ የተገነባ አእምሮ ደግሞ አገርን ይገነባል እንጂ፣ አገርን አይሰርቅም፡፡ በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ብቁ የሆነ ዜጋ ስለወደፊት የሚያስብና የሚተነብይ፤ ለአከባቢው ደህንነት የሚጠነቀቅ፤ የአገርን ሀብት ቆጥቦ ለሁሉም በፍትሃዊነት እንዲዳረስ የሚያደርግና እጁ ፈጽሞ ከሙስና የፀዳ ነው፡፡ ይህ ግን ያለዕውቀት፣ ክህሎትና አዎንታዊ አመለካከት ማናኛውንም ዓይነት ድግሪ ያላቸውን ሰዎች አያካትትም፡፡ ድግሪ መያዝ ብቻ በራሱ ምሁር አያሰኝምና፡፡ ድግሪ ያላቸው ነገር ግን ጥራት በሌለው ሂደት ያለፉ ሰዎች በኢትዮጵ ውስጥ ያለሀፍረት አቅዶ ጉቦ መቀበልና ማጭበርበር በትምህርቱ ዘርፍ የተለመደ ሆኗል፡፡ ትምህርት ያልቀየረው አመለካከትና ባህሪ ከመስረቅና ከማጭበርበር ሊቆጠብ አይችልም፡፡ በሁሉም ደረጃ ያሉ የትምህርት ሃላፊዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ከሕግ ውጪ ለራሳቸው ወይም ለቤተሰቦቻቸው ክፍያን ወይም ውለታን ይቀበላሉ፡፡ ከእውቀት፣ ከክህሎትና አዎንታዊ አመለካከት በብቃት ማነስ ምክንያት አርኪ

አገልግሎት አለመስጠትም ሙስና እና የሙስና መሰረት ነው። በተለይም አዎንታዊ አመለካከት ማምጣት በጣም ወሳኝ ነው። አመለካከትን አስመልክቶ ዶ/ር ዓለማየሁ ትክለማርያምና አቶ ጌታቸው ታደሰ (2016፤ ገጽ 148) አመለካከትን እንዲህ ገልፀው ነበር፦

> አመለካከት የሰው አዕምሮ ዕይታ እንደመሆኑ መጠን ለብዙ ጉዳዮችና እድገቶች መሰረት ነው፤ የሰው ልጅ ለሕይወት፣ ለዓለምና ለተለያዩ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊና ባህላዊ ጉዳዮች የሚሰጠው ዋጋ፣ ማንኛውንም ጉዳይ የሚያስብበት፣ አስቦ የሚያምንበት፣ ያመነውን በመግለጽ የሚተገብርበት፣ የአዕምሮ መነጽርና የድርጊት መርህ ነው፤ ሰዎችን፣ ክስተቶችንና ስሜቶችን መሰረት አድርገን የምንፈጽመው ድርጊት ስለጉዳዩ ከሚኖረን አመለካከትና በውስጣችን ከሚያድገው መርህ የሚመነጭ ነው። አመለካከት ከዘርፈ ብዙ የሰው ልጅ ተሞክሮዎች የሚዳብር እምነት ነው። ለተለያዩ ነገሮች የሚኖረን ስብስብ ደግሞ ለጉዳዩ የሚኖርንና በውስጣችን የሚሰርውን እሴት በማጠናከር ለድርጊት ሊያዘጋጀን ይችላል።

ይህ የሚመላክተን አመለካከት ከተቃና ዕውቀትም ይቃናል፤ በዚህም አዎንታዊ አመለካከት ከዳበረ ሙስና የመኖር ሁኔታው ይከስማል ማለት ነው።ጉዳዩን የበለጠ ለመገንዘብ ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በአግባቡ በማንበብ ተያይዞ የቀረበዉን ጥያቄ መልሱ።

**ኬዝ 1.3. በትምህርት የተገሩ የእስካንዲኔቭያን አገሮች ከሙስና የፀዱ ናቸው።**

የእስካንዲኔቭያን አገሮች የሚባሉት ዴንማርክ፣ ፊንላንድ፣ አይስላንድ፤ ኖርዌይ እና ስዊድን ናቸው። አይስላንድ ብዙ ባትታወቅም የተቀሩት ግን ከሙስና በመፅዳት ሁሌም ከመጀመሪያው ከ1-5 ያለውን ቦታ ይይዛሉ። ይህን ደረጃቸውን ስተው አያዉቁም። አንዳንዴ ስዊድን በ6ኛ ደረጃ ከመገኘትዋ በስተቀር። ለዚህ ምክንያት ደግሞ የትምህርት ሥርዓታቸው በዜጎች ላይ ያመጣው የሥነ-ምግባር ልዕቀት ነው። እነዚሁ አገሮች ደስታ ያለባቸው አገሮችም ተብለው ይጠራሉ። ከእነዚህ አገሮች ምን እንማራለን? ከሙስና መጽዳት ይቻለን ይሆን?

## *1.4. የሙስና ወንጀሎች ምንነት፣ ባህሪያትና አይነቶቹ*

በዚህ ክፍል የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎች በስፋት የሚዳሰሱበት ሲሆን ከነዚያም መካከል በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉትን ሰልጣኞች ከወድሁ እየለዩ እንዲሄዱ ጥረቶች ደረጋሉ።

መልመጃ 1.2.1. (8 ደቂቃዎች)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ቡድን በመሆን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. "ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት" በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

2. በትምህርት ዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡

3. "ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ" ከሙስና ወንጀል ጋር እንዴት እንደሚያያዝ ምሳሌዎችን በማቅረብ አስረዱ፡፡

4. የሚታዉቋቸዉን የሙስና ልዩ ባህሪትና አይነቶች ዘርዝሩ?

**ማስታወሻ**

የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) መሰረት ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፦

> የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣ በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣ በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ ሚስጥር

ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ “... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል...” በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች፣ በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የሙስና ወንጀሎችን የበለጠ ለመረዳት የወንጀሎቹን ልዩ ባህሪያት በሚገባ መረዳት ጠቃሚ ነዉ፡፡ ምክንያቱም የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ የሆነ ወንጀል ነዉ፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር፣ ለማጋለጥ፣ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ፡፡ የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፤

### 1. የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ፡፡ የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል፡፡

### 2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል ፡፡ ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል፡፡ ከዚህ

ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል፡፡ ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል፡፡

### 3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው፡፡ ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### 4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራሉ፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

“የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም” የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን

ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

5. **ድንበር ተሻጋሪነቱ**

ሰዎች የሙስና ወንጀል የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመንዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኑን ሊጊሊግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

በመቀጠል ደግሞ የሙስና ወንጀል አይነቶችን በዝርዝር ማየት ጠቃሚ ስለሆነ በአገሪቱ ያሉት የወንጀል ህጎች እንዴት እንደሚመለከቷቸዉ እና የትኞቹ ወንጀሎች በሙስ ወንጀልነት እንደተለዩ ማየት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣ በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡ የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1. **በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)**፡- ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር (በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው

ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

2. **ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)፡-** ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

3. **የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)፡-** ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

4. **አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)፡-** ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ፣ ወይም አጣሪ፣ ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት)፣ ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

5. **የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)፡-** ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣ የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤ በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ

የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

6. **አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)፡-** ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

7. **በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)፡-** የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንቀሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

8. **በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)፡-** ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣ የንግድ ስምምነት፣ የስራ ጨረታ፣ የዕቃ ማቅረብ ዉል፣ ወይም ሌላ ጥቅም ወይም በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን፣ ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

9. **በህገ-ወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)፡-** ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ሊከፈል

የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረከብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

10. **ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት** (**አንቀፅ** 18)፡- *ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ፣ ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ያጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡*

11. **ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት** (**አንቀፅ** 19)፡- *ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡ ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡ በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡*

12. **ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ** (**አንቀፅ** 20)፡- *ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡*

13. **ምንጬ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ** (**አንቀፅ** 21)፡- *ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ያለዉ*

ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

14. ***የሥራ ሚስጥርን መግለፅ*** **(አንቀፅ 22)፡-** አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ፣ ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኂላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

15. ***መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል*** **(አንቀፅ 23)፡-** ማንኛዉም ሰው የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፡፡ አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤ በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

16. ***መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ*** **(አንቀፅ 24)፡-** ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

17. ***ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት* (*አንቀፅ* 26)፡-** *ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡ በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡*

18. ***ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት* (*አንቀፅ* 25)፡-** *ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡*

19. ***ማቀባበል* (*አንቀፅ* 27)፡-** *ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለዉ ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣ ያገናኘ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡*

20. ***በሌለው ሥልጣን መጠቀም* (*አንቀፅ* 28)፡-** *ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡*

21. ***በግል ተሰሚነት መነገድ* (*አንቀፅ* 29)፡-** *ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል*

የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል። ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል።

22. **በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)፡-** ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

23. **ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)፡-** ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤ መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም።

24. **ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)፡-** ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ።

25. **በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)፡-** በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

**መልመጃ 1.2.2. (7 ደቂቃዎች)**

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ።**

1. ከላይ ከተራ ቁጥር 1-25 ከተዘረዘሩት የሙስና ወንጀሎች ዉስጥ የትኞቹ በትምህርት መስኩ እንደሚስተዋሉ በመወያየት ለመለየት ጥረት አድርጉ?

2. ከለያችሁቸዉ መካከል የትኞቹ የትምህርትቱን ጥራት ለማረጋገጥ አዳጋች እንዲሆን ያደርጋሉ? ለምን?

3. በትምህርት መስኩ የተደረገ የሙስና ተጋላጭነት የዳሰሳ ጥናት እንዳመላከተዉ ከሆነ ወደ 19 አይነት የሙስና ወንጀሎች እንደሚከሰቱ ያብራራልና በሃሳቡ ትስማማላችሁ? ለምን?

4. በየትኞቹ እርከኖች ላይስ ይስተዋላል?

**ማስታወሻ**

በኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና በትምህርቱ ዘርፍ ዘላቂ እድገት እንዳይመጣ ዋነኛው ተግዳሮት ነው። ሙስና ካለ የት/ቤቶች አቅርቦቶች ትኩረት ያጣሉ። ሙስና የሰዎችን እኩልነትና ፍትሃዊነት ያዛባል፤ ድህነትን ያባብሳል፤ በተገቢው እቅድ እንዳንመራ ያደርጋል፤ ሀብት ለእድገት እንዳይውል ያደርጋል። ሙስና የትምህርት ተቋማትን ዴሞክራሲ ያቀጭጫል፤ በትምህርት ተቋማት እሴቶች መገንባት ሲገባቸው፣ በሙስና እሴቶች ይሸረሸራሉ፤ ተማሪዎች በአግባቡ ተምረው ማደግ ሲገባቸው በኩረጃ ፈተናዎችን በማለፍ ያለእውቀት ከትምህርት ደረጃዎች ጫፍ ይደርሳሉ፤ የሰዎች በእውቀትና በዳበረ ክህሎት አገልግሎት ሰጥቶ መበልጸግ አደጋ ውስጥ ይሆናል፤ የትምህርት ሴክተሩ መሥርያ ቤቶች አሰራር ሥርዓተ-አልበኝነት የሰፈነበት ይሆናል። ሙስና ካለ ፈጠራ አይኖርም። በዚህ ምክንያት ዜጎች በውጪ ቁሳቁስና አገልግሎቶች ላይ ጥገኛ እንሆናለን፤ በሙስና ምክንያት የመቀጠር እድል የሌለው ዜጋ አገሩን ጥሎ ይሰደዳል፤ ሀብትን ለሁሉም እኩል ተደራሽ አይሆንም፤ ሰው ሀብቱን አፍስሶ የልማት ሥራ መሥራት ቢፈልግ በሙስና ምክንያት ከፍተኛ ወጪ ስለሚመጣበት ይከስርና ሥራዉን ያቆማል። ሙስናን ባልተከላከለ የትምህርት ዘርፍና መንግስት ላይ ሕዝብ ዕምነት ያጣል። ለምሳሌ፦ ለትምህርት ሥራ የተመደን ገንዘብ ተገቢ ላልሆነ ሥራ ወይም ለግል ጉዳይ ማዋል፤ መምህራን ተማሪን ፈተና ለማሳለፍ በስጦታ አሳቦ ገንዘብ ወይም ቁስ መቀበል፤ በተቀራኒ ፆታ ወሲባዊ ጥቃት መፈጸም፤ የተማሪ ምደባና ቅበላ ላይ አድልኦ መፈጸም፤ መምህር በግል የጻፈውን መጽኃፍ ተማሪ ያለፍላጎቱ እንዲገዛ ማግባባት ወይም ማስገደድ፤

የመማር ማስተማሩንም ሆነ የቢሮ ተግባራትን ወደ ጎን መተው እና ቸል ማለት፤ ሀሰተኛ መረጃ ለተመራቂ እንዲሰጥ ማድረግ እና የመሳሰሉት በሙሉ በትምህርት ዘርፉ ውስጥ የሚስተዋሉ የሙስና መገለጫዎች ናቸው፡፡

ሙስና በሁሉም የትምህርት እርከኖች ማለትም በትምህርት ሚኒስቴር፣ በክልል፣ በዞን/ክፍለ ከተማ፣ በወረዳና በት/ቤቶች ሊፈጸም ይችላል፡፡ ከትምህት ቤት በላይ ያሉት የትምህርት አስተዳደር እርከኖች በጀት በመመደብ ሂደት ውስጥ፣ በቂ የትምህርት መሳርያዎች ግብዓት ከማከፋፈል አንጻር፣ በግዢ፣ መጻሕፍትን በማሳተምና በማከፋፈል ሂደት፣ በግንባታ ሂደት፣ በዝውውር፣ በቅጥርና በእድገት ሙስና ሊፈጸም ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሙስና ደግሞ ለትምህርት ሥርዓቱ ከባድ አደጋ ነው፡፡ የትምህርትን ተደራሽነት ከመጉዳቱም በላይ ጥራቱንም በብርቱ ይጎዳል፡፡

በትምህርት ቤት ደረጃም ልጅን ትምህርት ቤት ለማስገባት፤ ጥሩ ማርክ ልጁ እንዲያገኝ ለማድረግ ከወላጆች በገንዘብ ወይም በዓይነት በመቀበል ሙስና ሊፈጸም ይችላል፡፡ የተሰጠውን የሀላፊነት ቦታ በመጠቀም አስተዳደር ወይም መምህር ብሄርን፣ ፆታንና ሀብትን መሰረት በማድረግ በማርክ አሰጣጥ ላይ መድሎ በመፍጠር ሙስና ሊካሄድ ይችላል፡፡ የሌሎችን ሰዎች ሥራ የራስ አድርጎ ማቅረብ፤ ይህም የትምህርት የጽሁፍ ሥራዎች፣ የምረቃ ጸሁፎች፣ ቴስቶችን መግዛት፣ ማርክ ማስቀየር፣ ሐሰተና ሰነድ (ፎረጀሪ) ማሰራት፣ የመመረቂያ ጽሁፎችን በሌሎች ሰዎች ከፍሎ ማሰራት፣ በፈተና ጊዜ መኮረጅ፣ ድግሪና ድፕሎማ መግዛት…ወዘተ ናቸው፡፡ ይሄን ጉዳይ የበለጠ ለመገንዘብ ቀትሎ የቀረበዉን ኬዝ መመልከት ጠቃሚ ነዉ፡፡

**ኬዝ 1.4. የድግሪ ገበያ በኢትዮጵያ**

*በመገናኛ ብዙሃን፣ ከፖለቲከኞችና ከከፍተኛ ባለስልጣናች እንደምንሰማው ከመጀመርያ ድግሪ ጀምሮ እስከ ፒኤችዲ ድግሪዎች ድረስ በገንዘብ ገዝተው በመንግስት መሥርያ ቤቶች የሚቀጠሩ በርካታዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ሰዎች ድግሪ ለምን ለመግዛት ተነሳሱ? ብለን ብንጠይቅ፣ በኩረጃ ክፍል የቆጠረውና የምረቃ ወረቀቱን በሰው ከፍሎ ያሰራዉ በእግር ትምህርት ቤት ከመመላለስ በስተቀር ከእኛ በምን ይሻላል በሚል ንቀት ነው ወደ ድግሪ ሸመታ የገቡት፡፡ አጠገቡ ያለውም ያዉ ከሆነ ማን ይፈታተናቸዋል? ማን እውቀታቸውን ይፈትሸ? የአዲስ አበባ መስተዳደር በ2016 ለሰራተኞች የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ሲሰጥ ብዙዎች መሬት የጠበበችባቸው ለዚህም ይሆን? መምህራን የሚያስተምሩትን ተፈትነው ያለፉት ጥቂቶች እንደነበሩ የትምህርት ሚኒስትሩ ነግረውን ነበር፡፡ እንግዲህ በእግራቸው*

*ትምህርት ቤት ተመላልሰው ከክፍል ወደ ክፍልም በነጻ በመዝዛቸው ምክንያት በትምህርት ጥራት ውስጥ ባላለፉና ይባስ ብሎ ድግሪ በገዙ ሙሰኞች ሕዝባችን መከራዉን ይገፋል፤ ይተዳደራል፣ ይታከማል፣ ይጎዝል፣ ምግቦችንና ሌሎች የተበላሹ ቁሳቁሶችን ይገዛል፣ ይዳኛል፣ ቤት ያሰራል፣ መንገድ ያስገነባል፣…ወዘተ. በዚህ ሁሉ ኪሳራና ድህነት ብቻ ነው ሲተርፈን የኖርነው፤ አሁንም እየኖርን ያለነው፡፡* ድግሪ ይገዛል፤ ሻጭም አለው፤ ይህ በአገር እድገት ምን ያስከትላል? ጥራት ያለዉ ትምህርት ለዜጎች በማዳረስ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች የጸዳች አገር የመገንባት ስራዉን አስቸጋሪ አያደርገዉም ወይ?

## *የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ*

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ ስለሆነም ሙስና ፈርጀ ብዙ የሆነ ጽንሰ-ሃሳብ ያለዉ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠልም የትምህርት ምንነትና ግቦች ዙሪያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ ጥራት ያለዉ ትምህርት ለጸረ-ሙስና ትግል የሚኖረዉን ፋይዳም ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫዉ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ በማድረግ ግንዛቤያችሁን እንዲታዳብሩ ትመከራላችሁ፡፡

## *የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች*

ቀትሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን በአግባቡ ካነበባችሁ በኋላ መልሶቻችሁን በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

1. ሙስና ማለት ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌዎች አስደግፋችሁ የተረደዳችሁትን በጽኁፍ ግለጹ?
2. የትምህርትን ጽንሰ-ሃሳብ እና ግቦች በተመለከተ የተረዳችሁትን በመዘርዘር ማብራሪያ ስጡባቸዉ?
3. ትምህርት ለጸረ-ሙስና መሳሪያነት ያለዉን ሚና ተንትኑ?
4. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያትን ዘርዝሩ?
5. የሙስና መገለጫዎችን በተመለከት ያገኛችሁትን ግንዛቤ መሰረት በማድረግ ለሌሎች ተሳታፊዎች ሃሳባችሁን አካፍሉ?

## ምዕራፍ ሁለት፡ በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎችና የሚስተዋሉ ክስተቶች (7 ሰዓታት)

በመጀመሪዉ ምዕራፍ የሙስና ወንጀሎችን አስመልክቶ ጽንሰ-ሃሳቡን፣ በትምህርት ዘርፉ ሙስና ለምን፣ እንዴት እና ትምህርት ለጸረ-ሙስና ትግል የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ተዳስሰዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የትምህርት ዘርፉ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚኖረዉን ተጋላጭነት፣ ለተጋላጭነቱ እንደምክንያት የሚነሱ ጉዳዮች፣ የአገሪቱ የትምህርት ጥራት መዉደቅ፣ የመምህራን ስልጠና ሁኔታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት፣ የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት፣ ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲሁም ስነ-ምግባርና ዕሴቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራቸዉን ቁርኝት ትኩረት በማድረግ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም በትምህርት መስኩ በአጠቃላ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲሁም በአስተዳደርና በአካዳሚክ ዘርፍ ያሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ዙሪያ ማብራሪያዎች በስፋት ይቀርባሉ፡፡

### የምዕራፉ ዓላማዎች/የሚጠበቁ የባህሪ ገጽታዎች

የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች በትክክል ተከታትለዉ ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች፡-

- የኢትዮጵያን የትምህርት ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ይለያሉ፡፡
- የትምህርት ዘርፉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተጋላጭነት ምክኒያቶች ይዘረዝራሉ፡፡
- የትምህርት ጥራት መውደቅ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉን አንድምታ ይገልጻሉ፡፡
- ሥርዓተ-ትምህርት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉን ግንኙነት ይተነትናሉ፡፡
- የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራችዉን ተያያዥነት ይገመግማሉ፡፡
- ሃላፊነትና ተጠያቂነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራቸዉን ቁርኝት በመገንዘብ ሚናቸዉን በአግባቡ ይወጣሉ፡፡
- ሥነ-ምግባር እና እሰቶቸ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን ግንኙነት በመገንዘብ ጥሩ ሥነ-ምግባርና መልካም እሰቶችን በተላበሰ መልኩ ስራቸዉን ይፈጽማሉ፡፡
- የትምህርት ዘርፉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች ይዘረዝራሉ፡፡
- በትምህርት መስኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ይተነትናሉ፡፡
- በአካዳሚክ ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፡፡

➢ የመሱናና ብልሹ አሰራሮች አጠቃላይ መገለጫዎችን በዝርዝር ከለዩ በኋላ የትምህርት መስኩ ምን ያክል ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንደተጋለጠ ለሌሎች ያስረዳሉ፡፡

## 2.1. በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትና ምክንያቶች

በዚህ ክፍል በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትንና ምክንያቶቹ ይቀርባሉ፡፡

**መልመጃ 2.1.1. (7 ደቂቃዎች)**

ከ 4-5 አባላት ያሉትን ቡድን በመመስረት ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎችና ሃሳቦች ዙሪያ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ከተወያያችሁ በኋላ ለሌሎች ሰልጣኞች አስረዱ፡፡ የዉይይታችሁን ሃሳቦች ደግሞ ቀጥሎ በማስታወሻነት ከቀረቡት ማብራሪያዎች ጋር በማስተያየት አዳብሩ፡፡

1. በእናንተ አረዳድ የትምህርት ዘርፍ የሚባለዉ ምንድነዉ? እነማንንስ ያካትታል?
2. የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ማለት ምን ማለት ነዉ?
3. በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትን አስመልክቶ ተጨባጭ ምሳሌዎችን በመጠቀም ያላችሁን ግንዛቤ ለቡድን አባላቶች አብራሩ፡፡

**ማስታወሻ**

**የትምህርት ዘርፍ** ሲባል የትምህርት አገልግሎትን የሚሰጡ የትምህርት ተቋማትን (ማለትም ትምህርት ቤቶችን፣ ኮሌጆችን፣ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆችንና ዩኒቨርሲቲዎችን) የሚያካትት ሆኖ በትምህርት አስተዳደርም ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ጀምሮ እስከ ወረዳ ትምህርት ፅ/ቤት ድረስ ያሉ ተቋማትን የሚመለከት መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ **በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት** ማለት ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲንሰራፉ/እንዲስፋፉ የሚያበረታቱ/ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን/ የስራ ክፍሎችን እና የአሰራር ስርዓቶችን የሚመለከት ነዉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች/የስራ ክፍሎች/የአሰራር ስርዓቶች ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመፈጸም የሚቀሉ/የሚያመቹ መሆናቸዉን፣ እንዲሁም አስፈላጊዉ ቅድመ-ጥንቃቄ ካልተደረገ፣ ትምህርት ካልተሰጠና ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ካልተደረገና የዕርምት እርምጃዎች ካልተወሰዱ በትምህርት ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረስ የሚችሉ ድርጊቶች እንዲፈጸሙ የሚረዱ/ አስቻይ (ምቹ)

ቦታዎች/ ነባራዊ ሁኔታዎች ናቸዉ። ሃሳቡን የበለጠ ለመረዳት ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች ማየት ጠቃሚ ነዉ።

- በትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዳይኖሩ/እንዲቀንሱ ሊያደርጉ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አለመኖር በተወሰነ ደረጃ ቢኖሩም ለሰራተኞች ሁሉ በሚፈለገዉ መጠን ግንዛቤ በማስጨበጥ ስራ ላይ እንዲያዉሉት አለማድረግ/በስራ አለመተርጎም /ስራ ላይ መዋላቸዉን አለመከታተል/ ተከታትሎም የእርምት እርምጃ አለመዉሰድ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤
- በሌላ በኩል ደግሞ የጸረ-ሙስናና ስነ-ምግባር ኮሚሽን ዶክመንቶችና መመሪያዎች እንደሚያዙት እያንዳንዱ ተቋም የተልዕኮዉን መግለጫ እና የስራ ድርሻዎችን በማዘጋጀትና ለሰራተኞቹ በማስገንዘብ ወደ ስራ እንዲገቡና ስራቸዉን በአግባቡ ሰርተዉ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የበኩላቸዉን አስተዋጽኦ ማድረግ አለመቻል ወይንም ክፍተት ማሳየት በራሱ አንዱ የተጋላጭነት ምሳሌ ይሆናል፤
- ሌላኛዉ ለትምህርት መስኩ እንደ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት የሚወሰደዉ ጉዳይ ደግሞ ከተቋማቱ ከሚጠበቁ አሠራሮች መካከል በየወቅቱ የሙስና ስጋት ትንተና ባለማድረግ፣ ተቋማቱ ያሉባቸውን ክፍተቶች ባለመለየትና የመፍትሄ እርምጃ አለመዉሰድ/ ችግሩን መፍታት የሚያስችል ስራ አለመስራት/ ማዘግየት/ በሚጠበቀዉ ደረጃ ችግሩን አለመገንዘብና መፍትሄዎቹንም በሚጠበቀዉ ልክ አለመለየት፤ ይልቁንስ ማዘረከረክ ይገኙበታል።

ከላይ እንደምሳሌ የቀረቡትን ሃሳቦች መሰረት በማድረግና እንደየተቋማችሁ ነባራዊ ሁኔታ በእናንተ እይታ በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ሊሆኑ የሚችሉትን ሌሎች ጉዳዮችን ጭምር በማንሳትና በመዘርዘር የበለጠ ግንዛቤያችሁን ማዳበር ትችላላችሁ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በቡድን በመሆን ካነበባችሁ በኋላ ተያይዘዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች በመስራት ግንዛቤአችሁን አዳብሩ።

**ኬዝ 2.1.1. የትምህርት ጊዜያት ብክነት**

*በትምህርት ሚኒስቴር የተደረገ አንድ ጥናት እንዳመላከተዉ በአገራችን ባሉት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ቢያንስ 4-5 ደቂቃዎች ይባክናሉ። ይህ ደግሞ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ፣ ቀናት እና ወራት ቢሰላ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የትምህርት ጊዜያት የሚባክኑ መሆኑን በማዉሳት የአገራችን የትምህርት ጊዜያት ብክነቶች ከአለም አቀፍና*

ከአፍሪካ አገራት አንጻር ሲታይ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳል። ይሄን ጉዳይ ከትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር በማስተሳሰር ያላችሁን ሃሳብ አቅርቡ። ተማሪዎች ትምህርታቸዉን በአግባቡና በጊዜዉ ተምረዉ የሚጠበቅባቸዉን ብቃት ማጎልበት እንዲችሉ ከማድረግ ጋር ያለዉን ግንኙነት ከግምት በማስገባት ተወያታችሁ የደረሳችሁበትን ለሌሎች ተሳታፊዎች ሃሳባችሁን አካፍሉ። አገር ገንቢ የሆኑ ዜጎችን የማፍራት ተልዕኮዉንም ከማሳካት አንጻር ሊኖረዉ የሚችለዉን እንድምታ ዘርዝሩ።

**መልመጃ 2.1.2 (7 ደቂቃዎች)**

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ በመወያየት መልሱ**

1. አንድ የትምህርት ተቋም ከላይ ከተጠቀሱት የተጋላጭነት ማሳያ ምሳሌዎች ዉስጥ በተወሰኑት ላይ ጥቂት ክፍተቶች ብቻ ቢኖሩት ተቋሙ የሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት አለዉ ወይስ የለዉም? ለምን?
2. የተቋሙን የሙስናና ብልሹ አሰራር መታገያ አቅሙንስ ይፈታተናል ውይሰ አይፈታተንም? ለምን? ምንስ መደረግ አለበት ይላሉ?
3. በትምህርት መስኩ ሊኖሩ የሚጠበቁ የአሰራር ስርዓቶች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መኖር ወይም አለመኖር ከተቋማቱ አጠቃላይ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት የሚኖራቸዉ አንድምታ ምንድነዉ? ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አንጻር ያላቸዉ ሚናስ ምንድነዉ?

**ማስታወሻ**

በትምህርት መስኩ በ 2014 ዓ.ም. የተደረገዉ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየዉ እያንዳንዱ የትምህርት ተቋም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮች መኖር አለመኖሩን፣ በሚመለከተዉ አካል የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መተግበራቸዉን/ ስራ ላይ ማዋላቸዉን የሚቆጣጠር፣ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የመታገል ስራዎች የሚያስተባብርና የሚያስፈጽም የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ማቋቋሙንና አስፈላጊዉን ድጋፍ ማድረጉን ለመዳሰስ ተሞክሯል። የተደረገዉ ጥናት ዉጤት እንደሚያሳዉ ከሆነ አብዛኛዎቹ (60%) የጥናቱ ተሳታፊዎች በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የተቋቋመ መሆኑን ሪፖርት ያደረጉ ቢሆንም ጥቂት የማይባሉ (29%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ የስነ-ምግባር

መከታተያ ክፍል መቋቋሙን እንደማያውቁ ገልፀዋል፡፡ ይህ ደግሞ አንዳንድ የትምህርት ተቋማት እና ትምህርትን የሚመሩ መስሪያ ቤቶች ለሰራተኞቻቸው የግንዚቤ ማስጨበጫ ስልጠና ያለመስጠታቸውን ከማሳየቱም በተጨማሪ ወደፊት በሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ በሚያደርጉት ትግል ላይም የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረዉ ግልጽ ነዉ፡፡

በተጨማሪም ይሄዉ በትምህርት መስኩ የተደረገዉ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየዉ ቀላል የማይባሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች (37 እና 29 በመቶ የሚሆኑት) በቅደም ተከተል እንደገለጹት በተቋማቸው ውስጥ በመልካም ሥነ-ምግባር አርአያ የሆኑ አመራሮችንና ሠራተኞችን የመለየትና ዕዉቅና የመስጠት ልምድ አለመኖሩን አስረድቷል፡፡ ከዚያን በፊትም የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ በተቋማት ውስጥ የመረጃ ግልፅነት መጓደልና የተቆራረጠ ፍሰት መኖር አንድን መስሪያ ቤት ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስጋት ተጋላጭ ከሚያደርጉ ጉዳዮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ አንድ ተቋም የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ለመታገል የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን፣ የህግ ማዕቀፎችን፣ አደራጃጀቶችንና እነዚህን ተቋማትና የአሰራር ማዕቀፎችን በሚገባ ተረድቶ ወደተግባር የሚቀይር/የሚተገብር አካል ሊኖረዉ ግድ የሚልና ሃላፊነትንና ተጠያቂነትን በአግባቡ የሚወጡ ሃላፊዎችና ሰራተኞች እንዲኖሩት የሚያስፈልግ መሆኑንና በነዚህ ዙሪያ ክፍተቶች ካሉ ግን ተቋሙ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉ መሆኑን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የተጋላጭነቱ መኖር ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በተቋሙ እንዲንሰራፉ አስቻይ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ መሆናቸዉን በዉል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠል በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ምክንያቶች ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በዝርዝር የምንመለከት ስለሆነ እንደ መነሻ ሃሳብ ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝና የመልመጃ ጥያቄዎች መጀመሪያ በየግላችሁ በመሞከርና በመቀጠልም በሃሳቡ ዙሪያ ሁለት ሁለት በመሆን ዉይይይ አድርጉ፡፡

### ኬዝ 2.1.2. በከፍተኛ ትምህርት የሃላፊነትና ተጠያቂነት ሁኔታ

*በአንድ አንድ የአገራችን ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች በነበራቸዉ ሃላፊነትና የመፈጸም አቅም ተጠቅመዉ ህግና ደንቡ ከሚፈቅደዉ ዉጭ ግዥዎችን የመፈጸም፣ የተለያዩ ክፍያዎችን የመፈጸም፣ ንብረቶችን የማስተላለፍና የመጠቀም፣ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት ሁኔታዎች እንደነበሩና በሂደቱም የተሳተፉ አካላት ብዛት ያላቸዉና በቡድን ጭምር የተደራጁ የሚመስሉ ሁኔታዎች እንደነበሩ የተለያዩ የመንግስትና የግል ሚዲያዎች ሲያወሱት እንደነበረ ይታወቃል፡፡* ይህ አይነቱ ተግባር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ካላቸዉ የተጋላጭነት ደረጃ አንጻር ሲታይ ምን አንድምታ አለዉ? ገጽታቸዉን ከማበላሸትና ተአማንነታቸዉን ከማሳጣት አንጻርስ እንዴት ይታያል? አገራዊ ተልዕኮዎቻቸዉን በትክክል ከማሳካት አንጻርስ ምን አንድምታ ይኖረዋል?

**መልመጃ 2.1.3 (5 ደቂቃዎች)**

1. በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ምክንያቶች ይሆናሉ ብላችሁ የሚታስቧቸዉን ዋና ዋና ጉዳዮች መጀመሪያ በግል በመዘርዝርና ቀጥሎ ደግሞ በቡድን በመሆን ዉይይት አድርጉባቸዉ፡፡ የደረሳችሁበትን ሃሳብ ለሌሎች ሰልጣኞች አካፍሉ፡፡

**ማስታወሻ**

በትምህርት ዘርፉ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት እንደምክንያት የሚነሱ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም በመስኩ በተደረገዉ ጥናት የተለዩት ግን **በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች** ተከፍለዉ ቀርበዋል፡፡ እነሱም፡-

1. **ከግለሰቦች የስነ-ምግባር አቋም ወይም የሞራል ልዕልና ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች፡-** ይህ ጉዳይ ግለሰቦች ምንም ሳይሰሩ በአጭር ጊዜ ለመክበር መፈለግ፣ የሰዎች ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ መሆን፣ የሞራል መላሸቅ ወይንም ዋልጌነት፣ ሱሰኛ መሆን፣ ግልጽ አሰራሮችን አለመዉደድ፣ደንብና መመሪያዎችን ጠንቅቆ አለማወቅ፣ ግዴለሽነት፣ የስራ ሃላፊነትን የመዉሰድ ዝቅተኛ ተነሳሽነት እና የማህብረሰቡን ጥሩ አመለካከቶች ወደማይጠቅሙ አመለካከቶች መቀየርን ያካትታል፡፡ እንዲህ አይነቱ ተግባራት በትምህርት ዘርፉም የሚስተዋሉ ጉዳዮች መሆናቸዉን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡
2. **ከአሰራር ጋር የሚያያዙ ምክያቶች፡-** አሰራር ሲባል በየተቋማቱ የሚገኙ አመራሮች ያሏቸውን ተነሳሽነትና አርአያነት፣ በተቋሙ የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎችንና ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘረጉ አሰራሮችን የሚመለከት ነው፡፡ የተጠናከረ የቁጥጥር ስርአት አለመኖር፣ የአመራሩ ልል መሆን፣ የህግ መላላት፣ ለተፈጸሙ ወንጀሎች መፍትሄ ያለማግኘት፣ የሚሰራን ሰው አለማበረታታት፣ ግልፅኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር አለመኖር፣ ሰራተኞች በብቃታቸውና በችሎታቸው ተመዝነው አለመቀጠር፣ ስልጠና አለመኖር፣ ማበረታቻ

(Motivation) አለመኖር እና ፍትሃዊ አስተዳደር አለመኖር ምክንያቶቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ በትምህርት መስኩ የተደረገዉ ጥናት አመላክቷል፡፡

3. **ከኢኮኖሚ ወይም ከገቢ መጠን ጋር የሚነሱ ችግሮች፡-** ከኢኮኖሚ አንፃር ጥናቱ እንዳመላከተዉ የሰራተኛዉ ገቢ ማነስ ወይም መንግስት ለሰራተኞች የሚከፍለዉ ደመወዝ እና የኑሮ ደረጃዉ አለመመጣጠን እና የሰዎች ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ለሙስና በር የሚከፍት ሆኖ ተጠቅሷል፡፡ የገቢ ማነሱ ግለሰቦች ሌሎች የገቢ አማራጮችን እንዲመለከቱና ወደ ሙስና እንዲገቡ ያደርጋቸዋል የሚል ሃሳብም በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

በተጨማሪም በትምህርት መስኩ ያሉትን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ምክንያቶችን የበለጠ ለመረዳት በማሰብ ኮሚሽኑ ጥናት ያደረገ ሲሆን በትምህርት ዘርፉ ዉስጥ ያሉ ሰራተኞች ለሙያቸው ያላቸው ክብርና የሚያንፀባርቁት የሙያ ስነ-ምግባር ምን ያህል እንደሆነ ለማየት ተሞክሮ የተገኘዉ ዉጤት እንደሚያሳየዉ ከሆነ ሁሉም ሰራተኞች ለሙያቸው ታማኝ ናቸው ማለት እንደሚከብድ፣ ሙያቸውንና ስራቸውን አክብረው የሚሰሩ እንዳሉ ሁሉ የማይሰሩም እንዳሉ ተመላክቷል፡፡ ሌሎች ደግሞ ከሙያ ስነ-ምግባር ይልቅ ለፖለቲካ እንደሚያደሉና ከሙያዊ አፈጻጸም ይልቅ ከአለቆቻቸዉ ጋር ከሥራ ውጪ ባላቸዉ ልዩ ግንኙነት ያለ ሥራ ለመኖር የሚሞክሩ እንዳሉም አስረድቷል፡፡

በአጠቃላይ በትምህርት ሴክተሩ ያሉት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ምክንያቶች ዘርፈ ብዙ መሆናቸዉን መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑንና ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመዋጋት ሂደት ላይ የሚኖራቸዉ ተጽዕኖም እጅግ የጎላ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም በትምህርት ዘርፉ የሚፈጸሙት ሙስናዎችና ብልሹ አሰራሮች የትምህርት ተቋማቱን አሰራሮችና ተያያዥ ጉዳዮችን ብቻ የሚጎዱ ሳይሆኑ አጠቃላይ የየትኛዉንም የስራ መስክ፣ አገልግሎት፣ ሃብት እንዲሁም ሁሉንም የማህብረሰብ ክፍሎች ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የመፍጠር አቅም ጭምር ያላቸዉ መሆኑ ጉዳዩን የከፋ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ የሚፈልግ መስክ መሆኑን በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በሚገባ በማየት አንድምታዉን ለመረዳት ሞክሩ፡፡

**ኬዝ 2.1.3፡- ከመምህራን ገቢና የሙያ ስነ-ምግባር ጋር የተያያዘ**

*አንድ የዩኒቨርሲቲ መምህር የሚከፈለኝ ደመወዝ በጣም አነስተኛ ስለሆነ የወር ወጪዎቼን መሸፈን አልቻልኩም በሚል እሳቤ ከማስተማር በተጨማሪ ሌሎች ስራዎችን በመስራት*

ኑሮዉን ለመደጎም ይወስናል፡፡ በዚሁ መሰረት በሌሎች መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡ አሳይንመቶችን፣ የፕሮጀክት ስራዎችን እና የመመረቂያ ጽሁፎችን እራሱ በመስራት (መልሶቹን በሚጠየቀዉ መሰረት በማዘጋጀት) ለተማሪዎች በገንዘብ ለመሸጥና በሚገኘዉ ገቢ ኑሮዉን ለመደጎም ጥረት ማድረግ ጀመረ፡፡ ይሄንኑ ተግባሩን በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎች ጭምር በማስተዋወቅ ገበያ የማፈላለግ ስራም እየሰራ ነዉ፡፡ በእናንተ እሳቤ የዚህ መምህር ተግባራት ከሙስናና ብልሰሹ አሰራሮች አንጻር እንዴት ይታያሉ? ከላይ ከተዘረዘሩት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተጋላጭነት ምክንያቶች ዉስጥ ከየትኞቹ ጋር ይገናኛል? እንዴት? ለምን? የመምህርነት ሙያ ስነ-ምግባር አክብሮ ከመስራት አንጻር ምን አንድምታ አለዉ? እንዲህ አይነቱ ተግባር በትምህርት መስኩ ላይ ሊኖረዉ የሚችለዉ አሉታዊ ተጽዕኖስ አለ ወይ? በተጨባጭ መረጃዎች አስደግፋችሁ ሃሳቦቻችሁን አስረዱ፡፡

## 2.2. የትምህርት ጥራት መዉደቅ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉ ቁርኝት

በክፍል 2.1 ስር በትምህርት ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትና ለተጋላጭነቱም እንደ ምክንያት የሚወሰዱ ዋና ዋና ጉዳዮች በሰፊዉ ተዳስሰዋል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ የአገሪቱ የትምህርት ጥራት መዉደቅ በዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትና ምክንያቶቹ ጋር የሚያስተሳስረዉ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በዚሁ መሰረት የትምህርት ጥራት ምንነት፣ የአገሪቱ የትምህርት ጥራት አሁናዉ ነባራዊ ሁኔታ እና የትምህርት ጥራት መዉደቅ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት የሚኖረዉ ሚና እንዲሁም ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመዋጋት ሂደት ጥራት ያለዉ ትምህርት የሚኖረዉን ሚና ለማየት ጥረት ይደረጋል፡፡

**መልመጃ 2.2.1. (7 ደቂቃዎች)**

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መጀመሪያ በየግላችሁ አስቡ፣ ቀጥሎ ደግሞ በቡድን በመሆን ተወያይታችሁበት መልሱ፡፡

1. በእናንተ አረዳድ የትምህርት ጥራት ማለት ምን ማለት ነዉ? የትምህርት ጥራት መለኪያዉ ምንድነዉ? ትምህርት ጥራት አለዉ የሚባለዉ ምን ምን ጉዳዮች ሲኖሩት ነዉ? የእኛን አገር አሁናዊ የትምህርት ጥራት ደረጃ እንዴት ትገልጻላችሁ?
2. ጥራት ያለዉ ትምህርት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመዋጋት አንጻር የሚኖረዉ ፋይዳ ምንድነዉ?

**ማስታወሻ**

በትምህርት መስኩ ያሉ ምሁራን ‹ጥራት› ለሚለዉ ቃል የተለያዩ ፊቺዎች የሚሰጡ ሲሆን በዋናነት ግን **ሃርቬይ** የሚባል ምሁር በ2004 የትምህርትን ጥራት ትርጉም ከአምስት ዋና ዋና ዕይታዎች አንጻር በመከፋፈል አስቀምጧል፡፡ እነሱም፡-

- ጥራት ማለት ከታለመዉ አላማ ጋር መስማማት (የታለመዉ አላማ ጋ መድረስ) ነዉ (Quality as fitness for purpose)
- ጥራት ማለት ላወጣነዉ ወጪ ዋጋ መስጠት ነዉ (Quality as value for money)
- ጥራት ማለት ሁለንተናዊ ለዉጥ ማምጣት ነዉ (Quality as transformative)
- ጥራት ማለት የላቀ/ተምሳሌታዊ ሆኖ መገኘት ነዉ (Quality as excellence)
- ጥራት ማለት ወጣ ያለ ብቃት፣ አልፎ አልፎ የሚገኝና በቀላሉ የማይደረስበት የልኬት ጥግ ነዉ (Quality as Exceptions) የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሆኖም ግን በአገራችን በትምህርት መስኩ ያሉት ተቋማት ጥራትን የሚመለከቱት ከላይ ከተጠቀሱት የጥራት አረዳድ እሳቤዎች ዉስጥ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ውይንም ሶስቱን ከግንዛቤ በመዉሰድ ነዉ፡፡ ስለሆነም ጥራት ማለት የተቀመጠዉን የትምህርት አላማ ወይንም ዝቅተኛ የመማር ብቃቶችን አሳልብቶ መገኘት፤ ለትምህርት ያወጣናቸዉን ወጪዎች ዋጋ በመስጠትና ከትምህርቱ የምንፈልጋቸዉን ዉጤቶች ማግኘታችንን ማረጋገጥ፤ የተፈለገዉን ሁለንተናዊ ለዉጥ ማምጣት መቻላችንን ማረጋገጥ የሚሉ እሳቤዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ጥራት ከግብዓት በበቂ ሁኔታና ጥራት ደረጃ መገኘት፣ ከሂደትና ከሚገኘዉ ዉጤት አንጻርም የሚታይ ጉዳይ መሆኑ ከግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ስለሆነም ለትምህርት ጥራት የምንሰጠዉ ትርጉሙም ሆነ ትምህርቱ ጥራት አለዉ ወይንስ የለዉም የሚለዉም ጥያቄ ለመመለስ ከላይ የተሰጡትን ሃሳቦች ከግንዛቤ በማስገባት ማየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የአገራችን የትምህርት ጥራት ሁኔታ በሁሉም የትምህርት እርከኖች በሚባል ደረጃ ችግር ያለበት መሆኑን የሚጠቁሙ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ በ2018 ዓ.ዓ በኢትዮጵያ ደረጃ የተደረገዉ የሮድ ማፕ ጥናት (Road Map Study) እና ሌሎች ጥናቶችም እንደሚያስረዱት የአገራችን የትምህርት ጥራት ደረጃ በሁሉም የትምህርት

እርከኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም ከማሽቆልቆሉም በላይ መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መፈኛጪያም መሆን ከጀመረ ዉሎ ማደሩን የተገኙ ዉጤቶች ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በትምህርት ሴክተሩ በሚሰጡ ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች ዙሪያም ብዙ ክፍተቶች ያሉ መሆኑንና በየደረጃዉ ጉዳዩ በሚመለከታቸዉ ሁሉም አካላት አፋጣኝ የእርምት እርምጃዎች ካልተወሰዱ በስተቀር የከፋ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ እጅግ አሳሳቢ ነገሮች እየተስተዋሉ መሆናቸዉም እሙን ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር የትምህርት ጥራቱ ማሽቆልቆል በስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ትግሉ ላይ የሚኖረዉን አንድምታም በሚገባ ማጤንና መረዳት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ ቀትሎ የቀረበዉን ኬዝ በጥሩ ሁኔታ በማጠን ጥያቄዎቹንም መልሱ፡፡

**ኬዝ 2.2.1፡- ከትምህርት ጥራት ማሽቆልቆል ጋር የተያያዘ**

*እንደሚታወቀዉ ባለፉት ሶስት ተከታታይ አመታት (ከ2014 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም) በትምህርት ሚኒስተር በተወሰደ እርምጃ መሰረት አገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል ፈተናን በዩኒቨርሲቲዎች እንድተገበር ከተደረገ በኋላ ፈተናዉን ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል በቅደም ተከተል 3.3 በመቶ፣ 3.2 በመቶ እና 5.4 በመቶ ብቻ የማለፊያ ዉጤት ያስመዘገቡ መሆኑ ይታወቃል፡፡* በእናንተ አረዳድ ይህ ዉጤት የአገሪቱን የትምህርት ጥራት ዉድቀት/ስብራት በትክክል ያሳያል ብላችሁ ታስባላችሁ ወይ? የትምህርት ጥራት መገለጫዎች ተብለዉ ከተዘረዘሩት እሳቤዎች አንጻርስ ምን ትርጉም ይሰጣችኋል? ይህ አይነቱ ዉጤት ደግሞ የአገሪቱ የትምህርት ጥራት ከፍተኛ ስብራት የደረሰበት መሆኑንና ብዙም መሻሻል እየታየበት እንዳልሆነ በግልጽ ያሳያል ወይ? ከሆነስ ለትምህርት ዘርፉ የሚኖረዉ ተጽዕኖ ምን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትና ምክንያቶቹስ ምን አንድምታ አለዉ?

**ማስታወሻ**

ከትምህርት ጥራት መገለጫዎች አንዱ የተፈለገወን የትምህርት ዓላማዎች/ዝቅተኛ የመማር ብቃቶችን መጎናጸፍ እንደሆነ ተገልጾአል፡፡ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ የተቀመጠዉ አላማ ከግብ መድረስ አለመድረሱ ሳይታወቅ (የግለሰቦች የመማራቸዉ ሁኔታ በሚገባ ሳይረጋገጥ እና ዝቅተኛዉን የመማር ብቃቶች መጎናጸፋቸዉ ሳይታይ) ከክፍል ክፍል የሚዛወሩ ከሆነ፤ ከትምህርት ተቋማት የሚመረቁና ወደ ስራ አለም የሚቀላቀሉ ከሆነ በሚሰጡት አገልግሎት ላይ ክፍተት ማሳየታቸዉ የማይቀር ጉዳይ ነዉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ድርጊት ደግሞ በራሱ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች በር የሚከፍትና እነዚህ እኩይ ተግባራት እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታ

የሚፈጥር በመሆኑ ከትምህርት ዘርፉም በተጨማሪ ሌሎች ሴክተሮችንም ጭምር የሚጎዳና እጅግ ከፍተኛ የሆነ ቀዉስ የሚፈጥር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን ላይ በአገራችን ያለዉ የትምህርት ጥራት በከፍተኛ ሁኔታ መጓደል የሚታይበት መሆኑ የማያጠያይቅ ከመሆኑም ባሻገር ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት እጅግ የጎላ ሚና የሚጫወት መሆኑን የበለጠ መረዳት አስፈላጊ ነዉ፡፡ እንደምሳሌ ለመዉሰድ ያክል መማር ሶስት ዋና ዋና ለዉጦችን ማምጣት የሚጠይቅ ሲሆን ሶስቱም የማይነጣጠሉ እና ጎልብተዉ በተግባርም ተፈጻሚ መሆን የሚገባቸዉ ጉዳችን ይይዛል፡፡ እነሱም በአእምሮ የማሰብ አቅም፣ ሙያዊ ብቃቶችን ማጎልበትና የሚፈለገዉን የባህሪ ለዉጥ አምጥቶ መገኘት ናቸዉ፡፡ ከነዚህ ዉስጥ አንዱን እንኳን በሚፈለገዉ የጥራት ደረጃ ይዞ አለመገኘት ብቃታችን ላይ ክፍተት መኖሩን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በስራችንም ዉጤታማ እንዳንሆን ያደርገናል፡፡ ስለሆነም ጥራቱን ያልጠበቀ ትምህርት መስጠት የዜጎችን መብት ካለመጠበቅም በላይ አገር ላይ ከፍተኛ የሆነ የዉድቀት አዋጅ ከማወጅና በተግባርም አገርን ለማፍረስ ከመንቀሳቀስ አይተናነስም፡፡ ምክንያቱም በእንደዚህ አይነት ስርዓት ዉስጥ አልፎ ነገ አገር የሚረከብ ዜጋ አገራዊ ሃላፊነቱን በሚገባ በመወጣትና አገርን በቀጣይነት የመገንባት ስራዉን ወቅቱ በሚጠይቀዉ እዉቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት፣ እሳቤ እና ተክኖሎጂ በመጠቀም የመፈጸም አቅም አይኖረዉም፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ለዜጎች በማዳረስ አገራዊ ዕይታዎችና አለም-አቀፍ እሳቤዎችን በሚገባ የተረዱ፣ አገርን በመገንባት ሂደት በቆራጥነት፣ በታማኝነትና በልበ-ሙሉነት የላቀ ተሳትፎ የሚያደርጉ፣ ወቅቱ የሚፈልገዉን እዉቀት፣ ክህሎትና በጎ አመለካከት የታጠቁ እና ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ለፍተዉ የድካማቸዉን ዋጋ ብቻ ማግኘትን የሚያልሙ እና ለሌሎችም የሚያስቡ የአገር አለኝታዎች መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህ አይነት የትምህርት ስርዓት ሲኖር ነዉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚጸየፉ እና ተጋላጭነቱም እንዳይኖር የበኩላቸዉን በጎ ሚና የሚጫወቱ ዜጎችን መፍጠር የሚቻለዉ፡፡

## *2.3. የመምህራን ስልጠናና የስራ ስምሪት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ ቁርኝት*

በክፍል 2.2 ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር በማያያዝ የትምህርት ጥራት ሚናን ከትምህርት ጥራት እሳቤዉ በመጀመርና የትምህርት ጥራት መጓደል ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት የሚኖረዉን ሚና ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ

የመምህራን ስልጠናና የስራ ስምሪት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን መስተጋብር ለመዳሰስ ጥረት ይደረጋል፡ በዚሁ መሰረት በኢትዮጵያ የመምህራን ስልጠና ሁኔታ እና የስራ ስምሪት ምን እንደሚመስል፣ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ ቁርኝት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ፡፡

**መልመጃ 2.3.1. (7 ደቂቃዎች)**

ልምዳችሁን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በየግላችሁ መልሱ፡፡

1. የአገራችንን የመምህራን ስልጠና ሁኔታ እንዴት ትገመግማላችሁ? ከሰልጣኝ ምልመላ ጀምሮ በስልጠና አሰጣጡ፣ አመራሩና ግምገማዉ እንድሁም ምደባዉ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት አንጻር ሲታይ ምን ይመስላል?
2. የመምህራን ስልጠናዉ ጥራት ያለዉ ትምህርት ለዜጎች ከማቅረብ አንጻር ምን ሚና ይኖረዋል?
3. የኢትዮጵያን የመምህራን የስራ ስምሪትና እድገት አሰጣጥ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር በማያያዝ ያላችሁን ሃሳብ አቅርቡ?

**ማስታወሻ**

የመምህራን ስልጠና በአገራችን ከተጀመረ ወደ 80 ዓመታት የሚጠጋ እድሜ ቢኖረዉም መስኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥራቱን ጠብቆ ብቃትና ብዛት ያላቸዉን መምህራን በሁሉም የትምህርት እርከኖች ከማፍራት ይልቅ በየጊዜዉ ለተለያዩ ችግሮች ሲዳረግ የኖረ መሆኑን በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ በዚህ የሽምግልና እድሜዉ የመምህራን ስልጠናዉ ከፍተኛ የሆነና እጅግ በጣም ዉስብስብ የሆኑ፣ ሳይፈቱ ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ዉጣ ውረዶች ዉስጥ አልፎ ዛሬ ላይ የደረሰ ፕሮግራም እንደ መሆኑ መጠን ለሙስናና ብልሹ አሰራሮችም ተጋላጭነቱ እየጎላ የመጣ መስክ ነዉ፡፡ ለምሳሌ በቅርብ አመታት ብቻ የተደረጉ ጥናቶችን ዋቢ አድርጎ ለማንሳት ቢያስፈልግ በ2003 ዓ.ዓ. ስር ነቀል የመምህራን ትምህርት ጥናት (Teacher Education System Overhaul or TESO) የሚባለዉ ዶክመንት እንደ ችግር ያነሳቸዉን ዋና ዋና ጉዳዮች ለመፍታት ተብሎ በ3 ዓመት የድግሪ ፕሮግራም መምህራንን የማሰልጠን እቅድ ተነድፎ ለተወሰኑ አመታት መምህራንን ማሰልጠን የተቻለ ቢሆንም በጥናቱ የተለዩት ዋና ዋና ችግሮች ግን እንደታሰበዉ ሳይፈቱ መቅረታቸዉ፤ ከዚያም አልፎ

በተለያዩ ጊዜያት በሌሎች የመምህራን ስልጠና ፕሮግራሞች ላይም ጥናቶች ተደርገዉ ተመሳሳይ ችግሮች የተገኙ መሆናቸዉ አንዱ ማሳያ ነዉ።

በተጨማሪም በ2018 እ.ኤ.አ. የሮድ ማፕ ጥናት (Road Map Study) አካል ተደርጎ በመምህራን ስልጠና ፕሮግራሙ ላይ የተደረገዉ ጥናት እንዳሳየዉ የመምህራን ስልጠናዉ ከምልመላ ጀምሮ እስከ ስምሪትና እድገት ድረስ በብዙ ችግሮች የተተበተበና የሚፈለገዉንም ጥራትና ብቃት ያለዉ መምህር በበቂ ሁኔታ ማፍራት ያልተቻለ መሆኑን አረጋግጧል። እንደምክንያትነት የሚነሱ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም መስኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች ጭምር የተተበተበ ስለመሆኑ የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል በዕጩ መምህራን ምልመላ ወቅት ክፍተቶች መኖራቸዉ፣ በስልጠና ወቅትም ብዙ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑ፣ በስራ ስምሪት ወቅትም እጅግ አስፈሪ የሆኑና ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ የሆኑ ድርጊቶች በብዙ ቦታዎች ላይ የሚስተዋሉ መሆናቸዉን መረዳት ያስፈልጋል።ለዚህ ማሳያዉ ደግሞ በስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በትምህርት ሴክተሩ የተደረገዉን የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት ብቻ ማየት በቂ ነዉ። በተጨማሪም ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በአግባቡ በማንበብ ከዚህ በታች የተነሱትን ጥያቄዎች መልሱ።

**ኬዝ 2.3.1.፦ የዕጩ መምህራን ምልመላና ምደባ ሁኔታን የሚመለከት**

*በኢትዮጵያ ዉስጥ በሚገኝ አንድ የዞን አስተዳደር በተደረገ የድፕሎማ ፕሮግራም እጩ መምህራን ምልመላ ወቅት በምልመላዉ ኮሚቴ ዉስጥ በነበሩ የተወሰኑ ግልሰቦች በመተባበር እነሱ የሚያዉቋቸዉ እጩዎች ባልተገባ መንገድ ዉድድሩን እንዲያሸንፉና የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ምርጫም ላይ የተሻለዉን ቦታና የትምህርት ፕሮግራም ማግኘት እንዲችሉ ከፍተኛ ሚና ተጫዉተዋል የሚል ሪፖርት ከዞኑና ከክልል የጸረ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከታተየያ ክፍሎች ጥቆማ ደርሶን ነዉ በማለት አበቱታ ቀረበ።* በእናንተ እሳቤ እንዲህ አይነቱ ድርጊት ቢፈጸም ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት አንጻር በመምህራን ስልጠናና ስምሪት ስራዉ ላይ የሚኖረዉ አንድምታ ምንድነዉ? መስኩንስ ለከፋ ችግር ይዳርጋል ብለዉ ያስባሉ? ከሆነስ ምን ምን ችግሮችን ልያስከትል እንደምችል በዝርዝር ያስረዱ?

**ማስታወሻ**

የመምህራን ስልጠና መስኩ በሁሉም ደረጃዎችና ቦታዎች በሚባል ሁኔታ እጅግ ዉስብስብ ችግሮች ዉስጥ ያለ መሆኑ፤ የወቅቱ የኑሮ ዉድነት ሁኔታም ታክሎበት ከፍተኛ የሆነ የሰዉ

ሃይል ፍልሰት የሚታይበትና በመስኩ ያለዉ የገቢ ሁኔታ አበረታች ካለመሆኑና ስራዉ ደግሞ አድካሚ ከመሆኑ የተነሳ ተተኪ ሃይልም እየጠፋ የሄደበት ከመሆኑ አንጻር ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉ አንድምታ በጣም ከፍተኛ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአገሪቱን የመምህራን ስልጠና ሁኔታ፣ የስራ ስምሪትና እድገት በሚገባ በማጠን አስፈላጊዉ የእርምት እርምጃዎች መወሰድ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በትምህርት መስኩ እንዳይንሰራፉ የበኩሉን ሚና ከመጨወቱም በላይ የአገሪቱን የትምህርት ጥራት ከማስጠበቅ አንጻርም ትልቅ ሚና መጫወት ይችላል፡፡

## *2.4. ሥርዓተ-ትምህርት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉ ግንኙነት*

ከላይ በቀረቡት ክፍሎች የትምህርት መስኩ በአጠቃላይና የመምህራን ስልጠናና የስራ ስምሪት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን መስተጋብርና ችግሮቹ በትምህርት መስኩ እንዳይንሰራፉ በማድረግ ጥረት ዉስጥ የሚኖራቸዉን ሚና ትኩረት በማድረግ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ክፍል ድግሞ የአገራችን ስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ግምገማና ማሻሻያ ሂደቶችና ተያያዥ ጉዳዮች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን ቁርኝት እና ችግሮቹን በመቅረፍ ሂደት የሚኖራቸዉን አስተዋጽኦ በተመለከተ ገለጻ ይደረጋል፡፡

**መልመጃ 2.4.1 (8 ደቂቃዎች)**

ልምዳችሁን መሰረት በማድረግና በቡድን በመሆን ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. በእናንተ እሳቤ ስርዓተ-ትምህርት ማለት ምን ማለት ነዉ? ከትምህርት ፖሊሲና ሌሎች የማስፈጸሚያ ስልቶች ጋር ያላቸዉ ግንኙነትና ልዩነት ምንድነዉ?
2. በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ያሉትን የአገራችን ስርዐተ-ትምህርቶች ጥንካሬና ክፍተቶች እንዴት ይገምግማሉ?
3. ስርዓተ-ትምህርቶቹ ጥራት ያለዉ ትምህርት ለዜጎች ከማቅረብ አንጻር ምን ሚና ይኖራቸዋል?
4. የኢትዮጵያ የስርዓተ-ትምህርት ይዘት፣ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ግምገማ፣ ማሻሻያና ሌሎች ስራዎች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን ጉድኝት በተመለከተ ያላችሁን ሃሳብ በተጨባጭ መረጃዎች በማስደገፍ ግለጹ?

**ማስታወሻ**

ስርዓተ-ትምህርትን ከትምህርት ፖሊሲ፣ ማስፈጸሚያ ስልቶች፣ ህጎችና መመሪያዎች ጋር አልፎ አልፎ በማመሳሰል የሚገልጹ ያሉ ቢሆንም ስርዐተ-ትምህርት ማለት ግን ከትምህርት ፖሊሲዉ የሚመነጭ ሆኖ የፖሊሲዉ ማስፈጸሚያ አንዱ ስልት ነዉ፡፡ ስለሆነም ስርዓተ-ትምህርት የአንድን አገር ትምህርት ከፖሊሲዉ ቀጥሎ የሚመራና ከትምህርት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ሁሉንም ጥያቄዎች (ማለትም የትምህርቱን ዓላማዎች፣ ይዘቶችና መልመጃዎች፣ የመማሪያና ማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የመርጃ መሳሪያዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ የመገምገሚያ ስልቶች፣ የተማሪዉንና የመምህሩን ፕሮፋይልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን መሰረት አድርገን የሚነሱ ጥያቄዎች) የሚመልስ ዶክመንት ነዉ፡፡ አሁን ባለዉ ሁኔታ በኢትዮጵያ ለአጠቃላይ ትምህርት የተዘጋጀ የስርዐተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያለ ሲሆን ማዕቀፉን መሰረት በማድረግ ደግሞ ፌሎዉ ቻርት፣ ሲላበስ፣ የተማሪ መጽሃፍት፣ የመምህሩ መምሪያ፣ ምርክ ሺቶችና ማኑዋሎች የተዘጋጁ መሆኑንና በጥቅሉ ግን እነዚህ ዶክመንቶች በሙሉ የስርዓተ-ትምህርት መሳሪያዎች በመባል የሚጠሩ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ደግሞ ስርዓተ-ትምህርት ማለት አንድን የአካዳሚክ ፕሮግራም (ከሰርቲፊኬት ጀምሮ እስከ ድህረ-ሶስተኛ ድግሪ ጥናቶች ወይም በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን በሙሉ) በበላይነት የሚመራ ዶክመንት እንደሆነ በመስኩ ያሉ ባለሞያዎች ያስረዳሉ፡፡

በአገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከጀመረ ከአንድ ምዕተ-አመትና ሁለት አስርት ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም ትምህርቱ በሚፈለገዉ ደረጃና ጥራት ዜጎችን በማፍራት ትምህርት በአገር ግንባታ ሂደት መጫወት የሚገባዉን ሚና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እያበረከተ ያለ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ ሆኖም ግን ለዘመናት የአገራችን ስርዓተ-ትምህርቶች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ከዉጭ ሀገራት የተቀዱ በመሆናቸዉና የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘቡ፣ የህዝቡን ባህልና ወግ ያላማከሉ፣ መጤ የሆኑ የዉጭ ሀገራት ባህሎችን የሚያንጸባርቁ፣ ዜጎች የሚፈለገዉን ዕዉቀት፣ ክህሎትና የባህሪ ለዉጦች በማምጣት በአገር ግንባታ ሂደት የሚጠበቅባቸዉን የጎላ ሚና እንዲጫወቱ የሚያደርግ ይዘት፣ ዝግጅት፣ አፈጻም፣ ግምገማና ማሻሻያ አልነበራቸዉም ተብሎ ይታማል፡፡ይህ ችግር ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎላ የመጣና እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑንና ይሄንኑ ችግር ለመቅረፍ ተብሎም በተለያዩ ጊዜያት የስርዓተ-ትምህርት ለዉጦችና ማሻሻያዎች የተደረጉ ቢሆኑም የተጠበቁትን ዉጤቶች ሳያመጡ አሁን ላለንበት ደረጃ መድረስ ተችሏል፡፡ በማያያዝም ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በማንበብ ጥያቄዎቹንም መልሱ፡፡

**ኬዝ 2.4.1፦ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅትና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚመለከት**

*አገራችን ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የአጠቃላይ ትምህርት የስርዓተ-ትምህርት ለዉጥ ስታደርግ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሷን ምሁራን ተጠቅማ፣ የዉጭ ባልቃ ገቢነቱንም በማስቀረትና የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ስርዓተ-ትምህርቶችን ለማዘጋጀት ጥረት ታደርግ በነበረበት ወቅት በትምህርት ዘርፉ የነበሩ እና የተለያየ የስራ ድርሻ የነበራቸዉ አካላት ከሌሎች የዉጭ አገር የድጋፍ ሰጪ አካላትና አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር የነበራቸዉ ግንኙነት በመጠቀም ሂደቱ እንዲጨናገፍና ዉድቅ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ እንደነበረና ይሄም የራሳቸዉን የግል ጥቅም ለማስከበር ሲባል የተደረገ እንቅስቃሴ እንደነበረ በወቅቱ በየደረጃዉ በተደረጉ ዉይይቶችና ግምገማዎች ለማወቅ ተችሏል።* በእናንተ እሳቤ ይህ አይነቱ ተግባር የተፈለገዉን አላማ ከማሳካት አንጻር ምን አንድምታ ይኖረዋል? ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመስኩ ከማስፋፋት አንጻርስ እንዴት ታያላችሁ? ብቃታ ያላቸዉና የአገሪቱን ችግሮች መቅረፍ የሚችሉ ዜጎችን በትምህርት አንጻ ለማዉጣት ከሚደረገዉ ጥረት አንጻር ተጽዕኖ ይኖረዋል ወይ?

**ማስታወሻ**

የአንድ አገር ስርዓተ-ትምህርት የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ዜጎች የሚጠበቅባቸዉን የአገር ግንባታ ስራ በብቃትና በብልሃት መወጣት እንዲችሉ፣ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚጠየፉ፣ የልፋታቸዉን ፍሬ ብቻ የሚሹ፣ ስራ ወዳድ ዜጎች በመቅረጽ ሂደት ትልቁን የመሪነት ሚና የሚጫወት መሆኑ ግልጽ ነዉ። ነገር ግን በስርዓተ-ትምህርቱ ዉስጥ እነዚህ ጉዳዮች በአግባቡ ትኩረት አግኝተዉ የትምህርቱ አካል ሆነዉ ለዜጎች መቅረብ ካልቻሉና ዜጎችም በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ማካበት የሚገባቸዉን ብቃቶች ካላጎለበቱ የሚጠበቅባቸዉን በአግባቡ ለመወጣት የሚቸገሩ ከመሆናቸዉም በላይ በአገር ላይ ከፍተኛ የሆነ ክሳራ የሚያስከትል ድርጊት ዉስጥም የመሳተፍ እድላቸዉ የላቀ ይሆናል።

ስለዚህ አገር ወዳድ፣ ብቃት ያለዉ፣ በጥሩ ስነ-ምግባር የታነጸ፣ አምራችና ትጉህ የሆነ ዜጋን ለመፍጠር የስርዓተ-ትምህርት ሚና የጎላ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ስርዓተ-ትምህርቱ ትምህርትን መልክ የሚያስይዝ፣ የሚመራ፣ ተግባር-ተኮር በሆነ መልኩ እንዲሰጥ እና የትምህርቱም ፍሬ ያማረ እንዲሆን የማድረግ አቅሙ እጅግ ከፍተኛ ነዉ። የአገሪቱ የትምህርት ስርዓት ጥሩ ከሆነ መምህራንም በጥሩ ሁኔታ እንዲያስተምሩና ተማሪዎችም በነቃ ሁኔታ ተምረዉ የሚጠበቅባቸዉን ብቃት እንዲያጎለብቱ መንገድ የሚያመቻች በመሆኑ ስርዓተ-ትምህርት የሚጫወተዉ ሚና ጉልህ ነዉ።

ሆኖም ግን ስርዓተ-ትምህርቱ ሲነደፍም ሆነ ሲተገበር በዚህ አይነት እሳቤ ካልተቃኘና የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡ መወጣት ካልቻለ በአገር እድገት ላይ የሚያሳርፈዉ ጉዳት እጅግ የከፋ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነቱ እጅግ ሰፊ የሚሆንበት አጋጣሚዎች ይኖራሉ። ለምሳሌ በኬዝ 3.4.1 ለማየት እንደተሞከረዉ ስርዓተ-ትምህርት በሚዘጋጅበት ጊዜ በጥብቅ ዲሲፒሊንና በአገር ወዳድነት ስሜት መመራት ይፈልጋል። አገርን ለችግር የሚዳርጉና የዜጎችን የወደፊት እድገት እጣ ፈንታ የሚገቱ ጉዳዮች በስርዓተ-ትምህርቱ አለመካተታቸዉን እንዲሁም የሚወሰዱ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችም ከአገሪቱ የእድገት ደረጃና ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ካልታዩና በፍላጎት ዳሰሳ ጥናቶች በደንብ ካልተደገፉ በቀጣይ የዜጎችን አቅም ግንባታ ሂደት ችግር ላይ የሚጥሉ ክስተቶች ልፈጠሩበት እንደሚችሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ። ብዙዉን ጊዜ የእኛን አገር ስርዓተ-ትምህረት ከጀርባዉ ሆነዉ የሚዘዉሩ እና የማስፈጸም የገንዘብ አቅም ያላቸዉ የአለም አገራትና ተቋማት ፍላጎቶች የሚታይባቸዉ መነሻ ሃሳቦች እንደ ምሳሌ በመዉሰድ ስርዓተ-ትምህርቱም ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች በከፍተኛ ደረጃ ተጋልጦ ያለ መሆኑን የሚያሳዩ ጥናቶችም መኖራቸዉ መስኩን በጥንቃቄ ማየት የሚገባ መሆኑን ያመላክታል።

## *2.5. የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ከሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ጋር ያለዉ ቁርኝት*

ከክፍል 2.1 እስከ 2.4 ከቀረቡት ሃሳቦች በአጠቃላይ የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ፣ ለተጋላጭነቱ እንደምክንያት የሚጠቀሱ ጉዳዮች፤ በማያያዝም በመምህራን ስልጠና እና በስርዓተ-ትምህርት ዙሪያም ተመሳሳይ ጉዳዮች ተነስተዉ ማብራሪያ ተሰጥቷል። በዚህ ክፍል ደግሞ የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ-ገብነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራቸዉን ግንኙነት ትኩረት በማድረግ ሃሳቦች ይቀርባሉ።

**መልመጃ 2.5.1. (6 ደቂቃዎች)**

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ።

1. የአገራችን የትምህርት አመራር ሁኔታ ምን ይመስላል? ከምልመላ ጀምሮ የስልጠና አሰጣጡ፣ ግምገማዉ እንድሁም ምደባዉ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉ አንድምታ ምን ይመስላል?

2. የትምህርት አመራሩ ጥራት ያለዉ ትምህርት ለዜጎች ከማቅረብ አንጻር የሚኖረዉን ሚና ዘርዝሩ?

3. በኢትዮጵያ ያለዉን የትምህርት አመራር የስራ ስምሪት ሁኔታ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር በማያያዝ ያላችሁን ሃሳብ ግለጹ? የፖለቲካ ጣልቃ-ገብነቱም ሊኖረዉ የሚችለዉን ተጽዕኖ አብራሩ?

**ማስታወሻ**

የአንድን አገር ትምህርት ዉጤታማ ሊያደርጉ ከሚችሉት መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል የትምህርት አመራሩ ሚና እጅግ የጎላ መሆኑ ግልጽ ነዉ። የትምህርት አመራሮቹ የመስኩን የተለየ ባህሪ በሚገባ የሚረዱና መማር-ማስተማሩን ዉጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ የአመርር ብቃቶችንና ጥበብን የተላበሱ (possessing competencies and arts expected of instructional leaders)፤ የትምህርትን ስራ በእቅድ የሚመሩ፣ አስፈላጊ ግብዐቶችን ለማሟላትና የትምህርት መስጫ ቦታዎች ለመማርና-ማስተማር ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚተጉ፤ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የሚጠበቁት ዉጤቶች እንዲመጡ ሙያዊ አስተዋጽኦዎችን የሚያደርጉ መሆን አለባቸዉ።

ሆኖም ግን በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ በትምህርት አመራርነት መስክ የተሳተፉ አካላት በዋናነት ስራቸዉን ሙያዉ በሚጠይቀዉ ልክ ከመምራት ይልቅ የፖለቲካ ተሳትፎአቸዉ ጎልቶ የሚታይ መሆኑ ይገለጻል። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን ትምህርት ለመምራት የሚያስፈልጉ የመፈጸም አቅሞችና ብቃቶች ሳይሆኑ የግለሰቦቹ የፖለቲካ ወገንተኝነትና ታማኝነት ብቻ እየታየ ምልመላ፣ ስልጠናና ምደባም የሚሰጣቸዉ ስለሆነ የሚጠበቅባቸዉን በአግባቡ ከመወጣት ይልቅ ላስቀመጣቸዉ አካል ብቻ አጎብዳጅ የመሆንና መስኩን ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ከመምራት ይልቅ በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እንዲናወጥ የማድረግ እድሉ በጣም ከፍተኛ ይሆናል።

ስለሆነም የትምህርት አመራሩ የሚጠበቅበትን ከመወጣት ይልቅ በፖለቲካ ዉስጥ በመዘፈቅ፣ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲስፋፉ እና መስኩ መስመሩን ስቶ ሌላ ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር ስለሚያደርገዉ በመማር-ማስተማሩ ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በ 2018 ዓ.ዓ በትምህርት ዘርፉ የተደረገዉን የጥናት ዉጤት ማያት በቂ ማሳያ ነዉ። በተጨማሪም ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በደንብ በማየት አንድምታዉን መገንዘብ ጠቃሚ ነዉ።

**ኬዝ 2.5.1፦ የአገራችን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የስራ አፈጻጸም ሁኔታ፤ የአመራሩ ሚናና ተጠያቂነት**

*ከ2014 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል ፈተና ተማሪዎችን ካስፈተኑት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ (በትንሹ ከአንድ ሽህ የሚበልጡ) ትምህርት ቤቶች አንድም ተማሪ ማሳለፍ ያልቻሉ መሆናቸዉን ትምህርት ሚኒስቴር በመግለጫዎቹ ዉስጥ በግልጽ ሲያወሳ የነበረ ቢሆንም እነዚያን ትምህርት ቤቶች በየደረጃዉ ሲመሩ የነበሩ የትምህርት አመራር አካላትና በትምህርት ቤቶቹም ሲያስተምሩ የነበሩ መምህራን ጉዳይ ብዙም ያልታየና ትኩረትም በአግባቡ ያላገኘ መሆኑ ግልጽ ነዉ።* በእናንተ እሳቤ ምንም እንኳን የትምህርት ጥራት ችግሮች በየደረጃዉ በነበሩት ስራዎች ጭምር መታየት ያለበት ቢሆንም እንዲህ አይነቱ አፈጻጸም ከትምህርት አመራሩ የስራ አፈጻጸምና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ጋር ምን ግንኙነት ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ተጠያቂነትን ከማስፈንና በትምህርት ዘርፉ እየታየ ያለዉን ስብራት ከመጠገን አንጻር ምን አንድምታ ይኖረዋል? በዚህ መልኩ መቀጠሉ አግባብነት አለዉ ብለዉ ያስባሉ? ካልሆነ ምን መደረግ አለበት ይላሉ? እንድህ አይነቱ ተግባር ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖረዉ መስተጋብር ምን ሊሆን ይችላል?

## *2.6. ሃላፊነትና ተጠያቂነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ ግንኙነት*

እስካሁን ከቀረቡት ጉዳዮች የትምህርት መስኩ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉን ነባራዊ ሁኔታና ለተጋላጭነቱም እንደ ምክንያት የሚነሱ ጉዳዮችን ከሌሎች ትምህርት-ነክ ማዕቀፎች ጋር በማስተያየት ገለጻዎች ተደርጓል። በመቀጥል ደግሞ በትምህርት ዘርፉ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን መስተጋብር ለማየት ጥረት ይደረጋል።

**መልመጃ 2.6.1 (5 ደቂቃዎች)**

ልምዳችሁን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ።

1. በእናንተ አረዳድ ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዴት ይገለጻል? ሃላፊነት ኖሮ ተጠያቂነት ባይኖር ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል? ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት

አንጻር በትምህርት መስኩ የሃላፊነትና ተጠያቂነት መስፈን ሚናዉ ምን ሊሆን ይችላል?

2. በአገራችን የትምህርት መስኩ ሃላፊነትና ተጠያቂነት በሚፈለገዉ ደረጃ እና በሁሉም የትምህርት እርከኖችና ተቋማት ሰፍኖአል ብሎ ያምናሉ? ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉ አንድምታስ ምንድነዉ?

**ማስታወሻ**

ሃላፊነት ማለት አንድ ሰዉ እንዲሰራዉ ወይንም እንዲተገብረዉ የተሰጠዉ የስራ ድርሻ ወይም የተጠያቂነት ወሰኑ የሚገደብበት ማለት ነው፡፡ በሌላ መልኩ ሃላፊነት ማለት በተመደብንበት የስራ መስክ ወይም ቦታ እንዲንወጣዉ የተጣለብን ግዴታ እንደ ማለት ነው፡፡ በትምህርት ሴክተሩ በተለያዩ ደረጃዎች ስራዎችን የሚተገብሩ አመራሮች፣ ሰራቶኞችና ተማሪዎች በየስራ ዘርፋቸዉ እንዲተገብሩት/ እንዲፈጽሙት የሚጠበቅባቸዉ የስራ ድርሻ ሃላፊነት ይባላል፡፡ ሃላፊነታችንን በሚጠበቀዉ የጥራት ደረጃ፣ ተጠያቂነትን በተላበሰ መልኩ እና ህግና ደንቡን መሰረት ባደረገ ሁኔታ መወጣት ይጠበቅብናል፡፡ ሃላፊነታችንን በአግባቡ የማንወጣ ከሆነ ግን ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ የመሆን እድሉ እጅግ የከፋ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ሁሉም በትምህርት ስራ ላይ የሚሳተፍ አካል የሚጠበቅበትን ሃላፊነት በአግባቡ መወጣት ያስፈልጋል፡፡ ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ ከዚሁ ጋር በማያያዝ እሳቤን ለመረዳትና ጥያቄዎቹንም ለመመለስ ሞክሩ፡፡

## ኬዝ 2.6.1፡- የመምህራን በተመደበላቸዉ ክፍለ-ጊዜ ተማሪዎችን ማስተማር፤ መግምገምና ዉጤት መስጠት እንዲሁም ሃላፊነትና ተጠያቂነትን የማስፈን ሁኔታ

*አንድ መምህር እንዲያስተምር የተመደበለትን ክፍለ ጊዜ/ የትምህርት አይነት በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳና ሰዓታት ተገኝቶ ከማስተማር ይልቅ ብዙ ክፍለ-ጊዜያትን መቅጣት፣ ከተማሪዎቹ ጋር በመስማማት የማይገባቸዉን ዉጤት የመስጠትና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን እንደሚፈጽም በተወሰኑ ስነ-ምግባር በተላበሱ ተማሪዎች ጥቆማ መሰረት የእለት ተዕለት ክትትል ተደርጎበት ድርጊቱ እዉነት መሆኑ ተረጋግጦ ቅጣት ተጣለበት፡፡* ይህ አይነቱ ተግባር ሃላፊነትንና ተጠያቂነትን በአግባቡ ከመወጣት አንጻር ምን ትርጉም አለዉ? ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉ አንድምታ ምንድነዉ? እንዲህ አይነቱ ተግባር በተማሪዎቹ የወደፊት እድገትና የስብዕና ግንባታ ላይ የሚኖረዉ አንድምታ ምንድነዉ?

**ማስታወሻ**

ተጠያቂነት የሚለው ቃል የእንግሊዝኛዉን (Accountability) የሚወክል ነው፡፡ የኦክስፎርድ አድቫንስድ መዝገበ ቃላት (Accountable፡- Responsible, answerable) በማለት ይገልጸዋል፡፡ የተጠያቂነት አሰራር ማለት ደግሞ ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበትና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ ለፈጸመው ጥፋት የሚጠየቅበትን በቅጣት ወይም ካሳ የማስከፈል ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት የሚከታተል፣ የሚቆጣጠርና እንደሚፈለገዉ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር እርምጃ ለመዉሰድ የሚያስችል ስልጣንና አቅም ያለዉ አካል ሊኖር ይገባል፡፡

በአንድ ተቋም ውስጥ የተጠያቂነት አሰራር ካልኖረ፣ በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሃላፊዎችና ሰራተኞች የተሰጣቸውን ሃላፊነት እንደሚመቻቸዉ እንዲጠቀሙበት ስለሚያደርግ ሙስናን ለመፈጸም የተመቻቸ ቦታ ይሆንላቸዋል፡፡ በርካታ ጥናቶች የተጠያቂነት ስርዓት አለመኖር ከሙስና ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸዉ ያመላክታሉ፡፡ በመሆኑም በአሰራር ውስጥ ተጠያቂነትን ማስፈን ሙስናን ለመከላከል ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ Robert Kilitgaard የተባሉ ተመራማሪ ተጠያቂነትና ሙስና ያላቸውን ትስስር እንደሚከተለዉ በቀመር ይገልጻሉ፡፡ C= M+D-A (Corruption equals monopoly plus Discretion minus Accountability) Robert Kilitgaard's (1988) formula. ሙስና = የስሌጣን ሞኖፖሊ + የመወሰን ስልጣን - ተጠያቂነት ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

በአንድ የትምህርት ተቋም የግልጽነትና የተጠያቂነት አለመኖር ከሚያስከትሉት ጉዳቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

- ሰራተኛው ማድረግ ያለበትንና የለሌበትን ስለማያዉቅ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት አይችልም፤
- የሚቆጣጠረው አካልም ይህንን ሳትፈጽም ቀርተሀል ብሎ ተጠያቂ ሊያደርገው አይችልም፤
- አገልግሎት ፈላጊዉም በቀላሉ የሚፈልገዉን አገልግሎት እንዳያገኝ ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር መብቱን ለማስከበርና ለመጠየቅ ስለሚቸገር ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ እንዲሆኑ በር ይከፍታል፤
- ለስርዓተ-አልበኝነት ምክንያት ይሆናል፤

- በአጠቃላይ ተጠያቂነት የሌለበት የአሰራር ስርዓት ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መፈጸሚያ ምቹ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

ስለሆነም በትምህርት ሴክተሩ ተጠያቂነትን ባሰፈነ መልኩ አሰራሮች ካልተዘረጉና ተጠያቂነት ካልሰፈነ በስተቀር የነገ አገር ተረካቢና ተስፋ የሚጣልበት ዜጋ የመገንባት ስራዉ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ችግር ዉስጥ የሚገባ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነዉ፡፡ ስለሆነም መስኩ ከእንደዚህ አይነት ክፍተቶች የጸዳና ሃላፊነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት መስክ እንዲሆን ሁሉም ተረባርቦ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## *2.7. ሥነ-ምግባርና ዕሴቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ ግንኙነት*

ከላይ በቀረቡት ክፍሎች በትምህርት መስኩ ያለዉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ከሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ጋር በማስተሳሰር ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ በትምህርት መስኩ ስነ-ምግባርና እሴቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን ቁርኝት ለማሳየት ጥረት ይደረጋል፡፡

**መልመጃ 2.7.1 (7 ደቂቃዎች)**

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መጀመሪያ በየግላችሁ ቀጥሎ ደግሞ ሁለት ሁለት በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

1. ስነ-ምግባር ማለት ምን ማለት ነዉ? እሴት ስባል ምን ትርጉም ይሰጣችኋል?
2. ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት አንጻር በትምህርት መስኩ የስነ-ምግባርና እሴቶች መነሳት አስፈላጊነቱን እንዴት ታያላችሁ?
3. በአገራችን በትምህርት መስኩ ተግባራዊ፤ ሙያዊና የስራ ስነ-ምግባሮችንና ምልካም እሴቶችን ስራ ላይ መዋል ምን ጥቅም አለዉ? ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉ አንድምታስ ምንድነዉ?

**ማስታወሻ**

ሥነ-ምግባር ኤቲክስ /Ethics/ የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካ ወይም ተመጣጣኝ የአማርኛ ትርጓሜ አለዉ፡፡ Ethics የእንግሉዝኛ ቃል ሲሆን የመጣውም ethos ከሚል

የግሪክ ቃል ነው። በግሪክ ቋንቋ ethos ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት ቦታ የሚል ትርጓሜ የነበረው ሲሆን ይህን ፊቺ በማስፋት ልምድ፣ ጸባይ፣ ባህርይ፣የአስተሳሰብና የአነጋገር ዘይቤ የሚሉ ትርጉሞችን እንደሚይዝ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ስለሆነም ስነ-ምግባር የማህበራዊ ሳይንስ አንድ የጥናት መስክ ሲሆን ትኩረት የሚያደርገውም ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው፣ ትክክለኛ የሆነውን ተግባር/ መልካም ምግባር የትኛው እንደሆነ የሚያመላክት እና በሰዎች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን እና ያልሆነውን፣ ጥሩውን እና መጥፎውን የምንለይበትና መልካሙን ይዘን እንዲንቀጥል የሚያደርግ የማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ነው። አንዳንድ ምሁራን ስነ-ምግባርን ከሌሎች ጉዳዮች ለምሳሌ ግብረ-ገብ (ሞራል)፣ ህግ እና ሌሎች ተያያዥ ሃሳቦች ጋር በማመሳሰል ሲጠቀሙበት የሚታዩ ቢሆንም በነዚህ ሃሳቦች መካከል መመሳሰሎች ቢኖሩም የየራሳቸዉ ትርጓሜም ያላቸዉ መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነዉ። ስነ-ምግባር የተለያዩ ዘርፎች ያሉት ስሆን እነሱም **ተግባራዊ፣ ሙያዊና የስራ** በመባል ይከፈላሉ። ሁሉም ግን ከአንድ ሰራተኛ የሚጠበቁ መሆናቸዉን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም በነዚህ ሃሳቦች ዙሪያ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለማግኘት ሌሎች ተያያዥ ጽሁፎችን በማንበብ መረዳት የሚቻሉ መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

እንደሚታወቀዉ ጥሩ እና መጥፎን እንዲሁም ትክክለኛንና ትክክል ያልሆነን ጉዳይ ለመለየት ምንም እንኳን የተለያዩ እሳቤዎች ቢኖሩም የትምህርት መስኩ እንደ ስነ-ምግባር ያስቀመጣቸዉን እሳቤዎች በመመርኮዝና ስራዎቻችንን በሚናከናዉንበት ጊዜም ከግንዛቤ በመዉሰድ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመጸየፍ መተግበር ያስፈልጋል። በሌላ መልኩ ስራዎቻችንን በሚናከናዉንበት ጊዜ የሙያ ስነ-ምግባሩ የሚያዘንን በትክክል ሳንሸራርፍ ስራ ላይ በማዋል አገር ከሴክተሩ የሚትጠብቀዉን ስነ-ምግባር የተላበሰ፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚጸየፍ፣ ለህብረተሰቡ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ፣ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ሳይሳሳና ሳይቆጠብ በታታሪነት የሚተገብር ዜጋን የማፍራት ተልዕኮ በአግባቡ መወጣት ይጠይቃል። በሌላ በኩል የትምህረት መስኩ እንደ መልካም እሴቶች የምቆጥራቸዉን ጉዳዮች በሚገባ በመረዳትና በተግባርም በመከተል ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች የጸዳ ተግባር በመፈጸም የአገር አለኝታችንን ማረጋገጥ ያሰፈልጋል። ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝም በሚገባ በማንበብ ተያይዘዉ የቀረቡ ጥያቄዎቹንም መልሱ።

### ኬዝ 2.7.1፦ በትምህርት መስኩ የሰዉ ሃይል ቅጥር፤ ዝዉዉርና እድገት ስራዎች ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ስነ-ምግባራትና እሴቶች

*በአንድ አንድ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች፣ የዞን ት/መምሪያዎች፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮዎች የሰዉ ሃይል ቅጥር፣ ዝዉዉርና እድገቶች በሚከናወኑበት ጊዜ ይሄንን አገልግሎት እንዲፈጽሙ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ ግለሰቦችና ቡድኖች አጋጣሚዉን በመጠቀም ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ጥረት ሲያደርጉ ማየት እየተለመደ መጥቷል፡፡ እንደምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ የመምህራንና ሰራተኞች ቅጥር ሲከናወን፤ የመምህራንና ሰራተኞች ዝዉዉር ሲፈጸም፤ የደረጃ እድገትና የትምህርት እድል ሲሰጥ ወዘተ… የሚስተዋሉ ያልተገባ ጥቅም የማግኘት እንቅስቃሴዎች በከፍተኛ ሁኔታ የሚታዩ መሆኑን በሚዲያዎች የሚተላለፉ መረጃዎችና በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ አሁን አሁን በነዚሁ ተቋማት የመምህራን ልማትና እደገት፤ በሰዉ ሃይል ልማትና አስተዳደር እና ሌሎች ተያያዥ ክፍሎች ዉስጥ በሃላፊነትና በባለሞያነት መስራት እጅግ አትራፊ መስክ እንደሆነ መነገር ከጀመረ ዉሎ አድሯል፡፡* በእናንተ እሳቤ እንዲህ አይነቱ ተግባር ስራን በጥሩ ስነ-ምግባርና በመልካም እሴቶች ተመርቶ መስራት ላይ የሚኖረዉ ተጽዕኖ ምንድነዉ? በትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲንሰራፉ ከማድረግ አንጻር ያላቸዉ አንድምታ ምንድነዉ?

**ማስታወሻ**

ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ዉስጥ የሚዘፈቁ ሰዎች ዓላማቸዉ በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚደረግ የአስተሳሰብ ጉድለት ዉጤት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ ለመቀየር ደግሞ ጥሩ የሆነ የስነ-ምግባርና የሞራል ዕሴቶች ግንባታ ማከናወን አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይሄንኑ እዉን ለማድረግ ደግሞ ጠንካራና ህዝባዊ መሰረት ያለዉ የፀረ-ሙስናና የብልሹ አሰራሮች ትግል ለመፍጠር መጀመሪያ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ በሆኑ እሳቤዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ያለዉ ማህበረሰብ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ግንዛቤዉ ያለዉ ማህበረሰብ ለፀረ-ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ትግል እንደ ስኬት መሰረት የሚወሰድ ጉዳይ ነዉ፡፡

### ኬዝ 2.7.2፦ በትምህርት ሴክተሩ ያልተገባ ዉድድርና የፈተና ላይ ኩሬጃዎች

*ላለፉት በርካታ ዓመታት በትምህርት ቤቶች በፈተናዎች ላይ የሚስተዋሉ ኩሬጃዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተንሰራፉ የመጡና መብት እስክመስል ድረስ ሲፈጸሙ የቆዩ በመሆናቸዉ ምክንያት ችግሩ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ መድረሱ ይታወቃል፡፡ በድርጊቱ ደግሞ ተማሪዎች ብቻ*

*ሳይሆኑ ፈተናዉን ለመፈተን፤ ለመቆጣጠርና ስራዉን በበላይነት ለመምራት ሃላፊነት የተሰጣቸዉ አካላት ጭምር የተሳተፉበት መሆኑና ይሄም ያልተገባ የዉድድርና የፉክክር ስሜትን በዉስጡ የያዘ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ችግሩ ከቁጥጥር ዉጭ በመሆኑም አገራዊና ሁሉን-አቀፍ መፍትሄ እንዲመጣ በማሰብ ካለፉት ሶስት አመታት ወዲህ ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ማየት የሚያስችሉ ተሞክሮዎች ቢደረጉም ኩሬጃን ግን ሙሉ በሙሉ ማስቆም አልተቻለም፡፡ የተቋማት ያልተገባ በዉጤት መፎካከር ስሜትም በአግባቡ አልተቃኘም፡፡ በመሆኑም ለኩሬጃ መስፋፋት አሁንም ጥሩ መደላድል ከመፍጠር አልተቆጠበም፡፡* በእናንተ አረዳድ እንዲህ አይነቱ ተግባር **ከተግባራዊ፤ ሙያዊና የስራ ስነ-ምግባሮችንና ምልካም እሴቶችን** ከማረጋገጥ አንሳር እንዴት ይታያል? ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በትምህርት መስኩ ከማስፋፋት አንጻር የሚኖራቸዉ አንድምታ ምንድነዉ? ከዜጎች የስብዕና ግንባታ ጋር ያለዉ ግንኙነትስ እንዴት ይታያል?

## *2.8. በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች*

ከላ በቀረቡት ክፍሎች በትምህርት መስኩ ያለዉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት፣ ለተጋላጭነቱ ምክንያቶችና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ በመስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መግለጫዎች ምን ምን እንደሆኑና በየትኞቹ የስራ ዘርፎች በስፋት እንደሚስተዋሉ ለግንዛቤ እንዲረዳን ዘርዘር ባለ መልኩ የሚንመለከት ይሆናል፡፡

**መልመጃ** 2.8.1 (8 **ደቂቃዎች**)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

1. የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫ ሲባል ምን ለማመላከት ነዉ? መገለጫዎቹስ ምንድናቸዉ?
2. በትምህርት መስኩ ያሉ የሙስና መገለጫዎች እነማን ናቸዉ? የብልሹ አሰራር መግልጫዎችስ ምንድናቸዉ?
3. በአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ያሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መግለጫዎች የሚታዉቋቸዉን ዘርዝሩ? በአካዳሚክ ዘርፍ ያሉትንም በዝርዝር አቅርቡ?

4. በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች በስፋት መኖር ለተገልጋዩ ማህብረሰብ ጥራት ያለዉ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር ለመስኩ ምን አንድምታ ይኖራቸዋል?

**ማስታወሻ**

የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች ሲባሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚፈጸምባቸዉ አኳሆኖችን/ድርጊቶችን ሁሉ የሚመለከት ጉዳይ ነዉ፡፡ እነሱም ቀጥሎ ከ(ሀ-ሠ) የቀረቡትን ዋና ዋና ድርጊቶች/እሳቤዎችን ያካትታል፡፡

**ሀ. ጉቦ**

ጉቦ አንድ ኃላፊ ወይም የመወሰን ሥልጣን ያለዉ የትምህርት መስኩ ሠራተኛ ተግባሩን ወይም በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ በማከናወን ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ሲገባው የተሰጠውን ኃላፊነት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም አንድን ኃላፊ ወይም የመወሰን ሥልጣን ያለዉን ሠራተኛ ተግባሩን ወይም በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዳያከናውን ሃሳቡን ወይም ድርጊቱን ማስለወጥ ወይም በኃላፊነቱ ማድረግ የሚገባውን ትክክለኛ ተግባር እንዳይፈጽም ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲፈጽም ለማድረግ የሚሰጥ ወይም የሚጠየቅ ተግባር ነው፡፡

**መልመጃ 2.8.2. (2 ደቂቃዎች)**

በእናንተ እሳቤ ስንት አይነት ጉቦዎች በትምህርት መስኩ ይስተዋላሉ? መገለጫዎቹስ ምንድናቸዉ?

**ማስታወሻ**

በትምህርት መስክም ጉቦን በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም፡-

1) ከአገልግሎት ፈላጊዉ የሚመነጭ ጉቦ (Bribery)፡- ይሄኛው የጉቦ ዓይነት ከአገልግሎት ተቀባይ /ከተገልጋይ/ የሚነሳ ሲሆን ለአገልግሎት ሰጪው መደለያ በመስጠት ሕጋዊ አሠራርን ለማስለወጥ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ይኸውም፡-

   ሀ. ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣ በቀላሉ የማይገኙ ነገሮችን ለማግኘት ወይም ከክፊያ ነፃ ለመሆን የሚፈጸም ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚገልጽ ነዉ፡፡ እንደምሳሌ

ለማንሳት ያክል የግል የትምህርት ተቋም ለመክፈት የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ለማግኘት፣ ከትምህርት ሴክተሩ ጋር የሚያያዙና በውጭ ምንዛሪ መንግስት የሚያወጣቸውን ጨረታዎች ለማሸነፍ፣ ለትምህርት አገልግሎት የሚዉል መሬት ድልድል ላይ የተሻለዉን ለማግኘት … ወዘተ፤

ለ. በትምህርት መስኩ ከሕጋዊ ክፊያ ነፃ ለመሆን፣ ታክስና የጉምሩክ ቀረጥ ለማስቀነስ፣ የዋጋ ቁጥጥር እንዳይኖር ለማድረግ … ወዘተ፤

ሐ. ፈጣን አገልግሎት ለማግኘት ወይም መረጃ ለማግኘት /የጨረታ መረጃዎች፣ የውሳኔ ሃሳቦችን አስቀድሞ ለማግኘት/፤

መ. አንድን ጥቅም ሌሎች እንዳይካፈሉና ለብቻ ለመጠቀም የሚከፈል/ ተወዳዳሪዎችን ከገበያ ለማስወጣት የሚደረግ እንቅስቃሴ መጥቀስ ይቻላል፡፡

2) ከአገልግሎት ሰጭ የሚመነጭ ጉቦ (Extortion or Extraction)- ይሄኛው የጉቦ ዓይነት መስጠት የሚገባውን ህጋዊ አገልግሎት በመከልከል ከአገልጋይ የሚጠየቅ ሲሆን ተገልጋዩን በማስፈራራት፣ በማስጨነቅ፣ ተጽዕኖ በማሳደር ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችም፡-

- ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን ከሚደርስባቸዉ ጥቃት እንጠብቃችኋለን በማለት፤
- በግልሰቦችና በድርጅቶች ላይ በስዉርና በተቀነባበረ መንገድ የተጋነነ የግብርና ታክስ ተመን እንዲጣልባቸዉ በማድረግና ያንን እንደሚያስቀንሱ ሆነዉ በመቅረብ፤
- የፈቃድ ጥያቄ (licenses) ያለአግባብ እንዲዘገዩ/መልስ እንዳያገኙ በማድረግና ጉዳዩ እንዲፋጠን አደርጋለዉ በማለት በተዘዋዋሪ በመጠቀም፤
- አንዳንድ የፖሊስ፣ የመከላከያ ወይንም የደህንነት አባላት በግለሰቦችና በድርጅቶች ላይ ተከታታይና ጭካኔ የተሞላበት ፍተሻና ክትትል በማድረግና በማስጨነቅ በተዘዋዋሪ የጉቦ ጥያቄ በማቅረብ፤
- ተገልጋዮች አገልግሎት ፍለጋ ወደ ተለያዩ ቢሮዎች ሲሄዱ ፋይላቸዉን በመደበቅ፣ ነገ ከነገ ወዲያ ተመለስ በማለትና በማጉላላት በተዘዋዋሪ ጉቦ መጠየቅ … ወዘተ ናቸዉ፡፡

## ኬዝ 2.8.1፡- ከግል የትምህርት ተቋማት አመታዊ ግብር አከፋፈልና የስራ ፈቃድ እድሳት ጋር የተያያዘ

*አንድ የግል የትምህርት ተቋም በወቅቱ የሚጠበቅበትን አመታዊ ግብርና የስራ ፈቃድ እድሳት ሳያደርግ ከቆየ በኋላ በሚመለከተዉ አካል በተደረገ ድንገተኛ ክትትልና ፍተሻ የተደረሰበት መሆኑን ሲገነዘብ ለክትትልና ፍተሻ የወጡትን አካላት በጥቅማ ጥቅም በመደለል ጉዳዩን ለማሳፈንና የተፈለገዉን እድሳትም በህገ-ወጥ መንገድ ለመጨረስ ሲንቀሳቀስ ተደርሶበት እርምጃ ተወሰደበት፡፡* በእናንተ እሳቤ እንዲህ አይነቱ ተግባር በትምህርት መስኩ ከሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራር መገለጫዎች ጋር የሚያገናኘዉ ጉዳይ አለ ወይ? ከላይ ከተጠቀሱት የጉቦ እሳቤዎች (ከአገልግሎት ሰጪ ወይም ተቀባይ የሚመነጭ ጉቦ) የተኛዉን የተከተለ ይመስላችኋል? ለምን? ይህ አይነቱ ተግባር በትምህርት ተቋማት መበራከት አገር ገንቢ እና ተስፋ የሚጣልባቸዉን ዜጎች በአግባቡ አስተምሮ ለስራ ዓለም ከማበርከት አንጻር የሚኖረዉ ተጽእኖ ይኖር ይሆን?

### ለ. ምዝበራ (Embezzlement)

በመንግስትና በሕዝብ የተሰጠን ኃላፊነትና ሥልጣን በመጠቀም በሥራው አጋጣሚ የሚያገኘውን የመንግስትና የሕዝብ ሃብት፣ የመንግሥት ንብረቶችን ለማስተዳደር ባለዉ ቀረቤታ በመጠቀም ወይም በቀጥታ በኃላፊነት እንዲጠብቃቸው የተሰጠውን ኃላፊነት ከለላ በማድረግ መስረቅ፣ መመዝበር፣ መውሰድ ወይም ማስወሰድ ወይም ያለአግባብ መገልገል ነው፡፡ ለምሳሌ- አንድን ተቋም ወይንም የተቋሙ ሃብት የሆነ ነገር ወስዶ ለሆነ የፖለቲካ ድርጅት አባል/ደጋፊ አሳልፎ መስጠት ወይንም ደግሞ አግባብ ባልሆነ መንገድ ማስተላለፍ ምዝባራ ተብሎ ይወሰዳል፡፡

## ኬዝ 2.8.2፡- ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የንብረት አወጋገድና በክራይ መልክ የመጠቀም ሁኔታ ጋር የተያያዘ

*አንድ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሃላፊ/ፕሬዚዳንት በከፍተኛ የዉጭ ምንዛሪ ለተቋሙ ስራ ተብሎ ተገዝቶ የገባን ተሽከርካሪ እንደተበላሸና ተጠግኖም አገልግሎት መስጠት የሚችል አይደለም በማለት በተሳሳተ መረጃ ንብረቱ እንዲወገድ ሲያደርግ ለራሱ የቅርብ ዘመድ በጣም በወረደ ዋጋ እንዲተላለፍ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ተሽከርካሪዉ መጠነኛ ጥገናና የቀለም ለዉጥ ብቻ ተደርጎለት በከፍተኛ ክራይ የትምህርት ተቋሙ መልሶ እንዲከራየዉና እንዲጠቀመዉ ያደረገ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጦና በተቋሙ የጸረ-ሙስናና*

ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ክፍል ተደርሶበት በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆን ተደረገ። ይህ አይነቱ ተግባር በትምህርት ተቋማት ከሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች ጋር ግንኙነት አለዉ ወይ? አለዉ ብላችሁ የሚታስቡ ከሆነ ከየትኛዉ መገለጫ ጋር የሚዛመድ ይመስላችኋል? ጉዳዩን ዉስብስብ የሚያደርገዉ ነገር አለ ወይ? የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ያላቸዉን የተጋላጭነት ነባራዊ ሁኔታ ይገልጻል ብላችሁ ታስባላችሁ ወይ? ሃሳቦቻችሁን በቡድን በመሆን አንሸራሽሩ።

### ሐ. ማጭበርበር (Fraud)

ይህ ድርጊት በዋነኛነት የኢኮኖሚ ወንጀል በመባል የሚፈረጅ ሲሆን በከፍተኛ ተንኮልና ቅንብር የሚፈጸም ነው። ይኸውም የመንግስት ተቋማትና ወኪልች ህገ-ወጥ ተግባራን ህጋዊ ሽፋን በመስጠት ሕገ-ወጥ በሆነ የንግድ ሥራ ላይ ሲሰማሩ/ በኮትሮባንድ ንግድ ውስጥ ሲገቡ፣ የተጭበረበሩ ሰነዶች በማዘጋጀትና እንዲዘጋጁ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሲሳተፉ፣ እንዲጠብቁና እንዲቆጣጠሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግስት ባለሥልጣኖች በንግድም ሆነ በሰነዶች ዙሪያ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሲፈጸም እያዩ እንዳላዩ በመሆን የሚፈጽሙት ድርጊት…ወዘተ ነው። በከፍተኛ ደረጃ ማጭበርበር ከሚፈረጁት ድርጊቶች መካከል የሚከተሉት ይካተታሉ፡-

- ጎስት የንግድ ተቋማትን በማቋቋም መነገድ፣ ለጎስት ሰራተኞች ፔሮል አዘጋጅቶ መክፈል፤
- ሰነዶችን በመሠረዝና በመደለዝ፣ የተሳሳተ የግዥ ማስረጃ በማቅረብ፣ የሐሰት ሰነዶችን በማዘጋጀት ወዘተ… በመሳሰሉት በመጠቀም ህገ-ወጥ ስራዎችን መስራት
- ሕገ-ወጥ የባንክ ኖቶችን በከፍተኛ ደረጃ ማሳተምና ማሰራጨት፣
- የመንግስት ተቋማት፣ የግል ተቋማት ወይም ግለሰቦች ለሰጧቸው አገልግሎቶች ክፊያ ሳይከፈሉ ሲቀሩ/ሲከለክሉ/፣ የመንግስት ወይም የፓርቲ ባለሥልጣናት በአደገኛ እጾችና በሰዎች ሕገ-ወጥ ዝውውር ሲሳተፉ፤
- ገንዘብን ከአገር ማሸሽና በሌላ አገር ሕጋዊ አስመስሎ ሥራ ላይ ማዋል (Money laundering)፣

- ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነ የአንድ አገር ምርትን ከፍተኛ ጥራት ያለው ምርት የምታመርት አገር ምርት በማስመሰል ሃሰተኛ የምስክር ወረቀት /ማረጋገጫ/ መስጠት ወይም መለያ ባጅ መለጠፍ፣ እንዲለጠፍ ፈቃድ መስጠት የመሳሰሉት ይገኙበታል።
- ሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ መታወቂያ ወረቀት ወይንም ማንኛውንም ሃሰተኛ ማረጋገጫ መስጠት፣
- ጊዜ ያለፈባቸዉንና የተበላሹ ምግቦች፣ መድሃኒቶች... ወዘተ በገበያ ላይ እንዲሸጡ ማረጋገጫ መስጠትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

### ኬዝ 2.8.3፡- ትክክለኛ ያልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎችና የትምህርት ተቋማት የሬጅስትራር አሰራሮች ጋር የሚያያዝ

*አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሬጅስትራር ሃላፊ ከሌሎች ግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን በተቋሙ ላልተማሩና በሚመለከታቸዉ አካላትም እዉቅና ላልነበራቸዉ ግለሰቦች የትምህርት ማስረጃዎችን (ሰርቲፊኬቶችንና ትራንስክርፕቶችን) በመስራትና በመስጠት ያልተገባ ጥቅም ሲያግበሰብሱ ለረጅም ጊዜያት ከቆዩ በኋላ ከአንድ ቀጣሪ መስሪያ ቤት በቀረበ የዶክመንት ይጣራልኝ ጥያቄ መሰረት ጉዳዩ በሌላ ገለልተኛ አካል ሲፈተሽ ይሄዉ ህገ-ወጥ ተግባር ሲፈጸም እንደነበረ በመታወቁ በጉዳዩ ዙሪያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳታፊ በነበሩ አካላት ላይ ህጋዊ እርምጃ ተወሰደ።* ከቀረበዉ ኬዝ የተገነዘባችሁትን ሃሳብ ለሌሎች ሰልጣኞች በማብራራት እንዲህ አይነቱ ድርጊት በትምህርት መስኩ ሊያስከትል የሚችለዉን ጉዳት በሰፊዉ ዘርዝሩ? ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በተቋማቱ እንዲንሰራፉ የማድረግ አቅሙንም ገምግሙ? ተግባሩ በራሳቸዉ ጥረት ለፍተዉና ደክመዉ ለተማሩ/ለሚማሩና የድካማቸዉን ፍሬ ብቻ በሚያገኙ ተማሪዎች ላይ የሚፈጥረዉ ጫናስ ይኖር ይሆን? ትምህርትን በጥራት በማቅረብ ዜጎች የሚጠበቅባቸዉን ብቃት አጎልብተዉ ሲገኙ ብቻ የሚገባቸዉን ዉጤት የመስጠትና አገር ገንቢ የሆኑና ተወዳዳሪ የሆኑ ምሩቃንን ለአገር የማበርከት ስራዉንስ ይጎዳል ብላችሁ ታስባላችሁ?

**መ. አድልዎ መፈጸም** (Nepotism, Favoritism, Clientlism)

ይህ የሙስናና ብልሹ አሰራር መገለጫ በቀጥታ የገንዘብ ጥቅምን የሚያስገኝ ባይመስልም በተዘዋዋሪ መንገድ ከረጅም ጊዜ ግንኙነት አኳያ ልዩ ልዩ ጥቅማ-ጥቅሞችን ማስገኘት ይችላል። ይህ የሙስናና ብልሹ አሰራር ወንጀል በዝምድና፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖትና በፆታ፣ በጋብቻ፣ ወይም በወዳጅነት ላይ ተመርኩዞ ከህዝብና ከመንግስት የተሰጠን ሥልጣን

በመጠቀም የግል ወይም የቡድን ፍላጎት ለማሟላትና ጥቅም ለማስገኘት ሲባል የሚፈጸም አድልኦ/ዎ ነዉ፡፡ በሌላ አገላለጽ ለዘመድ ወይም ለወዳጅ የሚደረግ የዉለታ ስራ ሲሆን ይህም ሹመትን በዝምድና መስጠትን፣ በያዙት ስልጣን ተጠቅሞ ዘመዶችንና ወዳጆችን ለመጥቀም ህግና ደንብ በጣሰ መንገድ ኮንትራቶች መስጠትን፣ ስራ ማስቀጠርን…ወዘተ የሚያካትት ነዉ፡፡ ዘርዘር ባለ መልኩ ጉዳዩን ለመረዳት ደግሞ ቀጥሎ የቀረቡትን ሃሳቦች ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

- **በዝምድና መስራት** (Nepotism):- ለሥጋ ዘመድ፣ ለቤተሰብ፣ ለሚስት፣ ለዘመዶች… ወዘተ. አግባብ ባልሆነ መንገድ ለመጥቀም የሚፈጸም ሲሆን ይህም፡
    - በሥራ ቅጥር፣ በዝውውር፣ በዕድገት ውድድር፤
    - ለትምህርት ዕድል በሚደረግ ምልመላ፤
    - የመንግስት ንብረት ወደ ግል በሚዛወርበት ጊዜ በሚደረግ ውድድር ቤተ-ዘመድን ማስቀደም … ወዘተ ያካትታል፡፡
- **ማዳላት** (Favoritism):- ለአንድ ወዳጅ ከቤተሰብ ወይም ከሥጋ ዝምድና ውጭ ለሆነ ሰው በእከክልኝ ልከክልህ አካሄድ የሚፈጸም ዉለታ ሲሆን ይህም ዜጎች በነፃ ውድድር ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ሌላ ጊዜ ዉለታ ለሚጠበቅበት ጓደኛ፣ የብሔረሰብ አባል፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባል… ወዘተ አሳልፎ መስጠትን የሚመለከት ነዉ፡፡ ይህ አይነቱ የሙስና ወንጀል ከተስፋፋና በብዛት የሚሰራበት ከሆነ የሕብረተሰቡን አንገት የሚያስደፋ፣ ዜጎች በአገራቸዉ ሠርተዉ ለመኖር ያላቸዉን መብትና ተስፋ የሚያቀጭጭና እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ አደገኛ ችግር ነዉ፡፡
- **በወዳጅነት መስራት** (Clientlism):- ይህ አይነቱ አድልዎ ደግሞ በአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ መካከል በተደጋጋሚ በሚቆጠር ግንኙነት መነሻ የሚፈጸም የሙስናና ብልሹ አሰራር ተግባር ነው፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ከሚፈጠር ተደጋጋሚ ግንኙነት የተነሳ ለደንበኞች ቅድሚያ በመስጠት ሰበብ በሌሎች ተገልጋዮች ላይ አድልዎን በመፈጸም በደል ያደርሳል፡፡

**ሠ. ስጦታ** (Gift)

በተቋማት የሚሰጥን አገልግሎት መነሻ በማድረግ ለአገልግሎት ሰጭዉ ዋጋ ያለዉ ስጦታ በመስጠት በኃላፊዉ ወይም በሠራተኛዉ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ተገቢ ያልሆነ ጥቅም

ለማግኘት የሚፈጸም ተግባር ነዉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ተግባር በአንዳንድ አገሮች አንድ ሰራተኛ መቀበል የሚገባዉን ስጦታ መጠን በህግ እስከመወሰን የደረሱበት ሁኔታ ሲኖር ከተወሰነዉ መጠን በላይ በሚሆንበት ጊዜ ግን የማስመዝገብ ግዴታ እንዳለባቸዉ በህጋቸዉ ያስቀምጣሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች መሆናቸዉን መረዳትና እነዚህ ተግባራት በትምህርት መስኩ ያሉና መልካቸዉን እየቀያየሩ የሚፈጸሙ መሆናቸዉን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመስኩ ደግሞ እንዲህ አይነት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች በስፋት መኖር የአገር ግንባታ ሂደቱን እጅግ በጣም ዉስብስብና ፈታኝ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ማስወገጃ ትግሉንም አስቸጋሪ የሚያደርግ መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነዉ፡፡

## 2.9. በትምህርት መስኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ያሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች

በክፍል 2.8 አጠቃላይ በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉትን ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች ዙሪያ ሰፋ ያለ ገለጻ ተደርጓል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ በመስኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ የስራ ክፍሎች የሚታዩት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች በስፋት ይቀርባሉ፡፡

**መልመጃ 2.9.1 (የ4 ደቂቃዎች)**

እስካሁን ያካበታችሁትን ልምድ በመጠቀም ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በየግላችሁ መልሱ፡፡

1. በትምህርት መስኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ የስራ ዘርፎች የሚባሉት እነ ማንን የሚያቅፉ ይመስላችኋል?
2. በዘርፉ ያሉት የሙስናና ብልሹ አሰራሮችስ ምንድናቸዉ? በተጨባጭ ምሳሌ አስደግፋችሁ ዘርዝሯቸዉ?
3. የትምህርት ሴክተሩን ተልዕኮ የማሳካት ሂደት ላይ የሚኖራቸዉን ተጽዕኖዎች ግለጹ?

**ማስታወሻ**

በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የትምህርት ዘርፉ በርካታ ተቋማትን ያቀፉ ሲሆን በነዚሁ ተቋማት የሚገኙ የአስተዳደርና ፋይናንስ የስራ ክፍሎቹን በምናይበት ጊዜ ተቋማቱ በጣም የተለያዩ መሆናቸውን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ትልቁ ልዩነታቸዉ

የግልና የመንግስት ተቋማት መሆናቸዉ ቢሆንም የመንግስትም ሆነው የተለያዩ አይነት አደረጃጀቶች እንዳላቸዉ ማወቅ ተገቢ ነዉ፡፡ የውስጥ ገቢ ከማመንጨት አኳያ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር አይነት ተቋማት ምንም የውስጥ ገቢ የሌላቸው በሚል ሲታዩ ሲችሉ ከበጀታቸው ከግማሽ በላይ የሆነውን ወጭያቸውን ከውስጥ ገቢ መሸፈን የሚችሉ የትምህርት ተቋማት እንዳሉም መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የውስጥ የቁጥጥር ስርዓት ከመዘርጋት አንፃር ጠንካራ የውስጥ ኦዲት ያላቸው በፌደራልና በክልል የሚገኙ የትምህርት አስተዳደር ተቋማት ሲሆኑ በተቃራኒዉ ደግሞ የተወሰኑ ተቋማት እንደዚህ አይነት የዉስጥ ቁጥጥር የሌላቸዉ እንደ የትምህርት ኮሌጆች፣ አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን እነዚህ የውስጥ ኦዲት የሌላቸው ተቋማት በክልል ኦዲተሮች በተለያዩ ወቅቶች የሚገመገሙ መሆኑን ግን ግንዚቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ በተቋማቱ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ቢሆንም ሁሉም በሚባል ደረጃ በውስጣቸው የአስተዳደርና የፋይናንስ ክፍል አላቸው፡፡ ዋና ስራዎቻቸዉም የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር፣ የፋይናንስና በጀት፣ ግዥና የንብረት አስተዳደር እንዲሁም ጠቅላላ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ እነዚህን የስራ ክፍሎች በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች በጣም ሰፊና የተለያዩ ናቸው፡፡

በተደረገዉ ጥናት መሰረት በነዚህ ተቋማትና የስራ ክፍሎች የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስጋቶች እንደሚከተለዉ ተለይተዉ ቀርቧል፡፡

- የሚገዙ እቃዎች የጥራት ችግር መኖር፣
- የጥገና አገልግሎት ጥራት መጓደል፣
- የግዥ ክፍል ለብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ መሆን፣
- የበጀት ድጎማዎችን ከመደበኛው ስራ ይልቅ ላልተፈለገ እና ከዋናዉ ተልዕኮ ዉጭ ለሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ ስራዎች ላይ ማዋል፣
- በኮሌጆችና ትምህርት ቤቶች የሚከናወነው የውጭ ኦዲት ሪፖርት ለትምህርት ቢሮው ብቻ ስለሚቀርብ ሰራተኛው ክፍተቱን ወይም ግኝቱን የማወቅ እድል የሌላቸዉ መሆኑ፣

- በተለያየ መልኩ የሚመጡ የድጋፍ በጀቶች አፈጻጸማቸው የተለያየ መሆን (ለምሳሌ፡- የስኩል ግራንት እና የብሎክ ግራንት የተለያየ አፈጻጸም ስላላቸው የበጀት አስተዳደሩን የተወሳሰበ እንዲሆን እያደረገዉ መሆኑ)፣
- ከውስጥ ገቢ የሚገኝ ገንዘብ ለብክነት የተጋለጠ መሆኑ፣
- አላስፈላጊ ግዥዎች (በተለይ ከመፅሃፍት ግዥ ጋር በተያያዘ) መኖራቸዉ፣
- መፅሃፍት ማሳተምና ሌሎች የቢሮ እቃዎችን በወረደ ጥራት መግዛት ይገኙበታል፡፡

**ኬዝ 2.9.1.፦ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዕቃዎች ግዥ ጋር የተያያዘ**

*በኢትዮጵያ በሚገኝ አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የጽዳት እቃዎች ግዥ ሲፈጸም የጥራት ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል የሚል ተደጋጋሚ ጥቆማዎች ይመጡ ስለነበረ ችግሮቹን ለመቅረፍ ታስቦ በቀጣይ በሚደረግ ተመሳሳይ ግዥ ጨረታ በሚከናወንበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ጥራት ያላቸዉን ዕቃዎች ለመግዛት በሚያስችል መልኩ ናሙናዎችም ቀርበዉ ደረጃ በማዉጣት የአሸናፊ ድርጅቱና የዕቃዎቹ መረጣ ጥራትን መሰረት አድርጎ እንዲካሄድና ግዥዉም በዚያዉ መሰረት እንዲፈጸም ዉሳኔ ተላለፈ፡፡ ግዥዉ በሚፈጸምበት ጊዜ እንደተለመደዉ ጥራታቸዉ እጅግ በጣም የወረዱ እቃዎች ተጭነዉ ወደ ተቋሙ ጊዜያዊ እቃ ማከማቻ ከደረሱ በኋላ ድንገተኛ ፍተሻ ሲደረግበት የአንደኛ አሸናፊ ድርጅቱ ናሙናዎች ሆን ተብሎ እንዲጠፉ (ለአቅራቢዉ ተመላሽ) የተደረጉና ተገዝተዉ የመጡት እቃዎችም ከቀሪ ሌሎች ናሙናዎች (ማለትም በሁለተኛ፣ በሶስተኛ እና በአራተኛ ደረጃ ከተለዩት ናሙናዎች) ጋር እንኳን ፈጽሞ የማይወዳደሩና ጥራታቸዉ በጣም የወረዱ ዕቃዎች መሆናቸዉ ስለተረጋገጠ ህጋዊ እርምጃ ተወሰደበት፡፡* በእናንተ እይታ እንድህ አይነቱ ተግባር በትምህርት መስኩ ለሚስተዋሉት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያላቸዉ አንድምታ ምንድነዉ? የተቋሙንና የትምህርት መስኩን የግዥ ስርዓት ይፈታተናል ብላችሁ ታስባላችሁ? ተቋሙ በሚሰጣቸዉ ሌሎች አገልግሎቶች ላይ የሚያሳድረዉ ጫና አለ ወይ?

**ማስታወሻ**

በአስተዳደርና ፋይናንስ የስራ ዘርፎች በሚገኙ የተለያዩ የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚታዩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችና ስጋቶች እንደየባህሪያቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ በቀዳሚነት በፋይናንስ የስራ ክፍል ከሚታዩ ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- ህጋዊ ያልሆነ ክፊያ መፈጸም፣

- የወጪና የገቢ የሂሳብ ሰነዶችን በአግባቡ አለመያዝ፣
- በለሌ ሰራተኛ ደመወዝ መክፈል፣
- ስራ ላይ ላልዋሉ ሰዎችና ስራ ላይ ላልዋሉ ቀናት የውሎ አበል መክፈል፣
- አንዳንድ ክፊያዎችን በወቅቱ አለመክፈል ወይም ገንዘብ በወቅቱ አለመሰብሰብ፣
- በተቋማት የተለያዩ ግብአቶችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች የሚያቀርቡት የዋጋ ጭማሪ ጥናት ሳያደርጉ በተጠየቀው መሰረት መክፈል፣
- ለበርካታ አመታት ያልተወራረዱ ሂሳቦች መኖር፣
- ከሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ ውጭ የባንክ አካውንት መክፈት፣ እና
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በየእለቱ አለማድረግ ይገኙበታል፡፡

በትምህርት መስኩ በተደረገዉ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት እንደተገለጸዉ የGEQUIP (General Education Quality Improvement Program For Equity) በጀት ድጋፍ ከፍተኛ ቢሆንም ለታለመለት ዓላማ ሲዉል ግን አይታይም የምል ግምገማ ከመሰንዘሩም በላይ ይህ ብር ርዕሰ-መምህራን እንደፈለጉት የሚያደርጉት ገንዘብ እንደሆነ እንደሚታምን አስረድቷል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የግዥ ክፍል ላይ ከሚታዩ ችግሮች መካከል የሆቴል አገልግሎቶች ግዥ በተለይ አዲስ አበባ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ላይ ተደጋጋሚ የአሰራር ክፍተቶች ሆኖ የተገኘ መሆኑን ጥናቱ አስገንዝቧል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ተቋማት ፍላጎት ያልቀረበበት የንብረት ግዥ መፈጸም፣ በመንግስት ግዥ ኤጀንሲ ከታገደ ድርጅት እቃ መግዛትና በዉድድር ወይም በጨረታ ያሸነፈን ድርጅት ግልጽ ባልሆነ ምክንያት እንዲወድቅ በማድረግ ከሌላ ድርጅት ንብረት መግዛት ሌላዉ የአሰራር ግድፈት ነዉ፡፡

ከንብረት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚታዩ ችግሮች ህንጻዎችንና የተገዙ ንብረቶችን የሚመለከቱ ናቸዉ፡፡ አንዳንድ የትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ግንባታ የሚያከናዉኑ ሲሆን ተገንብተዉ ያለቁ ህንጻዎችን ርክክብ አለማድረግና ርክክብ የተደረገላቸዉን ህንጻዎች ደግሞ በሰነድ አለመመዝገብና የባለቤትነት ሰነድ አለመያዝ ይታያል፡፡ ተገዝተዉ ከሚገቡ ንብረቶች መካከል በቆይታ የንብረት ጉድለት መከሰት፣ ንብረቶች ተከማችተዉ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ የማድረግ፣ ንብረቶቹን ባግባቡ በሰነድ አለመመዝገብና አልፎ አልፎ የንብረት ጉድለት መከሰት፣ ለስራ መዋል ያለባቸዉን ንብረቶች ባግባቡ ጥቅም ላይ አለማዋል ይታያል፡፡

የችግሮቹን አሳሳቢነት የበለጠ ለመረዳት ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ በማየትና ተያይዞ የተነሱትን ጥያቄዎች መልሱ።

**ኬዝ 2.9.2፦ በትምህርት ተቋማት የህንጻዎች ግንባታ፣ ርክክብና አስተዳደር የሚመለከት**

*አንድ የትምህርት ተቋም ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚዉሉ ህንጻዎችን በሚያስገነባበትና ርክክብ በሚያደርግበት ጊዜ ህንጻዎቹን አስመልክቶ የተያዙ መረጃዎችና ሰነዶች በአግባቡ ባለመቀመጣቸዉና ሲፈለጉም ባለመገኘታቸዉ የባለቤትነት መብት ለማረጋገጥ ተብሎ እንቅስቃሴ በሚጀምርበት ጊዜ በህግ አግባብ ለማረጋገጥ ያልቻለበት ሁኔታ ተፈጠረ።* ይህ አይነቱ አሰራር ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ጋር የሚኖረዉ ግንኙነት አለ ወይ? እናንተ ሃላፊነቱ ቢሰጣችሁ ችግሩ እንዳይፈጠር ምን ታደርጉ ነበር? እንዴትስ ችግሩን ለመፍታት ትሞክራላችሁ?

**ማስታወሻ**

በተመሳሳይ መልኩ በሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር የስራ ዘርፍ የሚታዩ ችግሮች ደግሞ የሚከተሉትን ያካትታሉ። በተድጋጋሚ በተለያዩ ተቋማት ከሚታዩት ችግሮች መካከል የመምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በስራ ሰዓታት አለመገኘት፣ የትምህርት ሰዓታትን ማባከን፣ በትምህርት ቤቶች አካባቢ ከደረጃ እድገት ጋር በተያያዘ የግልጸኝነት መጓደል፣ ከመምህራን ቅጥርና ዝዉዉር ጋር የሚገኛኙ ብልሹ አሰራሮች፣ ደንበኛን በአግባቡ አለማስተናግድ፣ አስተማሪዎችና አሰልጣኞች የራሳቸዉን ችሎታና አቅም በየጊዜዉ የማሳደግ ዉስንነት መኖር፣ ዝቅተኛ የስራ ተነሳሽነት መኖርና በተወሰኑ ቦታዎች ላይ በቅጥርና በደረጃ እድገት ሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችን ማስያዝ ይገኙበታል።

**ኬዝ 2.9.3፦ በትምህርት ተቋማት ሰራተኞች ዘንድ የሚስተዋሉ ሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችን የሚመለከት**

*በትምህርት መስኩ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶችና የትምህርት ማስረጃዎች ትክክለኛነት የማጣራት ስራዎች በሚፈጸሙበት ጊዜያት በርካታ የትምህርት ማስረጃዎች ሃሰተኛ ወይም በተሳሳተ መንገድ የተገኙ መሆናቸዉ በመረጋገጡ ምክንያት ብዛት ያላቸዉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ከነበሩበት ደረጃና ስራ እንዲነሱና ጉዳያቸዉ በህግ አግባብ እንዲታይ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል።* ይህ አይነቱ ድርጊትና አሰራር በትምህርት መስኩም ሆነ በአገር ግንባታ

ሂደት ላይ የሚኖረዉን ተጽዕኖ እንዴት ይገመግማሉ? ከሙስናና ብልሹ አሰራር ጋር ይያያዛል ወይ?

**ማስታወሻ**

እስካሁን የዳሰስናቸዉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች በትምህርት መስኩ መኖር የበለጠ ለመረዳት ይረዳ ዘንድ በመስኩ በተደረገዉ ጥናት የተገኙት አሃዚዊ መረጃዎች ደግሞ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡ በጥናቱ ከተሳተፉት ሰራተኞች መካከል 65 በመቶ የሚሆኑት በተቋማቸው ውስጥ የመልካም አስተዳደር ችግር አለ ብሎ የሚያስቡ ሲሆን ከዚህ አሃዝ የሚበልጡት (ከ 66 በመቶ በላይ የሚሆኑት) ተሳታፊዎች ደግሞ በተቋማቸዉ ሙስና አለ ብሎ ያስባሉ፡፡ በሌላ በኩል በተቋማቸው ውስጥ ሙስና የለም ብለዉ ከሚያስቡ ተሳታፉዎች መካከል ወደ 67 ከመቶ የሚሆኑት በተቋማቸው ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ የስራ ሂደቶች እንዳሉ አመላክቷል፡፡ይህ ደግሞ የሚያሳየዉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በአንድ ተቋም ዉስጥ በሆነ ጊዜ አለመከሰቱ በሌላ ጊዜ ላለመከሰቱ ዋስትና ሊሆን እንደማይችል ማሳያ ነዉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ዉስጥ 17 አይነት የሙስና ስጋቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ በትምህርት ዘርፉ ባሉ የአስተዳደርና ፋይናነስ የስራ ዘርፎች በርካታ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከሰት ምቹ የሆኑ ጉዳዮች መኖራቸዉን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ክፍተቶች በሚገባ ተረድቶ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተጽዕኖ ለመቀነስና ብሎም ለመግታት ሁሉም በትምህርት መስኩ ያሉ አካላት የበኩላቸዉን መልካም የሆነ ተሳትፎና ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የመዋጋት ትግል የተሳካ ለማድረግ ደግሞ በመስኩ ያሉት አካላት በተለይም ሰራተኞቹ በጉዳዩ ዙሪያ የተሸለ ግንዛቤ ኖሮአቸዉ የሚጠበቅባቸዉን እንዲወጡ ማስቻል አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም የሚጠበቅበትን በአግባቡ ከተወጣ ችግሮቹን የመቅረፍና ዜጎችን በጥሩ ስነ-ምግባርና ብቃት አጎልብቶ የነገዉ አገር ተረካቢ እንዲሆኑ የማደረግ ሃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት ከምን ጊዜዉም በላይ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

## *2.10. በአካዳሚክ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች*

ከላይ በቀረቡት ሁለት ክፍሎች (በክፍል 2.8 እና 2.9) በትምህርት ተቋማት የሚስተዋሉትን ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች እንዲሁም በትምህርት ሴክተሩ የአስተዳደርና ፋይናንስ መስኮች የሚታዩትን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች አስመልክቶ ዘርዘር

ያሉ ሃሳቦች ቀርበዉ ገለጻ ተደርጎባቸዋል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ በአካዳሚክ መስኩ የሚታዩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ ትኩረት ተደርጎ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

**መልመጃ 2.10.1. (8 ደቂቃዎች)**

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

1. በትምህርት መስኩ የአካዳሚክ ዘርፍ የሚባለዉ እነ ማንን የሚያቅፍ ይመስላችኋል?
2. በዘርፉ ያሉት የሙስናና ብልሹ አሰራሮችስ ምንድናቸዉ? በተጨባጭ ምሳሌ አስደግፋችሁ ዝርዝሯቸዉ?
3. ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ጥራት ያለዉ ትምህርት ለዜጎች በማዳረስ ብቃት ያላቸዉንና አገር ወዳድና ተረካቢ የሆኑ ዜጎችን በማፍራት ሂደት ላይ የሚኖራቸዉን ተጽዕኖዎች ግለጹ?

**ማስታወሻ**

በትምህርት መስኩ የአካዳሚክ ዘርፍ የሚባለዉ መስክ የመማር-ማስተማሩን ስራ በዋናነት የሚፈጽመዉ ዘርፍ ሲሆን ከአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፉ አስፈላጊዉን ድጋፍ እያገኘ በዋናነት ግን በየደረጃዉ ዜጎችን ዕዉቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ለዉጥ የሚያስታጥቅ (ብቃት ያለዉ ዜጋ የማፍራት ትልዕኮ ከግብ ለማደረስ ጥረት የሚያደረግ) አካል ነዉ፡፡ በስሩ መምህራን፣ ተማሪዎች እና መስኩን በአካዳሚክ መስመር መምራትና ማስተባበር ሃላፊነት የተሰጣቸዉን አካላት በሙሉ ያጠቃልላል፡፡

በዚህ መስክ በተደረገዉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስጋት የዳሰሳ ጥናት ቀጥሎ የቀረቡት ክፍተቶች እንደሚታዩ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከመማር ማስተማርና ስልጠና እንዲሁም ትምህርት አስተዳደር ጋር የተገናኙ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስጋቶች ተብለዉ ከተዘረዘሩት መካከል፡-

- ከመምህራን ወይም አሰልጣኞች ጋር በተያያዘ ከሚነሱ ስጋቶች መካከል በመምህራን ልማት የዘመድና የፓርቲ አሰራር፣ አድልዕና ጉቦ መቀበል እንደሚከሰት፤
- በመምህራን እና ሰራተኛ አስተዳደር ክፍል ህገ-ወጥ ቅጥር እና ዝውውር መኖር፤

- ከመምህራን አንፃር ሲታይ ደግሞ ለሁሉም እኩል ከመድረስ ይልቅ አንድ አንድ ተማሪዎችን ለይቶ ለመጥቀም በማሰብ አላስፈላጊ ውጤት የመስጠት፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ውጤት ማግኘት ሲገባቸው አለማግኘት የመሳሰሉ ችግሮች ይታያሉ፤

- የመምህራን ቅጥር ላይ ተቀራራቢ ዉጤት ሲመጣ አንድን በትዉዉቅ የማሳለፍ ነገር በተወሰኑ ቦታዎች ይታያል፤

- ከሃሰተኛ የትምህርት ሰነድ ጋር በተያያዘ የብቃት ማረጋገጫ እና ፈቃድ፣ የስራ ክፍሉን መስፈርት የማያሟሉ ተቋማትን ፈቃድ መስጠትና የፈቃድ እድሳት ስራ መስራት በመጀመሪያ ሊጠቀስ ይችላል፤

- በትምህርት ቤት አካባቢ የ8ኛ ክፍል የትምህርት ማስረጃዎች ሃሰተኛ ሆነው የተገኙበት አጋጣሚዎች ተከስቷል፤

- ከመምህራንና የትምህርት አስተዳደርና አመራር ላይ ያሉ ሰራተኞች ሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተገኘባቸው የትምህርት ተቋማት እንዳሉና በአንዳንድ ክልሎች ክትትል ተደርጎ ብዙ ሰዎች ላይ የእርምት እርምጃ እንደተወሰደ ማየት ተችሏል፤

- በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የትምህርት ማስረጃ የማጣራት ስራ ሲጀመር ሰራተኞች የመልቀቅ አዝማሚያዎች እንዳሳዩ ያሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል፤

- በግል ኮሌጆች ሰልጣኞች የሲ.ኦ.ሲ. (CoC) ምዜና እንዲያልፉ ያልተገባ ድጋፍ ማድረግና ባግባቡ ተምረው ላልጨረሱ ሰዎችና ፈፅሞ ላልተማሩ ሰዎች የትምህርት ማስረጃ ፕሪንት አድርጎ መሸጥ እንደሚታይ የተወሰኑ መረጃዎች አመላክተዋል፤

- ከዚሁ አንፃር አንዳንድ የግል ኮሌጆች የትምህርት ማስረጃን እውነተኛነት በተመለከተ ተደጋጋሚ ጥያቄ ከመንግስት አካላት እንደሚላክላቸዉና ምላሽ እንደሚሰጡ ጠቁመዋል፤

- በሬጅስትራር አካባቢ የሚታየው ችግርም የትምህርት ዘርፉ ውስጥ በቀጥታ ከመማር ማስተማር ጋር የሚገናኝ ስጋት ነው፡፡ በኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች በሚገኙ ሬጅስትራሮች ውስጥ የተማሪዎችን ውጤት የማሳሳትና ከዚያም አልፎ የማጭበርበር ተግባር ይፈፀማል፡፡ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የሚሰጡ የሬጂስትራር ሰራተኞች እንዳሉም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ይህ ችግር በግል ተቋማት ብቻም ሳይሆን በመንግስት ተቋማትም ሊከሰት የሚችልበት እድሉ ታይቷል፤

- በአንዳንድ ቦታዎች የፕሮጀክት ሥራ ሳይሰራ ክፊያ ማጽደቅ፣ የስራውን ጥራት ለድርድር ማቅረብና በኔትዎርክ መስራት ይከሰታል፤
- የመምህራን እና የሰራተኛ አስተዳደር ላይም ችግሮች እንዳሉ ጥናቶች ይጠቁማሉ፤
- የትምህርት ቤቶችን ብቃት የሚያረጋገጡ እና ፈቃድ የሚሰጡ የስራ ክፍሎች ላይም የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋቶች እንደሚታዩ መረጃ ሰጭዎች ጠቁመዋል፤
- ከዚህ ጋር በተያያዘ የተቋማት ፈቃድ እና እድሳት የሚሰጡ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት በርካታ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ጋር ስለሚገናኙ የሙስና ስጋት እንዳለባቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአጠቃላይ በአካዳሚክ መስኩ የሚታዩት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች በዋናነት ከላይ በተዘረዘሩት መልኩ የሚገለጹ መሆናቸዉንና በነዚህ ብቻ የተገደቡ እንዳልሆኑ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የነዚህ ችግሮች በመስኩ መኖር ደግሞ ተቋማቱ የሚጠበቅባቸዉን አግልግሎቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች በጸዳ መልኩ ለመስጠት የሚያስቸግራቸዉ ከመሆኑም በላይ የተቋቋሙለትን ተልዕኮ በሚገባ እንዳይወጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለሆነም በመስኩ ያሉት የአካዳሚክ ሰራተኞች እነዚህን ችግሮች በሚገባ በመረዳትና ያሏቸዉን ተጽዕኖም በመገንዘብ እኩይ ተግባራቱን ለመግታት በሚደረገዉ እንቅስቃሴ የበኩላቸዉን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

**መልመጃ 2.10.2 (5 ደቂቃዎች)**

በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ምክንያቶቻቸዉ ምን ምን እንደሆኑ በቡድን ሆናችሁ ዉይይት በማድረግ የተገነዘባችሁትን ለሌሎች ተሳታፊዎች አስረዱ?

**ማስታወሻ**

ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከሰት መነሻ ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱትን አስመልክቶ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ የችግሮቹ መነሻ ምክንያቶች በዋናነት ከሶስት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

- **የመጀመሪያው ከግለሰቦች ስነ-ምግባር አቋም ወይም የሞራል ልእልና ጋር የሚገናኝ** ነው፡፡ በሰዎች ዘንድ የሚታዩ የስነ-ምግባር ችግሮች ሲባል ሳይሰሩ በአጭር ጊዜ ለመክበር መፈለግ ወይም የሰዎች ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ መሆን፣

የሞራል መላሸቅ ወይም የሠራተኛው ዋልጌነት፣ ሱስ ለማርካት፣ ግልፅ አሰራር ያለመዉደድ፣ መመሪያና ደንብ ጠንቅቆ አለማወቅ፣ ግደለሽነት፣ የስራ ሃላፊነት የመውሰድ ዝቅተኛ ተነሳሽነት እና የማህበረሰቡ አመለካከት መቀየር የሚባሉ ምክንያቶችን ያካትታል።

- **ሁለተኛው መንስኤ ደግሞ ከአሰራር ጋር የተያያዘ ነው።** አሰራር ሲባል በየተቋማቱ የሚገኙ አመራሮች ያላቸው ተነሳሽነትና አርአያነት፣ በተቋሙ የተወሰደ የእርምት እርምጃዎችና ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተደረጉ አሰራሮችን የሚመለከት ነዉ። እንደምሳሌ ሊነሱ የሚችሉት ደግሞ፡-
    - የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር፣
    - የአመራሩ ልል መሆን፣
    - የህግ መላላት፣
    - የተፈጸሙ ወንጀሎች መፍትሄ ያለማግኘት፣
    - የሚሰራን ሰው አለማበረታታት፣
    - ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር አለመኖር፣
    - ሰራተኞች በብቃታቸውና ችሎታቸው ተመዝነው አለመቀጠር፣
    - ስልጠና አለመኖር፣
    - ማበረታቻ (Motivation) አለመኖር፣ እና
    - ፍትሃዊ አስተዳደር አለመኖርን እንደሚያካትት ተመላክቷል።
- **በሶስተኛነት ከኢኮኖሚ ወይም ከገቢ መጠን ጋር የሚነሱ ችግሮች** የሚታዩ ናቸዉ።

  በጥናቱ መሰረት ከኢኮኖሚ አንፃር በርካታ መረጃ ሰጭዎች እንደገለጹት ከሆነ የሰራተኛዉ ገቢ ማነስ ወይም መንግስት ለሰራተኞች የሚከፍለዉ ደመወዝ እና የኑሮ ደረጃዉ አለመመጣጠን እና የሰዎች ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ መሆን ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች በር የሚከፍት ሆኖ ተጠቅሷል።

ከዚህም በተጨማሪ በመስኩ ያሉ ሰራተኞች ስነ-ምግባርና መልካም እሴቶችን ጠብቀዉ ስራቸዉን በአግባቡ መስራት ላይም አልፎ አልፎ ክፍተቶች እንዳሉ የተደረገዉ ጥናት

አመላክቷል።ስለሆነም በነዚህ እና ሌሎች ተያያዝ ምክንያቶች የተነሳ በትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚከሰቱ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ።

### *የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ*

ይህ ሁለተኛ ምዕራፍ በትምህርት ዘርፉ ያለዉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነትና ለተጋላጭነቱም እንደምክንያት የሚወሰዱ ጉዳዮች እንዲሁም በመስኩ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ዘርዘር ያሉ ጉዳዮች ተዳስሰዉበታል። በዚሁ መሰረት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ምንነት፣ በትምህርት መስኩ ያሉት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት መስኮች፣ ለተጋላጭነቱም እንደ ምክንያት የሚወሰዱ፡- ከግለሰቦች የስነ-ምግባርና የሞራል ልዕልና ጋር የሚያያዙ፣ ከአሰራሮች ጋር የሚያያዙ እና ከኢኮኖሚ/የገቢ መጠን ማነስ ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች ተደሳስሰዋል። በመቀጠልም የአገሪቱ የትምህርት ጥራት መዉደቅ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ተያይዞ የሚኖረዉ ትርጉም ትኩረት ተሰጥቶት ቀርቧል። የመምህራን ስልጠና ሁኔታና የአገሪቱ የትምህርት ስርዓቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉ መስተጋብርም ተብራርቷል። በተያያዘ መልኩ የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነቱም ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት የነበራቸዉን ሚና በማዉሳት ገለጻ ተደርጓል። በመጨረሻም በትምህርት መስኩ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት እንዲሁም ስነ-ምግባርና የሞራል ልዕልና ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያላቸዉ አንድምታ ምን እንደሆነ ለመግለጽ ጥረት ተደርጓል።

በተጨማሪም የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫ ጽንሰ ሃሳብ ምን እንደሆነ ተብራርቷል። ቀጥሎም ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች የሆኑትና በትምህርት መስኩም የሚስተዋሉት እንደ ጉቦ፣ ምዝበራ፣ ማጭበርበር፣ አድልዖ መፈጸምና ስጦታ በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን በመቀጠል ደግሞ በአስተዳደርና ፋይናንስ እንዲሁም በአካዳሚክ ዘርፍ የሚስተዋሉ ዋና ዋና መገለጫዎች በስፋት ተዳስሰዋል። የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ደግሞ በመስኩ የተደረገዉን የዳሰሳ ጥናት መሰረት በማድረግ የተገኙ የጥናት ዉጤቶችን በመንተራስና የተለያዩ ኬዞችን በመጠቀም ገለጻ የተደረገ ሲሆን መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ያለዉ ተጋላጭነት በሚሰጡት አግልግሎቶች ላይም የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያስከትል በተወሰነ ደረጃ ለማመላከት ተሞክሯል።

## *የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች*

ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ መልሶቻችሁን በጽሁፍ ለአመቻቹ አቅርቡ።

1. የኢትዮጵያን የትምህርት ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ለይታችሁ ጻፉ?
2. የትምህርት ዘርፉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተጋላጭነት ምክኒያቶች ዘርዝሩ?
3. የትምህርት ጥራት መውደቅ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉን አንድምታ ግለጹ?
4. ሥርዓተ-ትምህርት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉን ግንኙነት በመዘርዘር በእያንዳንዳቸዉ ላይ የራሳችሁን ትንታነ ስጡ?
5. የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራችዉን ተያያዥነት በመገምገም ሃሳባችሁን በጽሁፍ አቅርቡ?
6. ሃላፊነትና ተጠያቂነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራቸዉን ቁርኝት ግለጹ?
7. ሥነ-ምግባር እና እሰቶቸ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን ግንኙነት ተንትኑ? ከእናንተ የእለት ተዕለት ስራ ጋር ያለዉን ቁርኝትም ግለጹ?
8. የትምህርት ዘርፉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች ዘርዝሩ?
9. በትምህርት መስኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ትንታነ ስጡ?
10. በአካዳሚክ ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎችን ዘርዝሩ?
11. የመሱናና ብልሹ አሰራሮች አጠቃላይ መገለጫዎችን በመዘርዘር የትምህርት መስኩ ምን ያክል ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንደተጋለጠ የተገነዘባችሁትን በጽሁፍ አቅርቡ?

## ምዕራፍ ሶስት፡- በትምህርት ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች እና የመከላከያ ስልቶች (3 ሰዓታት)

በምዕራፍ 2 በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎችና ምክንያቶቹ እንዲሁም በመስኩ የሚስተዋሉትን የሙስናና ብልሹ አስራሮች አስመልክቶ የተደረገዉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስጋት ዳሰሳ ጥናት መሰረት በማድረግ በስፋት የተለያዩ ጉዳዮችን ለማየት ተሞክሯል፡፡ መስኩን በአስተዳደርና ፋይናንስ እንዲሁም በአካዳሚ የስራ ዘርፎች በመክፈል የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስጋቶቹን/መገለጫዎቹን ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም እንደምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ ጉዳዮችም ተዳስሷል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በትምህርት ዘርፉ የሚስተዋሉት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች ምን ምን እንደሆኑ ለማየት ጥረት የሚደረግ ሆኖ ጉዳቶቹም በትዉልድ ላይ፣ በትምህርቱን ጥራት ላይ እንዲሁም አገር ገንቢ የሆኑ ዜጎችን የማፍራት ተግባራት ላይ የሚኖራቸዉን ተጽዕኖዎች በማዉሳት ሰፋ ያለ ገለጻ ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችም በስፋት ይዳሰሳሉ፡፡

### የምዕራፉ ዓላማዎች/የሚጠበቁ የባህሪ ገጽታዎች

የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች በትክክል ተከታትለዉ ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች፦

- በትምህርት ዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፡፡
- የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት በትምህርት ጥራት፣ በትዉልድና በአገር ግንባታ ስራዎች ላይ የሚኖረዉን አሉታዊ ተጽዕኖ ይተነትናሉ፡፡
- ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሏቸዉን ጉዳቶች በሚገባ በመረዳት ሌሎች የስራ ባለደረቦችም ግንዛቤ እንዲያገኙ የበኩላቸዉን በጎ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡
- የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶች ምንነትን ይገልጻሉ፡፡
- ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- በትምህርት ምስኩ በተጨባጭ ስራ ላይ ሊዉሉ የሚችሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን ይለያሉ፡፡
- በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከል የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይዘርዝራሉ፡፡

- በመስኩ የተለዩትን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን በመተግበር ግንባር-ቀደም ተምሳሌት በመሆን ስራቸዉን ያከናዉናሉ፡፡

## *3.1. በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች አስመልክቶ በመስኩ የተደረጉ የጥናት ዉጤቶች*

በዚህ ክፍል በፌዴራል የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት የዳሰሳ ጥናት በማደረግ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ያላቸዉ ነባራዊ ሁኔታ በመገንዘብ ሌሎች የመከላከያ ስልቶችን ለመንደፍ ታስቦ የተካሄዱትንና የተገኙ ዉጤቶችን መሰረት በማድረግ ሃሳቦች ይቀርባሉ፡፡

**መልመጃ 3.1.1 (5 ደቂቃዎች)**

ከታች የቀረበዉን ጥያቄ በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

1. በእናንተ አረዳድ በትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ የሚያስከትሉትን ጉዳቶች/ተጽዕኖዎች ከተወያያችሁበት በኋላ በዝርዝር ለሌሎች ተሳታፊዎች አስረዱ?

**ማስታወሻ**

በየትኛዉም ተቋም ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ የሚያደርሱት ጉዳቶች እንደሚኖሩ እሙን ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት በትምህርት መስኩ ሙስና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ ሊያደርሱ የሚችሉት ጉዳቶች የተለያዩ ቢሆኑም በዋናነት ግን የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

በመስኩ የተደረገዉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስጋት የዳሰሳ ጥናት እንዳሳየዉ የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፤ በመዝገብ ቤት ወይም ሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል ያላለፉ ተማሪዎችን እንዳለፉ ተደርጎ ሰርቲፍኬት መስጠት እና ወደሌላ ት/ቤት ሄደዉ እንዲማሩ ማድረግ፤ ሁለት ቦታ ላይ ደመወዝ መዉሰድ፤ ለተማሪ የማርክ ማጭበርበር መስራት፤ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት፤ በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፤ ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር እና ደረጃ ዕድገት፤ ህግና ደንብን ያልተከተለ ግዥ መፈጸም፤ የመረጃና ማስረጃ ማጭበርበር እና የአሰራር ግልጽነት መጓደል ብዙ ጉዳቶችን የሚያስከትሉ እንደሆኑ ተመላክቷል፡፡ በሌሉ ሰራተኞች ስም ደመውዝ መክፈል ወይም መዉሰድ እና ለስልጠና

መስተንግዶ የሚያዘዉ በጀት የተጋነነ መሆን ተብለዉ የተለዩት ቢከሰቱ የራሳቸዉ የሆነ ጉዳት/ ተጽዕኖ ሊያደርሱ እንደሚችሉ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

በተጨማሪም በትምህርት መስኩ ባሉ የተለያዩ የስራ ክፌልች ዉስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት ለማወቅ በተደረገዉ ጥናት መሰረት ግዥ፣ ፋይናንስ፣ ሰዉ ሃብት ልማትና አስተዳደር እንዲሁም ንብረት ክፍሎች አካባቢ የሚከሰቱ ክፍተቶች የራሳቸዉ የሆነ ተጽእኖ/ጉዳት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሬጅስትራር፣ መዝገብ ቤት/መረጃ ክፍል፣ ማህበረሰብ አገሌግልትና ምርምር የስራ ክፍሎች ዉስጥ ሙስና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ አሳሳቢ ተጽዕኖ/ጉዳት የሚያስከትሉ እንደሚችሉ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

በእያንዳንዱ የስራ ክፍል ባሉት ዝርዝር ስራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ ሊያስከትሉ የሚችሉት ጉዳቶች እንደሚከተሉ ቀርቧል፡፡

1. በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚደረጉ የግዥ ሂደቶች ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ ሊያስከትሉ የሚችሉት ተጽዕኖ/ጉዳት ሲታይ በግዥ በጀት ዝግጅት ወቅት (ለተቋሙ የማያስፈልጉ ዕቃዎች እንዲገዙ በጀት እንዲያዝ በማድረግ)፣ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት (የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን ብቻ በተለየ ሁኔታ እንዲጋበዙ አድርጎ በማዘጋጀት) እና በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ ወቅት የሚከሰቱ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የጎላ ተጽዕኖ/ጉዳት ያላቸዉ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡
2. በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚደረጉ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ ስራዎች ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰት ሊያስከትሉ ከሚችሏቸዉ ተጽዕኖዎች/ጉዳቶች መካከል ህጉ ከሚፈቅደዉ ዉጪ የሙያ ፈቃድ መስጠት፣ ህጉ ከሚፈቅደዉ ዉጪ የሙያ ፈቃድ እድሳት ማካሄድ እና ህጉ ከሚፈቅደዉ ዉጪ የሙያ ፈቃድ ስረዛ ማካሄድ የከፋ ተጽዕኖ/ጉዳት የሚያደርሱ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መሆናቸዉን በመስኩ የተደረገ ጥናት አመላክቷል፡፡
3. በትምህርት ተቋማት ውስጥ ከሚደረጉ የግንባታ ስራዎች መካከል ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ ሊያስከትሉ የሚችሉት ተጽዕኖዎች/ጉዳቶች ሲታዩ ድግሞ በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲካሄድ መፍቀድ፣ በጨረታ ጊዜ ብቃት የሌለዉ ተቋራጭ ጨረታዉን እንዲያሸንፍ ማድረግ፣ በህንፃ ርክክብ ጊዜ ጥራቱ የተጓደለ ህንፃ መረከብ እና የተሳሳተ የህንፃ ዲዛይን ማዉጣት

ተብለዉ የተለዩት የሙስናና ብልሹ አሰራሮች አደገኛ ተጽዕኖ/ጉዳት ያላቸዉ ተብለዉ የተለዩ መሆናቸዉን ጥናቱ አመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ በትምህርት መስኩ ስር ባሉ የተለያዩ የስራ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢከሰቱ ሊያስከትሉ የሚችሏቸዉ ጉዳቶች/ተጽዕኖዎች በርካቶች መሆናቸዉንና ከስራ ክፍል ስራ ክፍል የሚለያዩ እንዲሁም የጉዳቶቹ ደረጃም ልዩነት ያላቸዉ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ተቋማቱ በእንደዚህ አይነት ጉዳት ስር ከወደቁ ደግሞ የተጣለባቸዉን አገራዊ ተልዕኮ ለማሳካት እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ መግባት ስለሚችሉና በነዚሁ ተቋማት የሚገጥም ችግር ደግሞ ወደ ሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጭምር የመስፋፋት እድሉም ከፍተኛ በመሆኑ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት የመከላከልና ከተከሰተም በአፋጣኝ የዕርምት እርምጃ መዉሰድ እንደሚያስፈልገዉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚኖራቸዉን ጉዳቶች የበለጠ ለመረዳት ቀጥሎ የቀረቡትን ሃሳቦች ማብላላት አስፈላጊ ነዉ፡፡

**መልመጃ 3.1.2. (5 ደቂቃዎች)**

ቀጥሎ የቀረበዉን ጥያቄ በቡድን ሆናችሁ በመወያየት ምልስ ስጡበት፡፡

1. ከላይ በሰፊዉ የተዘረዘሩትና ሌሎች ተያያዥ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች በትምህርት መስኩ መንሰራፋት በትዉልድ ላይ፣ በትምህርት ጥራትና በሀገር ግንባታ ሂደት ላይ የሚኖራቸዉ ጉዳቶች ምንድናቸዉ?

**ማስታወሻ**

ኢትዮጵያ አደናቃፊ በሆኑና መጥፎ በነበሩ አጋጣሚዎች የተነሳ የተመቻቸ የፖለቲካና የማኅበራዊ ሕይወት ለማደላደል የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ አላጋጠማትም፡፡ በ1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተካሄደዉን የመንግስት ለውጥ ተከትሎ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች በአገሪቱ የልማት፣ የሠላም፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጉዞ ላይ ከፍተኛ እንቅፋት እየሆነ የመጣና እንደሚገኝ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ የትምህርት መስኩም በተመሳሳይ ሁኔታ ለከፋ ችግር እየተዳረገ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ይሄንኑ ጉዳት የበለጠ ለመረዳት ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በትምህርት መስኩ በሚንሰራፋበት ጊዜ በትዉልድ ግንባታ፣ በትምህርት ጥራትና በአገር ልማት ላይ የሚያስከትሏቸዉን ጉዳቶች እንደሚከተለዉ ማየት ተገቢ ነዉ፡፡

## 3.2. የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መጋለጥ በትዉልድ ግንባታ ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት

በዚህ ክፍል የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢጋለጥ በትዉልድ ግንባታ ሂደት ላይ ሊያስከትል የሚችሏቸዉን ጉዳቶች ትኩረት በማድረግ ገለጻ ይሰጣል፡፡

**መልመጃ 3.2.1 (5 ደቂቃዎች)**

1) በእናንተ እሳቤ ትዉልድ ማለት ምን ማለት ነወ? የትዉልድ ግንባታ ሲባልስ ምንድነዉ? ትዉልድስ እንዴት ነዉ የሚገነባዉ? ትዉልድን ለመገንባት ምን ምን ያስፈልጋል?
2) የአንድ አገር ትዉልድ በአግባቡና በስነ-ስርዓት የማይገነባ እና የነገዉ አገር ተረካቢ ዜጎች በእዉቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ጎልብተዉ ካልወጡ ምን ሊፈጠር ይችላል?
3) ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ጋር ምን የሚያገናኘዉ ጉዳይ አለ?

**ማስታወሻ**

**ትዉልድ** የሚባለዉ በሆነ የጊዜ ወሰን የተወለዱና ያደጉ የማህበረሰብ ክፍልን የሚወክል ሲሆን ትዉልዱ አገርን ተንከባክበዉ ካቆዩት ቅድመ-ዓያቶች፣ አያቶችና ወላጆች ተረክቦ የማስቀጠል ሃላፊነት የሚጠበቅባቸዉና ተስፋ የሚጣልባቸዉ ሰዎች ናቸዉ፡፡

**ኬዝ 3.2.1፡- በትዉልድ ግንባታ ሂደት የማህበረሱ ባህላዊ አሰራሮች ሚና**

*ኢትዮጵያ ዉስጥ በሚገኝ አንድ የማህበረሰብ ክፍል ትዉልድን ለነገዉ ሃላፊነት በአግባቡ እንዲበቁ በማሰብ በተወሰኑ የእድሜ ክልል የሚገኙትን ተወልደዉ እራሳቸዉን ካወቁ ጊዜ ጀምሮ በሚያልፉበት በተለያዩ የእድገት እርከኖች ዉስጥ የተለያዩ ሃላፊነቶችን እንዲወጡ በማድረግና ይሄንኑ መወጣት አለመወጣታቸዉን ለማረጋገጥ እንዲቻል ደግሞ በታላላቆችና አንጋፋ አዛዉንቶች ጭምር ክትትልና ምክር እንዲያገኙ በማድረግ እንዲበቁ ሁኔታዎች ይመቻችላቸዋል፡፡ በመቀጠልም በተለያዩ ደረጃዎች በማህብረሰቡ ሃላፊነቶች እየተሰጣቸዉ ማህበረሰቡን ባላቸዉ አቅምና ብቃት እንዲያገለግሉ በማድረግ የተጣለባቸዉን ሃላፊነት በአግባቡ በመወጣት የተሻለ አገልግሎት ለማህበረሰባቸዉ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡* እንዲህ አይነቱ ተግባር ከትዉልድ ግንባታ ሂደት ጋር የሚያያይዘዉ ነገር አለ ወይ? መሰል ድርጊቶቹ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢጋለጡ ልያስከትሉ የሚችሉት ጉዳት ምንድነዉ? ይህ አይነቱ ባህልና የአሰራር ስርዓት ቢጎለብት ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳት ከመቀነስ አንጻር ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

**ማስታወሻ**

የትዉልድ ግንባታ እጅግ በጣም ዉስብስብና ፈታኝ እንደሆነ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በዋናነት የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ማለትም ሰላም፣ ፖለቲካ፣ ትምህርት፣ ባህል፣ ወግ፣ እምነት፣ ኢኮኖሚ፣ የማህበረሱ የአኗኗር ዘይቤና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በትዉልድ ግንባታ ላይ የራሳቸዉን አንድምታ አላቸዉ፡፡የትዉልድ ግንባታ ሂደቱም ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቅና የብዙ አካላት ርብርብን የሚፈልግ ጉዳይ ነዉ፡፡ በትዉልድ ግንባታ ስራ ትምህርት የሚጫወተዉ ሚና እጅግ የጎላ ቢሆንም መስኩ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተተበተበ ከሆነና በትምህርት ተቋማትም ሆነ በሌሎች ተቋማት ከስነ-ምግባርና መልካም እሴቶች ያፈነገጡ አሰራሮች የሚስተዋሉ ከሆነ ስራዉን እጅግ ዉስብስብና ዉጤት አልባ ያደርገዋል፡፡

በሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተተበተበ የትምህርት መስክ ደግሞ የተጣለበትን ትዉልድን በተፈላጊ ዕዉቀቶች፣ ክህሎቶችና በጥሩ ስነ-ምግባር የመገንባት ስራን በአግባቡ መወጣት ስለሚቸግረዉና ዉጫዊ ነባራዊ ሁኔታዉም የማይፈቅድለት ስለሚሆን ትዉልድ የመገንባት ስራዉ እጅግ ፈታኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ብቃት ያለዉ፣ አገር ወዳድና ተቆርቋሪ እንዲሁም ተስፋ የሚጣልበትን ትዉልድ የመፍጠርና የመገንባት ስራን ችግር ዉስጥ የሚከትና በሂደት ደግሞ በማህበረሰቡና በአገር ደረጃ የነበረዉን ጠቃሚ ባህሎች፣ ወጎች፣ እምነቶች፣ ህግጋትና ሌሎች መመሪያዎች ወደ ጎን እየተገፉ በመጥፎ ሁኔታዎች እንዲተኩ በማድረግ አገር እንዲትፈርስ የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡

## 3.3. የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መጋለጥ በትምህርት ጥራት ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት

ከላይ በቀረቡት የምዕራፉ ክፍሎች የትምህረት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ቢጋለጥ ሊያስከትል የሚችላቸዉን ጉዳቶች ጠቅለል ባለ መልኩና በትዉልድ ግንባታ ላይ የሚኖረዉን ተጽዕኖ ትኩረት በማድረግ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ለትምህርት ጥራት ያላቸዉ አንድምታ ይቀርባል፡፡

**መልመጃ 3.3.1 (9 ደቂቃዎች)**

በቡድን በመሆን ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ካላችሁ ልምድና ግንዛቤ በመነሳት የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ አዳጋች የመሚያደርጉ ነገሮች ምንድናቸዉ?

2. ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በትምህረት መስኩ መንሰራፋት የትምህርትን ጥራት ከማስጠበቅ አንጻር ምን አንድምታ ይኖረዋል?
3. ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በተንሰራፉበት የትምህርት ተቋማት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ለዜጎች በማቅረብ ብቃት ያላቸዉንና አገርን በጥሩ መልኩ ሊገነቡ የሚችሉ ባለሞያዎችን ማፍራት ይቻላል ወይ? ከተቻለስ ስራዉ ቀላል ነዉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ሂደቱን ሊያወሳስቡ የሚችሉ ነገሮች ምን ይሆናሉ?

**ማስታወሻ**

የትምህርት መስኩ ለብዙ ችግሮች የተጋለጠ እንደመሆኑ መጠን መስኩ ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ደግሞ በባህሪዉ ለሌሎች ሴክተሮች ጭምር በቀላሉ የሚስፋፋ/የሚዛመትና ከፍተኛ የሆነ ቀዉስ የማስከተል አቅም ያለዉ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ በመሆኑም በሁሉም የትምህርት እርከኖችና ተቋማት የሚሰጠዉ ትምህርት ጥራቱ ካልተጠበቀ እና ተምረዉ የሚወጡ ዜጎችም የሚፈለገዉን እዉቀት፣ ክህሎትና የአስተሳሰብ ልዕልና ይዞ መገኘት ካልቻሉ አምራች ዜጋ መሆን ስለማይችሉና በሁሉም መስክ የመወዳደርና የመፈጸም አቅማቸዉ ችግር ዉስጥ ስለሚገባ የአገሪቱ የትምህርት ስርዓትም እንዲወድቅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ይህ በእንድህ እንዳለ በመስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚንሰራፉበት ከሆነ የትምህርቱን ጥራት የባሰ የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ ጥራቱን ለማሻሻል የሚደረግ ጥረትን ጭምር በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ ጉዳይ ነዉ፡፡ የችግሩን አሳሳቢነት የበለጠ ለመረዳት ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝና ተያይዞ የተጠየቁትን ጥያቄዎች በመመለስ ጥረት አድርጉ፡፡

**ኬዝ 3.3.1፡- ተማሪዎች ለትምህርት የሚሰጡት እሳቤ በጎ አለመሆን**

*በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉት በርካታ ተማሪዎች ለትምህርትና ለመማር የሚሰጡት ቦታ እጅግ የወረደ ከመሆኑም በላይ መማርን እንደ ጊዜ ማጥፊያ አድርጎ ማየትና የወደፊት ህይወታቸዉ ላይ ይህ ነዉ የሚባል ተጽእኖ እንደሌለዉ ማዉሳት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ይባስ ብሎም ምንም ሳይደክሙና ሳይለፉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ የተሻለ ነገር የማግኘት ፍላጎታቸዉ ደግሞ ከምንጊዜዉም በተለየ ሁኔታ ጨምሮ ይታያል፡፡ በዚህ ረገድ ወላጆች፣ መምህራንና የትምህርት አመራር አካላት ተማሪዎቹ በትምህርታቸዉ እንድበረቱ በማሰብ ብዙ ዋጋዎችን እየከፈሉ የበኩላቸዉን ጥረት እያደረጉ ቢሆንም እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ በመቅረፍ ተማሪዎቻቸዉ በትምህርታቸዉ ብርቱ እንዲሆኑ ማድረግ ግን አለመቻላቸዉን ይገልጻሉ፡፡* በእናንተ አረዳድ ይህ ዐይነቱ እሳቤ ሊመጣ የቻለበት ነባራዉ ሁኔታ ምንድነዉ? ጥራት ያለዉ ትምህርት ለዜጎች በማዳረስ በብቃቱ የሚተማመንና የነገ አገር ተረካቢ ትዉልድ የመፍጠር ሂደት ላይ ያላቸዉ ተግዳሮቶች ምንድናቸዉ? ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች

መንሰራፋት ጋር የሚያገናኘዉ ጉዳይ አለ ወይ? ጊዜዉ ለተማሪ ሰዉና ለትምህርት የተስማማ አይደለም፤ መማር በራሱ መጎዳት ነዉ የሚል እሳቤ የሚያንጸባርቁ አሉ፡፡ በሃሳባቸዉ ትስማማላችሁ ወይም አትስማሙም? ከምን ተነስተዉ ይሆን በዚህ መልኩ ሃሳባቸዉን ማንሳት የቻሉት? እንዲህ አይነቱ እሳቤስ በሂደት መስኩን ችግር ዉስጥ የሚከት ይመስላችኋል?

**ማስታወሻ**

ሙስና በተንሰራፋበት የትምህርት ዘርፍ ጥራት ያለዉ ትምህርት ለዜጎች ማዳረስ እጅግ ፈታኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ለትምህርት የሚሰጠዉ ዋጋና ለተማሪ ሰዉ የሚኖረዉ ቦታ ቀስ በቀስ እያሽቆለቆለ የሚሄድና በምትኩ በተለያዩ መንገዶች ሳይማሩና የሚፈለገዉን ብቃት ሳያጎለብቱ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች በመጠቀም የሚፈለጉትን ቦታዎች በቀላሉ የሚያገኙ ስለምመስላቸዉና በሂደት ደግሞ ችግሩ እጅግ ወደ ከፋ ደረጃ ስለሚደርስ የትምህርቱን ጥራት በጣም ይጎዳል፡፡ ጥራቱን ለማጎለበት የሚደረገዉንም እንቅስቃሴ በእጅጉ ስለሚፈታተነዉ ጉዳዩን ወደ ባሰ አዘቅጥ የሚከት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከተዉ አካል የችግሩን አሳሳቢነት በሚገባ በማጤን፣ በመረዳትና የጥራት ማሻሻያ ሃሳቦችን በማፍለቅ እንዲሁም የፈለቁትን የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ስልቶች ደግሞ በትክክልና በቆራጥነት በመተግበርና አስፈላጊዉን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ችግሩ እንዲቀረፈፍ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

## 3.4. የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች መጋለጥ በአገር ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳቶች

ከላይ በቀረቡት ክፍሎች ለመዳሰስ እንደተሞከረዉ የትምህርት መስኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች በሚጋለጥበት ጊዜ የሚያስከትለዉ ጉዳት በተለያየ ሁኔታ ቀርቧል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ በአገር ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት በተወሰነ ደረጃ ይቀርባል፡፡

**መልመጃ 3.4.1. (5 ደቂቃዎች)**

**ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በየግላችሁ መልሱ፡፡**

1) እስካሁን ያካበታችሁትን ግንዛቤዎች መነሻ በማድረግ በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት በአገር ላይ የሚኖራቸዉን ተጽዕኖዎች ዘርዝሩ?

2) የአገር ግንባታ ሂደት የተሳካ እንዲሆንና ብልጽግና እንዲረጋገጥ ለማስቻል ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚጸየፉ ዜጎችን መፍጠር ያስፈልጋል ብሎ ይገምታሉ?

**ማስታወሻ**

ትምህርት በአገር ግንባታ ሂደት የሚጫወተዉ ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ ይህን ሚናዉን በአግባቡ ለመወጣት የሚችለዉ ደግሞ በተለያዩ የሙያ መስኮችና የትምህርት ደረጃዎች ብቃት ያላቸዉን ባለሙያዎች ማፍራት ሲችል ነዉ፡፡ ይህን ተልዕኮ በአግባቡ መወጣት እንዲችል ደግሞ መስኩ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች በጸዳ መልኩ ስራዎችን መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን መስኩ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች ከተተበተበ አገር የመገንባት ተልዕኮዉን በአግባቡ ማሳካት አይችልም፡፡ ይልቁንም አገርን ለከፋ ችግር የሚዳርጉ፣ ችግር ፈጣሪ እና ጥገኛ ዜጎች የሚፈጠሩበት እድል የሰፋ ይሆናል፡፡ ችግሩን የበለጠ ለመረዳት ቀይሎ የቀረበዉን ኬዝ በማየት ተያይዞ የቀረቡት ጥያቄዎችም ለመመለስ ሞክሩ፡፡

**ኬዝ 3.4.1፡- ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚያያዝ**

*እንደሚታወቀዉ አገራችን ለበርካታ ዓመታት በብዙ ችግሮች ዉስጥ የሚትገኝ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ከችግሮቹ ለማላቀቅ በማሰብ በተለያዩ አካላት በተለያየ ጊዜያት ብዙ ጥረቶች ተደርጓል፤ እየተደረጉም ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን ሁኔታዉን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀምና ለአመታት ሲያልሙት የነበሩትን ፍላጎቶች በአቋራጭ ለማሳካት የሚፈልጉ ወገኖች በጣም ዘግናኝና አስከፊ የሆኑ ወንጀሎችንና ማጭበርበሮችን በመፈጸም አገር ወደለየላት ትርምስና ጦርነት እንዲትገባና እንዲትበታተን ለማድረግ እየጣሩ ይገኛሉ፡፡ ያገኙትን ሃብትና ንብረትም አገር አፍራሽ ለሆኑ እንቅስቃሴዎች እንዲዉል ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡* በእናንተ እሳቤ እንድህ አይነቱ ተግባር ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ጋር የሚያገናኘዉ ነገር አለ ወይ? የትምህርት መስኩ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች መተብተብ ለእንደዚህ አይነት ችግር አገርን ይዳርጋል ብለዉ ያስባሉ ወይ?

## *3.5. በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶች*

እስካሁን በቀረቡት ሃሳቦች የሙስና ወንጀሎችን፤ በትምህርት መስኩ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎችና ምክንያቶቹ፤ በመስኩ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲሁም የሚያስከትሉት ጉዳቶች ተዳስሰዋል፡፡ በዚህ የመጨረሻዉ ክፍል ደግሞ በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶች በሰፊዉ ይቀርባሉ፡፡

መልመጃ 3.5.1. (10 ደቂቃዎች)

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በሚገባ ካነበባችሁ በኂላ መጀመሪያ በየግላችሁ ቀጥሎም በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

1) ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል ይቻላል? እንዴት?

2) የመከላከያ ስልቶች ሲባሉ ምን ማለት ነዉ?
3) ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶች የሚባሉት እነማን ናቸዉ?
4) በትምህርት መስኩ የተንሰራፋዉን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከል የሚያስችሉ ዜዴዎች እነማን ናቸዉ?

**ማስታወሻ**

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ የትምህርት ዘርፉ ደግሞ በየጊዜዉ እየተወሳሰበ የመጣዉን ሙስናና ብልሹ አሰራር ስርዓት ባለዉ መልኩ ካልተከላከለ፤ በዘርፉ የሚፈጸሙ ሙስናዎችና ብልሹ አሰራሮች ለሌሎች ሴክተሮች የሙስናና ብልሹ አሰራር ዘር እንደ መዝራት ነው፡፡ የትምህርት ዘርፉ እነዚህን ችግሮች በመከላከል ስራ ምሳሌ መሆን ብቻ ሳይሆን ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚጸየፍና የሚከላከል ዜጋ እየፈጠረ በሌሎች ሴክተሮች ማሰማራት ይጠበቅበታል፡፡ የትምህርት ዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት ይረዳዉ ዘንድ በየጊዜው የሚሻሻሉ ዘርፎች ታሳቢ ያደረገ፤ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የትምርት ሴክተሩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

ዜጋን በእውቀት፣ በክህሎትና በስብዕና ግንባታ የሚገነቡት መደበኛና ኢ-መደበኛ ትምህርቶች ናቸው፡፡ ትምህርቶቹ ሥነ-ምግባርን፣ ግብረ-ገብነትን፣ መልካም እሴቶችን የሚያሰርፁ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ማስፈን፣ አስገዳጅ ሕጎችንና መመሪያዎችን መጠቀም፣ ስጋቶችን መቆጣጠር፣ ግንዛቤን የማዳበርና ሕዝብን አሳታፊ የማድረግ ሂደት በተሳካ ሁኔታ መፈጸም አለባቸው፡፡ እነዚህን በአግባቡ መተግበር ሙስና ከተከሰተ በኂላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፡፡ በትምህርት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ምእራፍ ውስጥ በትምህርት ዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ይዳሰሳሉ፡፡

ከብዙ በጥቂቱ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ጥራት ያለው ትምህርትን ማስፈን፤ተከታታይ የአቅም ግንባታን ማስፋፋት፤ የሃላፊነት ቦታና የሥራን ቅጥሮችን በችሎታ/ብቃትን መሠረት ማድረግ፤ ግንዛቤን በዜጎች ውስጥ ማስፋፋት፤

እውነተኛ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ፤ የሀብትን ምንጭ ማሳወቅ፤ ጠንካራ የኦዲት ሲስተም ማቋቋም፤ ጠንከር ያለ ቅጣትን መወሰንና ማስፈጸም፤ አነስተኛ ደመዎዝ ያላቸውን ሰዎች ለኑሯቸው መደጎሚያ/ማበረታቻ መስጠት፤ የሥነ-ምግባር ፖሊሲን በትክክል ማስፈጸም፤ በሁሉም አሰራር ግልጸኝነትን ማስፈን፤ መልካም አመራርን ማስፈን፤ ሕዝብን በብቃት ማሳተፍና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች በግልጽነት ማሳወቅ፤ ሙስናን ሪፖርት የማድረግና ምላሽ የማግኘት ሲስተም መመስረት፤ የቅጥር ሥርዓትን በግልጽነት ማሳወቅ፤ የሚዲያ ነጻነት ድሞክራሲያዊ ማድረግና ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ለምሳሌ፡- የግዥና ግንባታ ሥራዎችንና የመሳሰሉትን አዉቶሜት ማድረግ (በቴክኖሎጂ መቆጣጠር) እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህ በላይ በጥቅሉ ከተዘረዘሩት ዉስጥ አንዳንዶችን በመጠኑም ቢሆን ማብራራት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ይረዳሉ ተብለዉ ትኩረት ከተሰጣቸዉ ስልቶች/ዜዴዎች መካከል ወደ 10 የሚሆኑት እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

1. **የትምህርት ዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት**

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የትምህርት ዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው። የትምህርት ዘርፉ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም መልካም እሴቶችን ጠንቀቅው ሊያውቁ ይገባል። የትምህርት ዘርፉ የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች፣ የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል። በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ መልኩ እንዲሰሩና የሚጠበቅባቸዉን አገልግሎት በጥሩ ስነ-ምግባር እንዲሰጡ ለማድረግና አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው። ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በታች ያሉትን እሴቶች ማስረጽና ግንዛቤዎችን መስፋፋት ያስፈልጋል።

3.6. **እሴቶችን ማስረጽ፡-** ሰዎች በሕግ በማጠር ቅጣትን ፈርተው ከሙስና እንዲርቁ ከማድረግ ይልቅ፣ ሥነ-ምግባርን፣ ቅንነትን፣ የሞራል ከፍታን እንዲላበሱ ማድረጉ ተመራጭ ነው። በግለሰብ ሰራተኛውም ሆነ በተቋም የሞራል እሴቶችን በማስረጽ ሙስናን መከላከል ይቻላል። ይህ አቀራረብም አራት ዜዴዎች ይኖሩታል፡-

- ✓ **ጠንካራ የለውጥ አመራር ከላይ የማኖር መርህ፡-** ይህ ማለት ጠንካራ ፀረ-ሙስና እሴቶችን የተላበሰ፤ ሙስናን የሚጸየፍ፤ ተጽእኖ ፈጣሪና አርኣያ የሚሆን አመራር በቦታ መመደብ፤

- ✓ **የስልጠና ፕሮግራሞች**፡-ተከታታይ የሥነ-ምግባር ስልጠናዎችን ማደራጀትና መስጠት
- ✓ **ውስጣዊ ተነሳሽነት**፡- ሥነ-ምግባርንና እሴቶችን በሰራኞች በማስረጽ ከሽልማት ይልቅ ሰራተኞች አምነውበት ሙስናን የሚጠየፉ በራሳቸው ተነሳሽነት ሌሎችን የሚያነቃቁና የሚያስተምሩ፣ ሥርዓት ያላቸው ዜጎች የመፍጠር ሂደት ነው፡፡
- ✓ **የተቋምን ባህል መቀየር**፡- ከሙስና ነጻ የሆነና የተለወጠ ተቋማዊ ባህልን በደርጅቶች ማስፈን፤ በእርግጥ ጠንካራና ሥነ-ምግባር ያለው አመራር ካለ የድርጅት ባህል ሊቀየር ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የትምህርት ሴክተሩ የዕውቀት ማዕከል በመሆኑ ሰፊ የግንዛቤ ማዳበርያ ፕሮገራሞችን ዘርግቶ ለሌሎች ሴክተሮችም መትረፍና ሕዝብን አሳታፊ ማድረግ አለበት፡፡

3.7. **ግንዛቤን የማዳበርና ሕዝብን አሳታፊ የማድረግ ሂደት**፡-ይህ አቀራረብ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ሊቀንስ እንደሚችል ይታመናል፡፡ ይህም አምስት ተግባራትን ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም፡- *የግንዛቤ ንቅናቄ፣ ፊሽካ መንፋት፣ የሀሳብ ነጻነት፣ ነጻ ፕሬስ እና ኢ-መንግስት* (E-government) ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸዉ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

- ✓ **ግንዛቤን የማዳበር**፡- ይህ ፀረ ሙስና ትምህርትን የማስፋፋት ሂደት ነው፡፡ የግንዛቤ አሰጣጡ በሰፊው የሚካሄድ ሲሆን እሱም በቪዲዮ፣. በቴሌቪዥኖች፣ በሬድዮ እና በሌሎች ምቹ በሆኑ መንገዶች በሙሉ ነው፡፡
- ✓ **ፊሽካ መንፋት**፡- ይህ በእውነተኛ ፊሽካ መንፋት ሳይሆን የሙስና ምልክቶች ማለትም ኢ-ሞራላዊ ባህሪያት፣ ማግለሎች፣ ማጭበርበሮች፣ ትንኮሳዎች ወይም ሙስና ሲታይ ቶሎ ለሚመለከተው አካል ጥቆማ የመስጠት ሂደት ነው፡፡
- ✓ **የመረጃ ነጻነት**፡- ዜጎች የመንግስትን መረጃ የማግኘት ነጻነትን ማጎናጸፍ፤ ግልጸኝነትን መርህ አድርጎ መፈጸም ሙስናን ለመከላከል ይረዳል፡፡
- ✓ **ኢ-መንግስት** (E-government):- የመንግስትን የግዥ ሥርዓትና አገልግሎቶችን በመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍና ሕዝብ መረጃ እንዲያገኝ ማድረግ ናቸው፡፡

## 4. የሥነ-ምግባር ደንብንና ሕጎችን ተግባራዊ ማድረግ

### 4.2. የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር

ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህሪያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም የሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፤ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

### 4.3. አስገዳጅ ሕጎችንና መመሪያዎችን መጠቀም

ይህ ሁለት አበይት ጉዳዮች አሉት፤ እነሱም ውጫዊ የማነቃቂያ ዘዴን መጠቀምና ቅጣት ናቸው፡፡

- ✓ **ውጫዊ የማነቃቂያ ዘዴዎች**፡- ይህም ሰዎች ከሙስና ሲቆጠቡ በደመወዝ ጭማሪ ወይም በሌሎች መንገዶች ማበረታቻ በመስጠት እጃቸውን እንዲሰበስቡ በማድረግ ነው፡፡
- ✓ **ቅጣት**፡- ሰዎች የወጣን ሕግ ፈርተው እንዲታቀቡ በፀረ-ሙስና ሕጎች የሚጠቀሱ ቅጣቶች ተፈጻሚ የሚሆኑበት ነው፡፡

## 5. ግልጸኝነትና ተጠያቂነት

የትምህርት ሥርዓቱ በራሱ በማናቸውም አሰራር ግልጽ የሆነ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲኖር ያልተቋረጠ ግንዛቤ መፍጠር አለበት፡፡ የትምህርት ዘርፉ የፀረ-ሙስና ትምህርት በፕሮጀክት ወይም በሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ በማካተት የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ግልጽ የሆነ የግዢ ሥርዓት፣ የምዘና ዘዴ እና የዘርፉ አሰራሮች ግልጽና ተጠያቂነት በሚያሰፍን መንግድ መሆን አለበት፡፡ ማህበረሰብን ያሳተፈ ክትትልና ማህበራዊ ተጠያቂነትም ማስፈን አለበት፡፡ ለምሳሌ የትምህርት ቤት የወላጅ፤ የመምህርና የተማሪ ህብረት ከትምህርት ቤት አመራር ጋር በመሆን እቅዶችንና አፈጻጸማቸውን መከታተልና በትክክል መሰራቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ ኮሚቴ በትምህርት ቤት ያለውን የሙስና ሥጋቶችና ባህርያቶችን መለየት አለበት፡፡ ፀረ-ሙስና ሕጎችና መመሪያዎች ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት፡፡ ግንዛቤን ከመፍጠር ባሻገር የመምህራንና

የሰራተኞችን ሥራ በትጋት መከታተልና ክፍተቶች ከታየ ደግሞ አዎንታዊ በሆነ መንገድ በጥናትና ምርምር መረጃን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲስተካከል ማድረግ ነው፡፡

## 5.2. ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡ የትምህርት መስኩም የሚሰጠውን አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተቋማዊ አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

## 5.3. ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /ቅጣት ወይም ካሳ የመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር የመጠየቅ ስልጣን ያለዉ አካል መኖር አለበት፡፡ ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

# 6. የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በትምህርት ዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት

ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

**7. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል**

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሲፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

**8. ስጋቶችን ለመቆጣጠር አስቀድሞ መከላከል**

በተቋሙ ውስጥ ጠንካራ አመራር ካለ ሙስና ከመከሰቱ በፊት የሚቆጣጠርበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ዘዴ የሙስናን የመከሰት ዕድልን የሚቀንስ ሲሆን ስልቶቹም ዘርፈ ብዙ ናቸዉ፡፡ እነሱም፡- የኦዲት የሥጋቶች ዳሰሳ፣ በትኩረት ነገሮችን መከታተል፣ የአራት ዓይንማ መርሆዎች፣ አሴቶችን ማስታወቅ፣ የሃላፊነት ቦታዎችን መቀያየር፤ ብቃትን ያማከለ የአመራር ቅጥርና ምደባ ናቸው፡፡

- ✓ **ኦዲትና የሥጋቶች ዳሰሳ**፡- በተቋሙ ውስጥ የሙስና ሥጋቶች ናቸው የተባሉትን ወይም ተጋላጭ የሆኑትን መለየት፤ ክትትል የማድረግና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ሪፖርት በማድረግ ሙስናን የመከላከል ሂደት ነው፡፡
- ✓ **በትኩረት ነገሮችን መከታተል**፡- ይህ ሙስና ከድርጂቱ ውጪ ባሉ ምክንያቶች ሊከሰት ስለሚችል ነው፡፡ ከተቋሙ ጋር አብረው የሚሰሩ ድርጅቶች የሚፈልጉትን ለማግኘት ሲሉ የሚፈጥሩትን አስቀድሞ ስጋቶችን መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን

መርምሮ ርፖርት የሚያዝበት ነው፡፡ ይህም የዚያን ድርጅት ማንነትና ተዓማንነት የሚመረመርበት ሂደት ነው፡፡

- ✓ **የአራት ዓይንማ መርሆዎች**፡- ይህ ብዙውን ጊዜ ሙስና ድብቅ በመሆኑ በአንድ ሰው የሚፈጸም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በጉዳዮች ላይ አንድ ሰው ከሚወስን ይልቅ ሁለትና ከዚያ በላይ ሰው ቢያረጋግጥ ሙስናን ሊቀንስ ይችላል፡፡
- ✓ **አሴቶችን /ሀብት ማሳወቅ**፡- ሀብትን ማስመዝገብ፣ ተጠያቂነትን፣ የገቢ ምንጭን፤ የቢዝነስ ፍላጎትንና ሊኖሩ የሚችሉ ግጭቶችን አስቀድሞ ማሳወቅ ናቸው፡፡
- ✓ **የሀላፊነት ቦታዎችን መቀያየር**፡- ሙስና በሚፈጠርባቸው ተቋማት በየጊዜው የሥራ ቦታዎችን መቀያየር አስፈላጊ ነው፡፡
- ✓ **ብቃትን ያማከለ የአመራር ቅጥርና ምደባ**፡- የሚቀጠረው ሰው ችሎታው፣ ክህሎቱ፣ ተሞክሮው እና በአጠቃላይ ብቃቱ በሚገባ የተፈተሸ መሆን አለበት፡፡

### 9. የትምህርት ዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሜይንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን አለባቸዉ፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካል ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

### 10. የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቸዉ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- ✓ በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፤
- ✓ ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፤
- ✓ ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፤

✓ የጥቅም ግጭትን የመከላከከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፤

✓ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፤

✓ በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፤

✓ በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት።

**11. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት**

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው ጉዳይ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው። ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል። እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል።

**12. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል**

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው። በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

**ኬዝ 3.5.1፡- በትምህርት ጥራት አለመኖር የወደቁ ተቋማት**

*ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት (ከ1990ዎቹ ጀምሮ) የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በርካታ ምሩቃንን ሲያፈሩ እንደነበር አይካድም። አንዳንዱ ከልቡ ለትምህርት ጥራት ተጨንቆ ሲሰራ፣ ከፊሉ ደግሞ ስለሚያገኘው ትርፍ እንጂ ብዙም ሳይጨነቅ ድግሪ ሲሰጥ ቆይቷል፤ በዚህም በርካታ ተቋማት በአፈጻጸም ጉድለት ሕዝቡን አሳቀለዋል፤ በሕዝቡ ከፍተኛ ሮሮ ተሰምቷል፤ ያለእጅ መንሻ የሚሰራ በመጥፋቱ ተገልጋዩ ወገንም ሳይወድ በግድ ጉዳዩ እንዲፋጠንለት ወይም እንዲያልቅለት ጉቦ ይሰጣል። የግል ከፍተኛ ተቋማትን የሚቆጣጠረው ባለስልጣንም ከደረጃ በታች የሚሰሩ፣ ሳይፈቀድላቸው ፕሮግራም የከፈቱ እያለ ከማላዘን በስተቀር ጠንከር ያለ እርምጃ ሲወስድ ባለመታየቱ ምናልባትም ተቋማቱ ድግሪ ወደ መሸጥ*

ሳይሸጋገሩ አይቀሩም። ታድያ በቅርቡ የመውጫ ፈተና ተግባራዊ መሆኑን ተከትሎ በርካታ የግል ኮሌጆች ውጤት ማስመዝገብ አልቻሉም። ለምሳሌ በ2015 በአጠቃላይ የግል ኮሌጆች የማሳለፍ መጠናቸው 17 ፐርሰንት ብቻ ሲሆን፤ በ2016 ደግሞ ካላፈው ዓመት ዝቅ ባለ መንገድ ያለፉት የሁሉም የግል ተቋማት የመውጫ ፈተናን የማለፍ ምጣኔው 13 ፐርሰንት ብቻ ነው። ከዚህ ውስጥ የመውጫ ፈተናውን ምንም ያላሳለፉ 22 ተቋማት ፕሮግራማቸውን እንዳያካሄዱ እንዲሰረዙ ተደርጓል። ከመንግስት ተቋማት ጋር ስናነጻጽር የመንግስት ተቋማት በሁለቱም ጊዜያት ከ50 ፐርሰንት በላይ ሲያሳልፉ አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ እስከ 90 ፐርስነት የመውጫ ፈተናውን ሊያሳልፉ ችለዋል። ከዚህ ውስጥ አንዳንድ የትምህርት ክፍሎች ደግሞ 100 ፐርሰነት ሊያሳልፉ ችለዋል። ቀጥሎስ? እነዚህ የተቀሩት 50 ፐርሰንት እንኳን ማስመዝገብ ያልቻሉት የትምህርት ተቋማት ወይ ከፍ ያለ ውጤት ማስመዝግብ አለባቸው አለበለዚያ 22ቱ ኮሌጆች የገጠማቸው እጣ ፈንታ ሊገጥማቸው ይችላል። የግል ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የወደፊት ዕጣ ፈንታቸው ምን ይሆናል? የመዉጫ ፈተና ፋይዳውን እንዴት አያችሁት? ወደፊትስ ምን ይሁን?

## *የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ*

በዚህ ሶስተኛዉ ምዕራፍ በትምህርት ዘርፉ ያለዉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት የሚያስከትሉት ጉዳቶች እና የመከላከያ ስልቶቹ ምን እንደሚመስሉ ለመዳሰስ ተሞክሯል። ጉዳቶቹን የበለጠ ለመግለጽ በማሰብ መጀመሪያ በትምህርት መስኩ በጠቅላላዉ የሚስተዋሉት ጉዳቶች ዘርዘር ባለ መልኩ ቀርቧል። በመቀጠልም የሙስናና ብልሹ አሰራሮች በትምህርት መስኩ መንሰራፋት በተዉልድ ግንባታ፣ በትምህርት ጥራትና በአገር ግንባታ ላይ የሚያስከትሉት ጉዳቶች ቀርበዋል።

በትምህርት መስኩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት እጅግ በጣም ዉስብስብ የሆኑና ለማስተካከል እንኳን ረጅም ዓመታትን የሚጠይቁ ጉዳቶችን የሚያደርሱ መሆኑንና ጉዳቶቹም ደግሞ ቀስ በቀስ ወደ ሌሎች ተቋማት ጭምር በቀላሉ የመዛመትና በአገር ደረጃ ትልቅ ቀዉስ መፍጠር የሚችል ተጽዕኖ እንደሚኖረዉም ተገልጾአል። ስለሆነም የመስኩን ሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋትን በቁርጠኝነትና በብቃት የመታገል ስራዎች በአግባቡ መተግበር አስፈላጊ መሆኑም አጽንዖት ተሰጥቷል።

በመቀተልም የሙስንና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶቹን አስመልክቶ ሰፋ ያለ ማብራሪ ተሰጥቷል። በዚሁ መሰረት መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ

ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይደርስ ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ እነደሆነ ተገልጾአል፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም ሊደርስ የምችለዉን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስናና ብልሹ አሰረራሮች መከላከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከያ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አስር ዋና ዋና ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ አስር ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡

### *የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች*

በምዕራፍ አራት ስር የቀረቡትን ይዘቶች በሚገባ የተረዳችሁና የሚጠበቁ ብቃቶችን መጎናጸፋችሁን ለማወቅ ይረዳ ዘንድ ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች ስሩ፡፡

1) በትምህርት ዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳቶች ዘርዝሩ?
2) የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት በትምህርት ጥራት፣ በትዉልድና በአገር ግንባታ ስራዎች ላይ የሚኖረዉን አሉታዊ ተጽዕኖ በመተንተን ሃሳባችሁን ግለጹ?
3) ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሏቸዉን ጉዳቶች በሚገባ በመረዳት ሌሎች የስራ ባለደረቦችም ግንዛቤ እንዲያገኙበትን ዋና ዋና ሃሳቦች በጽሁፍ አቅርቡ?
4) በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?
5) በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኖቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
6) ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

7) በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

## *የሞጁሉ የራስ-ብቃት መገምገሚያ ጥያቄዎች*

### *መመሪያ*

በአምስቱም ምዕራፎች ስር የቀረቡትን ይዘቶች በሚገባ የተረዳችሁና የሚጠበቁ ብቃቶችን መጎናጸፋችሁን ለማወቅ ይረዳ ዘንድ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 1 የቀረቡትን የመመዘኛ ልኬቶችን በአግባቡ በማንበብ ያላችሁበትን የግንዛቤ ደረጃ አረጋግጡ፡፡ ያልተረዳችሁትና የሚጠበቀዉን ብቃት ደረጃ መጎናጽ አለመቻላችሁን ካወቃችሁ ደግሞ በጉዳዩ ዙሪያ የተሰጡትን ማስታወሻዎች ደጋግማችሁ በማንበብና በሚደረገዉ የፊት ለፊት ገለጻ ጊዜም ጉዳዩን በጥሞና በመከታተል ለመረዳት ሞክሩ፡፡

**ሰንጠረዥ 1.፡ የሞጁሉ የሰልጣኞች ብቃት መገምገሚያ ጥያቄዎች**

| ተ.ቁ | የብቃት መለኪያዎቹ ዝርዝር | አማራጮች | |
|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይደለም |
| 1 | የሙስናን ጽንሰ ሀሳብ በሚገባ መግለጽ እችላለዉ | | |
| 2 | ሙስና ወንጀል መሆኑን በመገንዘብ ለሌሎች አስረዳለዉ | | |
| 3 | የሙስናን መገለጫዎችን በሚገባ ማስረዳት እችላለዉ | | |
| 4 | በትምርት ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱትን የሙስና ኣይነቶች መግለጽ እችላሁ | | |
| 5 | የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያትንና ዋና ዋና የሙስና አይነቶችን መዘርዝር እችላለዉ | | |
| 6 | ትምህርት ምን እንደሆነ በሚገባ ማብራራት እችላለዉ | | |
| 7 | ሰዎች ድግሪ ኖሯቸው ለሙስናና ለብልሹ አሰራሮች የተጋለጡበትን ምክንያት መዘርዝር እችላለሁ | | |
| 8 | ጥራት ያለው ትምህርት ሙስናን ለመከላከል ያለውን ፋይዳ በሚገባ መተንተን እችላለሁ | | |
| 9 | የኢትዮጵያን የትምህርት ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት በሚገባ መለየት እችላለዉ፡፡ | | |
| 10 | የትምህርት ዘርፉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተጋላጭነት ምክንያቶች ተረድቸ መዘርዝር እችላለሁ፡፡ | | |
| 11 | የትምህርት ጥራት መውደቅ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለዉን አንድምታ መግለጽ እችላለዉ፡፡ | | |
| 12 | ሥርዓተ-ትምህርት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያለዉን ግንኙነት መተንተን እችላለሁ፡፡ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 13 | የትምህርት አመራርና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራችዉን ተያያዥነት መገምገም እችላለዉ፡፡ | | |
| 14 | ሃላፊነትና ተጠያቂነት ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር የሚኖራቸዉን ቁርኝት በመገንዘብ ሚናየን በአግባቡ መወጣት እችላለሁ፡፡ | | |
| 15 | ሥነ-ምግባር እና እሰቶቸ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ጋር ያላቸዉን ግንኙነት በመገንዘብ ጥሩ ሥነ-ምግባርና መልካም እሰቶችን በተላበሰ መልኩ ስራዎቸን መፈጸም እችላለሁ፡፡ | | |
| 16 | የትምህርት ዘርፉን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎች መዘርዘር እችላለሁ፡፡ | | |
| 17 | በትምህርት መስኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል መተንተን እችላለሁ፡፡ | | |
| 18 | በአካዳሚክ ዘርፉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መገለጫዎችን በዝርዝር በማመላከት ለሌሎች አስረዳለሁ፡፡ | | |
| 19 | የመሱናና ብልሹ አሰራሮች አጠቃላይ መገለጫዎችን በዝርዝር በመለየት የትምህርት መስኩ ምን ያክል ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንደተጋለጠ ለሌሎች ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | | |
| 20 | በትምህርት ዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳቶች መዘርዘር እችላለዉ፡፡ | | |
| 21 | በመስኩ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት የጉዳት መጠን መለየት እችላለዉ፡፡ | | |
| 22 | የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መንሰራፋት በትምህርት ጥራት፣ በትዉልድና በአገር ግንባታ ስራዎች ላይ የሚኖረዉን አሉታዊ ተጽዕኖ መተንተን እችላለዉ፡፡ | | |
| 23 | ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሏቸዉን ጉዳቶች በሚገባ በመረዳት ሌሎች የስራ ባለደረቦች ግንዛቤ እንዲያገኙ የበኩሌን በጎ አስተዋጽኦ ማድረግ እችላለዉ፡፡ | | |
| 24 | ስራዎቼን ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች በጸዳ መልኩ መስራት እችላለዉ፡፡ | | |
| 25 | የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶች ምንነትን ይገልጻሉ፡፡ | | |
| 26 | ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን ይዘረዝራሉ፡፡ | | |
| 26 | በትምህርት ምስኩ በተጨባች ስራ ላይ ሊዉሉ የሚችሉየሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን ይለያሉ፡፡ | | |
| 27 | በትምህርት መስኩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከል የሚስችሉ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይዘርዝራሉ፡፡ | | |
| 28 | በመስኩ የተለዩትን የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን በመተግበር ግንባር-ቀደም ተምሳሌት በመሆን ስራቸዉን ያከናዉናሉ፡፡ | | |

## *ዋቢዎች/ማጣቀሻዎች*


Federal Ethics and Anti-Corruption Commision (2012). *Ethiopia Second Corruption Perception Survey*. Addis Ababa.

Federal Ethics and Anti-Corruption Commision (2021). *Ethiopian National Corruption Perception Survey Third Report*, Addis Ababa.

Harvey, L., (2004). Analytic Quality Glossary. *Quality Research International*, http://www.qualityresearchinternational.com/glossary/

Ministry of Education (2003). Teacher Education System Overhaul (TESO) Handbook. *Ministry of Education, Addis Ababa.*

Ministry of Education (2018). Ethiopian Education Development Roadmap (2018-30). *Ministry of Education, Addis Ababa.*

Robert, Klitgaard (1988). Combating Corruption. *International Cooperation against Corruption*.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ፣ ፌዴራል ነጋሪተ ጋዜጣ፣ *የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 8811/2015 (2007 ዓ.ም)*

ዓለማየሁ ተክለማርምና ጌታቸው ታደስ (2013)፣ *የሕጸጽ ቅብብሎሽ፡* ሰላም ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2014). *የትምህርት ሴክተር የሙስና ስጋት ጥናት ሪፖርት፡፡* አዲስ አበባ

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015). *መሰረታዊ ሥነ-ምግባር ትምህርት ማስተማሪያና ማሰሌጠኛ ሞጁል፡፡* አዲስ አበባ

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015). *የሙስና ጽንሰ-ሀሳብ እና የመከላከያ ስሌቶች ማሰልጠኛ ሞጁል፡፡* አዲስ አበባ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION
ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et